

‹‹ሕዝብ ሁሉም የእሱ መሆኑን ማወቅ አለበት››

ጠበቃ ተማም አባቡልጉ



‹‹ፍርድ ቤት ...በገለልተኝነት ይሰራል የሚል እምነት የለኝም››

የሕግ አማካሪ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ወሰኔ



‹‹የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ራስን በራስ ሳንሱር እንድታደርግ ያስገድዳል››

ዳኛ ፀጋዬ ደምሴ


# የሚሊዮኖች ድምፅ

ዓርብ ጥር 18 /2007 ዓ.ም **ነፃነትን፣ፍትህንና እኩልነትን እናውጃለን!** አንደኛ ዓመት ቅፅ 1 ቁ 5 ዋጋ 10 ብር




**የጨለማ ውስጥ ብርቅርቅ ብርሃኖች!**

(ዳዊት ከበደ ወየሳ - ከአትላንታ) 11

# ‹‹ኃይለማርያም ደሳለኝ የአንድ ፋብሪካ ማናጀር ቢሆን ውጤታማ ይሆን ነበር››

**አቶ ኤርሚያስ ለገሠ/ የቀድሞ የመንግሥት ጉዳዮች ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ሚኒስትር ዴኤታ/**

## ‹‹የኢህአዴግ መሰረታዊ ባህሪና መርሆ ተቀይሯል የሚል እምነት የለኝም››

## ‹‹አቶ መለስ ...የሚያውቀውን ስለጻፍኩ ብዙ ይገረማል ብዬ አላስብም››

## ‹‹ለአቶ አንዷለም አራጌ አጋርነቴን በማሳየቴ አክብሮታቸውን ነግረውኛል››

## ‹‹የጫካ ሕግ የሆነው ‹ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት (Democratic centralism››እንዳለ ነው››



Exclusive interview

# ርዕሰ አንቀፅ

## ምርጫ ቦርድ የምርጫውን ሰላማዊ ሂደት ከማወክ ተግባሩ ሊታቀብ ይገባዋል!

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጠውን ሕገ-መንሥታዊ ተልዕኮ ህዝባዊ አደራ ወደ ጎን በመተው ለገዢው ፓርቲ ያለውን ወገንተኝነት በግልጽ በሚታይ ሁኔታ እያሳየ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ፣ ያህልም በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እና በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ላይ እየፈጸመ ያለውን ህገ-ወጥ ተግባር ማንሳት ይቻላል፡፡ ሁለቱ ፓርቲዎች በምርጫው ላይ ለመፎካከር የተዘጋጁ ቢሆንም በምርጫ ቦርድ ያልተገባ ድርጊት እየተገፉ ይገኛሉ፡፡

በተለይም አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) በምርጫ 2007 ለመወዳደር ያለውን ዝግጁነት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በምርጫው ለመሳተፍ እንደሚፈልግ ገና ከጠዋቱ በይፋ ያሳወቀ ፓርቲ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በምርጫ ቦርድ በኩል የተያዘው አቋም ፓርቲውን ዘግቶ ራሱ ቦርዱ ላደራጃቸው ተለጣፊ ኃይሎች ለመስጠት እየተዘጋጀ ነው፡፡

የአንድነት አባላት ለዓመታት ዋጋ እየከፈሉ ያቆዩትን ፓርቲ ምርጫ ቦርድ ድንገት ተነስቶ በአንድ ጀምበር ቢዘጋው ወይም ለሌሎች አሳልፎ ቢሰጠው፣ ፓርቲያቸውን በግፍ የሚነጠቁት አባላት ድርጊቱን በዝምታ ያዩታል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ ‹‹ምን ሊፈጥሩ ይችላሉ?›› የሚለውን ጥያቄ ለመገመት፣ የንብ መንጋ ቀፎው ሲሰበርበት የሚሆነውን ነገር ማሰብ ብቻ በቂ ነው፡፡

ይህ የምርጫ ቦርድ ተግባር በምርጫው ዴሞክራሲዊነት እና ፍትሃዊነት ላይ ጥያቄ የሚያስነሳ ብቻ ሳይሆን የምርጫውን ሂደት ሰላማዊነትም የሚያውክ አውዳሚ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሕግ የተሰጠውን አደራ ያለ ምንም አድልዎ መስራት ቢያቅተው እንኳ ከእንዲህ አይነቱ አጥፊ ተግባር መታቀብ ይኖርበታል እንላለን፡፡

**ነፃነትን፣ፍትህንና እኩልነትን እናውጃለን!**

**የሚሊዮኖች ድምፅ ጋዜጣ ታህሳስ 2007 ዓ.ም ተመሰረተች፡፡**

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ስለሺ ሐጎስ
አድራሻ፡-
አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 8
የቤት ቁ.257
ስልክ ፡- 01 11249659

**ምክትል ዋና አዘጋጅ**
ኤልያስ ገብሩ
0912064882

**አምደኞች፡-**
በሪሁን አዳነ
መስከረም ያረጋል
ፊራኦል ባጫ

**ሪፖርተሮች**
ሀብታሙ ምናለ
ንዋይ ገበየሁ
አሸናፊ አሳመረው
ምስክር አወል

**ዲዛይን እና ሌይአውት**
አብነት ረጋሳ
0913366064

**የህትመት ክፍል ኃላፊ**
ወንድወሰን ክንፈ

**ማሽን ኦፕሬተር**
ነብዩ መኮንን

አሳታሚ፡-አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
አድራሻ፡-አራዳ ክ/ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁ. አዲስ
አታሚ፡- አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)

የዝግጅት ክፍሉ ስልክ፡-01 11249659
ፖ.ሳ. ቁ. 4222

Email:-udjparty@gmail.com
andinet@ andinet.org
ፋክስ ቁጥር ፡-+251-111226288

# የጾታዊ ጥቃት ታላቅ ወንድም - ሰብዓዊነት



**አብርሃም ፍቃዱ**

በ1948 ዓ.ም ኢትዮጵያም በተቀበለችው የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ድንጋጌ ውስጥ በአንቀጽ ሶስት ሥር “Everyone has the right to life, liberty and security of person” የሚለው ይገኝበታል፡፡ በዚህ ጽሑፌ፣ በመኖር መብት ውስጥ በጉልህ ያልተዘረዘሩ ሆኖም ከእኛ አንጻር ልንመለከታቸው የፈለኳቸውን ጥቃቅን የሚመስሉ ጉዳዮችን ላስቃኛችሁ፡፡

ጉዳዩ የተፈጸመው ከሶስት ዓመታት በፊት ነበር፡፡ በአንድ ጠባብ ኮሮኮንቻም ቅያስ ውስጥ ህጻናት ኳስ ይጫወታሉ፡፡ በጨዋታው መሐል አንድ ልጅ ወድቆ ይሞታል፡፡ መቼም ‹‹የመጀመሪያዎቹ ተጠያቂዎች አብረውት ይጫወቱ የነበሩት ጓደኞቹ ናቸው›› እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽኑ ካጸደቃቸው ሌሎች ህጎች መካከል ለህጻናት ልዩ ጥበቃ እንዲደረግላቸውም ያውጃል፡፡ በመሆኑም የተመቸ ሜዳ ማዘጋጀት ያለበት አካል ማዘጋጀት ባለመቻሉ ምክንያት ተናግረው መብታቸውን ማስከበር የማይችሉትን ህጻናት ሰብዓዊ መብት ገፍፏል፡፡

ክፍት ቦታን በተመለከተ፣ አራት-በአራት (ሳጥን መሰል) ሕንጻ ካልተገነባ የሚበርደው አካል አለ፡፡ ልጆች ደስታቸውን ከሚሸምቱበት ሜዳ ላይ ሲነጥላቸው፣ ለሕጻናት ጥበቃ የቆመው አካል ሲከላከልላቸው አይታይም፤ ወይንም የጾታዊ ጥቃት ታላቅ ወንድም የሆነውን ሰብዓዊነት መሆኑን አልተረዳም፡፡



እንዲሁም በመገንባት ላይ ባሉት እና በተገነቡት የመኖሪያ መንደሮች ንድፍ ላይም በአብዛኞች ህጻናት ሊጫወቱበት የሚችሉባቸውን ቦታዎች ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመቦረቂያ ዕድሜያቸው ላይ የቁም እስረኛ ሆነው የመኖር መብታቸው አደጋ ውስጥ ወድቋል፡፡

ወደሁለተኛው ጉዳይ ልለፍ፡- በከተሞቻችን ውስጥ የትራፊክ አደጋ በየዓመቱ እጅግ እየጨመረ ይገኛል፡፡ ጉዳዩ ከሚያሳስባቸው መካከል እግረኞች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ፡፡ የባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ትኩረት የሚሠጠው ስለዋናው የመኪና መንገድ እንጂ እግረኞች ስለሚሄዱበት መንገድ (Pedestrian) ማስተዋልን የሚያውቅበት አይመስልም፡፡ያሉትም መንገዶች በውሃ እና ፍሳሽ ባለሥልጣን እና በኢትዮ-ቴሌኮም መስሪያ ቤቶች በመቆፋፈራቸው ምክንያት ለመሄድ ምቹ አይደሉም፡፡

አብዛኞቻችሁ ከምኒሊክ ሐውልት ፊት-ለፊት ያለውን የቁልቁለት መንገድ እንደምታውቁት እገምታለሁ፡፡ ይሄ ፍጹም ጠባብ ከሆኑ መንገዶች መካከል የሚመደብ ነው፡፡ የእግረኛ መንገድ የለውም፤ ወደሁለት አቅጣጫ የሚሄዱ መኪኖች ከላይም ከታችም ይመላለሱበታል፡፡በተጨማሪ እግረኞችንና የመንገድ ላይ ሱቆችን ያስተናግዳል፡፡በከተማችን ይንን የመሰለ (የጠቀስኩትን) እግረኞችን ለአደጋ የሚያጋልጡ መንገዶችን ማስተዋል ትችላላችሁ፡፡

እግረኞች ለሚመላለሱበት መንገድ ትኩረት ከተነፈጋቸው፣ የመኖር መብታቸው ወይንም ሰብዓዊ ክብራቸው አልተጣሰም ትላላችሁ?! በሌላ መልኩ ታክሲዎች በተደጋጋሚ እያቆራረጡ በመጫን አስቸግረዋችሁ ይሆናል፡፡ እንግዲያውም፣ ከህዝብ በተሰበሰበ ግብር የሚተዳደረው የመንግሥት ባለሥልጣን መስሪያ ቤት፣ ሥራውን በአግባቡ ባለማከናወኑ ምክንያት እና ቸልተኛ በመሆኑ ሳቢያ የመኖር መብት ላይ እንግልት እንዲፈጠር በማድረግ የተሳፋሪዎችን ሰብዓዊ መብት አልሸረሸረም ማለት ይቻላል?

የመጀመሪያ ዓመት ተመራቂ ናችሁ? ዘንድሮ ልትመረቁ እየተዘጋጃችሁ ነው? እንግዲያው፣ በአብዛኞቹ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች እና በሌሎችም ድርጅቶች ተፈላጊ አይደላችሁማ! ምክንያቱም ልምድ የላችሁም፡፡ አስራ ምናምን ዓመታት ተምራችሁ የተመረቃችሁበት ትምህርት ብቁ እንዳልሆናችሁና ዋጋ ቢስ እንደነበረ እስከ አስር ዓመት የሚደርስ የሥራ ልምድ በመደርደር፣ በተጨማሪም የትምህርት ፖሊሲውንም ቁመት በመጠራጠር ትልልቅ የምንላቸው የፌደራል መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ለማስታወቂያ በተጉ ጋዜጦች ላይ በገደምዳሜ እየተናገሩ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ሁኔታ በታዳጊ ሀገር ስም ተምሮና ሥራ ሰርቶ የመኖር መብት ዓይን አልተጎለጎለም ማለት ይቻላል?!

በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰብዓዊ መብትን የምንመለከትበት መስታወት እየደበዘዘ ይመስለኛል፡፡ ሁላችንም ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ መስታወቱ ውስጥ የምንመለከታቸው መብቶች ከመጻፍ፣ ከመናገርና ሰላማዊ ሰልፍ ከመውጣት በስተቀር ከላይ የተነሱትና ሌሎችም ጉዳዮች እየደበዘዙ ይገኛሉ፡፡ መስታወቶቻችን ሁሉንም መብቶች ማየት እንዲቻላቸው በደንብ ወልውለን እና አስተካክለን መቆየት ብንችል የተሻለች ሰብዓዊ መብት (የመኖር መብት) የሚከበርባት ኢትዮጵያ ብቅ እንደምትል ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

# ሜሮናዊነትና አስቴራዊነት

**“በመብት ማስከበር ጉዳይ ከሲኒማ ቤቶች ጋር የምትገባቸው ሙግቶች፣እራሷን በትምህርት እና በስልጠና ለማሳደግ የምታደርጋቸው ጥረቶች ከሁሉም ከሁሉም የህዝብን እንባ በድርጎሽ ለመቀየር ካልመረጡ አርቲስቶች መካከል አንዷ በመሆኗ ትመሰገናለች**



**ፊራኦል ባጫ**

ለረሃብተኛ ዳቦ ብርቁ ነው ሆነና ነገሩ በርባና ቢስነት ተመች ከተመታው የአርቲስቶች ማሳ ውስጥ ሁለት ጽንፍና ጽንፍ ላይ የቆሙ ሴቶችን አስተዋልን፡፡ ሁለቱም የሰሞነኛ መነጋገሪያ እና መነታረኪያ ለመሆን የበቁት አንደኛዋ መንግስትን የሚተች ግጥም አነበበች ሌላኛዋ ደግሞ የመንግስት ባለሥልጣናትን በዝምታ ያቆየ ጥያቄ ጠየቀች በሚል ነው፡፡

በማኅበር ከመከነው የአርቲስቶች ስብስብ ውስጥ እነኝህን ማግኘት ተስፋ ቢመስልም ከመጠየቅና ከመግጠም አልፈው እራሳቸውን ለእውነት የሰጡ ኢትዮጵያውያንን ውለታ በእነዚህ አይነ ገብ አርቲስቶች ሰሞነኛ መድፈር ማጠፋት ግን ተገቢ አይደለም፡፡ ቢሆንም ቢሆንም ሳይሞት ከተገነዘው ሰፈር ሁለት ተንፋሽ በማግኘታችን ደስታችንን አንደብቅም፡፡

በዚሁ ግርግር ውስጥ ግን ሜሮን ጌትነት እና አስቴር በዳኔ አንድ ዓላማና ግለ መዝገባቸው ከአንድ የተቀዳ ማስመሰል የተሳሳተ ነው፡፡ አስቴር ጥያቄውን ያቀረበችበትና ሜሮን ግጥሙን ያነበበችበት መነሾ ለየቅል ነው፡፡ ሁለቱ በየፊናቸው ሲያሳዩት ከነበረው ነገር ተነስተን ጉዳዩን ብናየው ደግሞ አንደኛዋ የአጋጣሚ አነፍናፊነት (opportunist) አንደኛዋ ደግሞ ውስጠቷን በቅንነት ያስነበበች (openhearted) ሆና እናገኛቸዋለን፡፡

****

ባለፈው ጥቂት ዓመታት ውስጥ በቴሌቪዥንና በራዲዮን እጅጉን በመብዛት (over exposed) በመሆን ሜሮን ጌትነትን የበለጠ ሰው የለም፡፡ ከአመታት በፊት ጃፓን ደርሶ በመጣ ባለራዕይ ወጣትነትና በገጣሚነት የምናውቃት ሜሮን በተዋናይነት ፊቷን ካስመታች በኋላ የገንዘብ ካዝና የሆነውና ብዙ ወጣት ሊደፍረው የማይፈለገውን የመንግሥት ቤት ደጅ መጥናት ጀመረች፡፡

አብዝታ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ህንጻ የማትጠፋው ሜሮን በመንግስት የሚዘጋጁና በሚሊየን ብሮች የሚጠጋ በጀት ያላቸውን መድረኮች አነፍንፎ በመጠጋት ተወዳዳሪ አልነበራትም፡፡እናት ለምን ትሙት የተሰኘውን የጤና ጥበቃ ፌስቲቫል ጀምረን፣የብሄር ብሄረሰቦች ቀን፣የባንዲራ ሳምንት፣የመከላከያ ሰራዊት ፕሮጀክቶችን ብንጠቅስ ሜሮን ጌትነትን የማናይበት መድረክ አልነበረም፡፡

ሜሮን መድረክ ስትመራ የኪነጥበብ ጣዕም ከመስጠት ይልቅ የመንግስት ባለሥልጣናትን ምኞት ለማሳካት ትተጋ ነበር፡፡ የጥያቄና መልስን የመሰሉ ዝግጅቶችን ስትመራ ደግሞ ከአድር ባይነት የሚገዝፍ ትወና ታሳያለች፡፡ የመከላከያ ሰራዊት ስፖንሰር ዝግጅት ጊዜ የሰራዊቱን መዝሙር ሰማሁ ብላ የሳየችው መነፋረቅ ሰለሞን ተካ አርበኞች ግንባር ታጋዮች መካካል ሆኖ ከተንሰቀሰቀው ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ለአለፉት አራት ዓመታት ሜሮን ጌትነት የወጣቶች የሞራል መላሸቅ ምልክት ነበረች፡፡ካሰበችው ባላይ ገንዘብ ማግኘት ብትችልም ሜሮንን በተምሳሌትነት የሚጠራ አልነበረም፡፡በዳና ድራማ ላይ ስትታይ እንኳ ‹ይቺ ልጅ..ትን ልትለን ነው፡፡›› ሲሉ በጆሮዬ የሰማኃቸው ወገኖች ነበሩ፡፡

ሰኔ 5/2005 የገጣሚያንና ደራሲያን ደሴት የሆነው ጦቢያ ግጥምን በጃዝ ላይ ከመንፈቅ በፊት ባለፈው ሰሞን አቧራ ስላነሳው ግጥም ተነበበ፡፡ በዚያ የነበረው ታዳሚ የግጥሙ አንዳንድ የቀለም ችግሮቹና ግር የሚሉ ፍልስፍናዎቹን እያረመመ ቢሆን አጣጣመ፡፡ በዚያ ቀን ከተሰማው የበረከት በላይነህ ፣የመንግስቱ ዘገየ እና ዮሃንስ ኃ/ማሪያም ግጥም የተለየ አይን አልተሰጠውም፡፡ ሜሮን ልታነሳ የፈለገችው ሀሳብ ማራኪ ሆኖ ሳለ በዚያው ሳምንት ትሰራቸው ከነበሩት መንግስት ደገፍ እንቅስቃሴዎች አንጻር እኔን ጨምሮ ህዝቡ በሌባ አፍ ስለ ታማኝነት መስማት የሆነበት ይመስል ከትህትና ጭብጨባ በቀር ወደ ቤቱ ይዞት የሄደው ግርምት አልነበረም፡፡

ከዚህ ግጥም መነበብ በኃላ ሜሮን ግጥሙን የጻፈችው ከልብ በመነጨ ቁጭት ሳይሆን የራስ ሆቴልን ከባድ ታዳሚ ውገዘት ላለመስማት እንደነበር የሚያሳይ ነገር ተፈጠረ፡፡ ሜሮን በመከላከያ ሰራዊት ስፖንሰር ከተደረገው የጥያቄ ውድድር ዝግጅት ጀምራ በተለመደው የብልጣብልጥ ረገጣዋ ቀጠለችበት፡፡

ከስደስት ወር በኃላ ግን ይሄ ግጥም በማህበራዊ ድህረ ገጽ ተለቀቀ፡፡ ያልታሰበ መነጋገሪያ ሆነ፡፡ በማንና በምን ሁኔታ ላይ እንደተጻፈ ፣የሃገር ቤቱን ሰው ይሁን ዲያስፖራውን ማብጠልጠሉ ባልታወቀበት ሁኔታ ከሳምንት በፊት ትኮሰኩሰን የነበረችውን ልጅ ልንለብሳት ተጣደፍን፡፡ ሜሮንም የአሜሪካ ጉዞዋ እንደሸዋፈራሁ ደሳለኝ ውግዘት እንዳይበዛበት መንገዱን ጨርቅ ማድረጊያ ፈለገች፡፡ ግጥሙ ላስነሳው ስሜት ምላሽ ባለመስጠት አንድም ከአምባገነኖች እግር ስር ሌላ ጊዜ ደግሞ ከፍትህ ናፋቂ እግር ስር እንደማትታጣ አሳየች፡፡

ለሜሮን የተሰጠው ሙገሳና የክብር ስም ተገቢ አይደለም፡፡መንግስቱ ኃ/ማሪያም ስለፍቅር ቢዘፈን እንደማሞገስ ነው -ለሰራው እንኳ ይቅርታ ሳይጠይቅ፡፡ ልናስበው የሚገባው ነገር ሜሮን ይሄን ግጥም እንዴት ጻፈች ሳይሆን ምን የተሻለ ነገር እያውጠነጠነች ይሆን የሚል ነው፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከምትማረው ልማታዊ የትምህርት ዘርፍ አንጻር አያጣረስባትም ወይ? ወይንስ ከዩኒቲ ተማሪነቷ ጀምሮ የሄደችባቸው ብልጣብልጥ የህይወት መንገዶች አንዱ ክፍል ነው? መልስ ያሻዋል፡፡

ለማንኛውም ግን የሜሮን ሰሞነኛ ሁኔታ ስልታዊ ማፈግፈግ እንጂ ወደ ህዝባዊነት ሰፈር መምጣት አይደለም፡፡ሜሮናዊነት የጥሪ ካርዱን ግዘፈት አይቶ አለባበስን እና ማንነትን ለሸወዳ እንደማስተካከል ነው እላለሁ…ባያዘልቅም፡፡

****

አስቴር በዳኔ ፍልሚያ ወዳድ ናት፡፡ ለአይናችን ከቀረበችበት ‹ጎጆ መውጫ› ድራማ ጀምሮ አስቴር ራሷን ለማሳደግ የምትለፋ ሴት ነበረች፡፡የአስቴር ችግር ብዙ ነገሮችን በእልህ ለማሳካት በመጣሯ የሚከሰቱ የኪነጥበብ ስራዎቿ ሀቅም አንዴ ላይ አንዴ ታች ማለቱ ነው፡፡ የተወሰኑ መቶ ሺ ብሮች የተሸለመችበት የቅዱስ ያሬድ ፊልም ፕሮጀክት የኔ ነው የሚል ሰው ስሞታን የሆነ ጥግ ላይ መስማታችንን ሳንደብቅ እንቆቅልሽን በመሰለ ፊልሟ ውስጥ የሚታዩ የኪነጥበብ እንከኖች አስቴር የበለጠ መስራት እንዳለባት ያስመክረናል፡፡

በመብት ማስከበር ጉዳይ ከሲኒማ ቤቶች ጋር የምትገባቸው ሙግቶች፣እራሷን በትምህርት እና በስልጠና ለማሳደግ የምታደርጋቸው ጥረቶች ከሁሉም ከሁሉም የህዝብን እንባ በድርጎሽ ለመቀየር ካልመረጡ አርቲስቶች መካከል አንዷ በመሆኗ ትመሰገናለች፡፡

አስቴር የቅርብ ጊዜ ርጋታዋና ሁኔታዋ ደግሞ በእድሜ ውስጥ የበሰለች መሆኗን ያሳያል፡፡በተለይ ለህጻናት የሚሆኑ መጽሃፍትን በማዘጋጀት የማቅረቧ ጥረት ልጂቱ ከግላዊ ዝና ይልቅ ማህበረሰባዊ መሰረት ያለው ጉዞ መምረጧን ያሳያል፡፡

የአስቴር ሰሞነኛ ጉዳይና የተከተለው ሁሉ ነገር የብስለቷና የማመዛዘኗ ጫፍ ይመስላል፡፡በደደቢቱ ጉብኝት ጊዜ አርቲስት ሁሉ ፊቱን አስመትቶ የገኘ'ውን ፓርቲ የኃላ ላይ ፍርፋሪ ለመልቀም የተዘጋጀ ይመስል ነበር፡፡አንዳንዱ ባለሥልጣን በጨፈረበት ሁሉ እየዘለለ በመግባትና በመውረገረግ ወዳጅነቱን ሲያይ ሌሎቹ ከአንድ ባለጊዜ አንገት ላይ በመሸጎጥ ፍቅር አስጨነቀኝ አይነት ጨዋታ ተውነዋል፡፡

ህወሃት እሰቲ ትንሽ ዘና ልበል ብሎ ባዘጋጃቸው መድረኮች ላይ እየተነሱ ‹የናንተ ነገርማ የቱ ተጀምሮ የቱ ያልቃል…ሰላም ላለ 50 ብር ነው፡፡ አስፍቶ ለጠየቀ እስከ 200 ብር ነው› አይነት ከልብ ያልሆነ ሙገሳ ይከታተል ነበረ፡፡ብዙው እያንጎላጀም ቢሆን ከህዝብ ዕልቂት መማር ያለብንን እንደ መመዘዝ ወንድምን መግደል በጀግነት የሚሰብኩትን ባለስልጣናት ከመስማት በቀር የረባ ጥያቄ ሊጠይቅ አልደፈረም፡፡

በዚህ መሃል ነው እንግዲህ አስቴር በዳኔ ከከፈነው አዳራሽ ውስጥ ይያው ጥያቄዎችን ለባለስልጣናቱ ያከታተለችው፡፡

‹‹ዛሬ ባልናገረው የሚቆጨኝ የተከፈለው መስዋዕትነት እጅግ በጣም ከባድ እንደነበር ግልጽ ነው፡፡ በጆሮ ስሰማው ደርግ ተደምስሶ ታጋይ እንዲህ ሆኖ ሲባል ከሁለቱም ወገን የተሰዉት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ልጆች ናቸው፡፡ የሞቱት፣ እግራቸው የተቆረጠ፣ ዓይናቸው የጠፋ ስላሉ ለሁለቱም ‹ጠላት› የሚለው ቃል ተገቢ አይመስለኝም፡፡ የወንድማማቾች ደም በመፍሰሱ ቤተሰቦቻቸው ዘንድ ሄደን ስናይ ልብ የሚሰብር ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የጦርነትና የትግል ታሪክ ዘመኑ የፈጠረው ነው፡፡ በወቅቱ መንግሥታዊ ለውጥ ለማምጣት የትጥቅ ትግሉ አማራጭ አልነበረውም፡፡ አሁንስ?››

‹‹የትግሉ ዋና ሐሳብ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገሪቱ ለማምጣት ነው፡፡ የመንግሥትም ሆነ የሥርዓት ለውጥ በጦርነት ሳይሆን በዲሞክራሲ እንዲሆን ነበር ያ ሁሉ ከባድ መስዋዕትነት የተከፈለው፡፡ አሁን ላይ ሲታሰብ የሚመጣው ግንቦት ላይ 24 ዓመት የሚሆነው ሥልጣን ላይ ያለው አንድ ፓርቲ ነው፡፡ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ላይ ልባችሁ ምን ይላል? ያኔ ለሥልጣን ሳይሆን ለሕዝብ ስትታገሉ በጦርነት ሳይሆን በዲሞክራሲ ለውጥ እንዲደረግ ነበር፡፡ አይለደም?››

‹‹በእርግጥ የድሮን አስተሳሰብ መናፈቅ አዲስ አስተሳሰብ ለመቀበል ይከብዳል፡፡ አሁን ዝም ብዬ ሳስበው ራሱ ተቃዋሚ የሚለው ቃል ራሱ ጥሩ አይደለም፡፡ ተፎካካሪ ቢባል፡፡ አዲስ አስተሳሰብና ፍልስፍና ያለው ተተኪ መሪ ሊፈጠር አይችልም የሚል አቋም ነው ያላችሁ?››

‹‹እውነት መናገር እወዳለሁ … ምክንያቱም እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፡፡ ‘So, next time’ ምን ያህል አዲስ ታሪክ አዲስ አስተሳሰብ በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተለውጦ እናያለን?....እናንተስ በምርጫ ትወርዱ ይሆን?››

አስቴር ይሄን ጥያቄ መጠየቋ ከቦታውና ዙሪያዋን ከከበቧት ሰዎች አንጻር የሚገርም ነው፡፡ ነውር ግን አልነበረም፡፡ የተናገረችውን እንድትሰጋበት የሚፈልጉት ዳዊት ከበደና ወዳጆቹ ይሄን መናገርም ድፍረት መስሏቸው ‹በቆርጦ ቀጥል ቴክኖሎጂ› ሊያፍረከርኳትሞከሩ፡፡

ፍንክች ያባ ቢለዋ ልጅ አስቴር የተናገረችው አምናበት መሆኑን ከማስረገጥ አልፋ ለተቃዋሚም ሆነ ለመንግሥት ሰዎች የሚበጅ ያለችውን የዜግነት ድምፆን ደገመችው፡፡

አስቴር በቅርቡ ከኢሳቱ ተቦርነ በየነ ጋር ቆይታ ነበራት ፡፡ ጉዳይዋ ለኢትዮጵያና ለኢትዮያዊነት የሚበጀውን ከመናገር ፈቀቅ እንዳማይል አሳይተዋለች፡፡ ጉዳዩን ለበለጠ ዝና ከመጠቀም ይልቅ የተናገረችው ከፍጹም ተቆርቋሪነት እና ቅንነት እንደሆነ አስምራለች፡፡

እንግዲህ አስቴርና ሜሮን ልዩነታቸው ይሄ ነው ….ሜሮን በባለሥልጣናት ፊት ልማታዊ አንባገነነትን ታቀነቅናለች፣በህዝብ መድረክ ላይ ህዝባዊ ቁጭትን ትዘፍናለች፡፡አስቴር ግን በባለስልጣናት ፊት የህዝብን ጥያቄ አስተጋባች ፣ በህዝብ ፊት ደግሞ የሃገር አሳቢነቷን አስረግጣ ቀረች፡፡ ቃሏ ፔንዱለም ሳይሆን የዕምነት ምሰሶ መሆኑን አረጋገጠች፡፡

አስቴራዊነት በሁላችንም ላይ ያብብ አቦ…

# ሀገር የመምራት ብቃት ያለው ማነው?



ኤልያስ ገብሩ

**"ግን ሥልጣን ላይ ወጥተው ሳናያቸው ገና ‹‹ተቃዋሚዎች ብቁ አይደሉም›› ብሎ በጅምላ መግለጽ በግሌ የማላምንበት ጉዳይ ነው:: ሕዝብ መርጧቸው ሥልጣን ይያዙና ያኔ በተግባር እንያቸው! እንገምግማቸው! ተፈትነው ይታዩ::**

ከገዥው መንግሥት ሹማምንቶች ጀምሮ በኅብረተሰቡ ውስጥ፣ በራሳቸው በተቃዋሚዎችና በተወሰኑ የሚዲያ ባለሙያዎች ዘንድ አልፎ አልፎ የሚደመጡ አስተሳሰቦች አሉ:: እነዚህም ‹‹ተቃዋሚዎች ሀገር የመምራት ብቃት የላቸውም፣/አይረቡም/፣‹‹ተስፋ የሚጣልባቸው አይደሉም›› ወዘተ. የሚሉ ናቸው::

በብዙ ነገሮች የታነቀውን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ሕገ-መንግሥታዊ መብትን ለአፍታ ተወት ላድርገው:: ሰዎች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሯዊ መብት አላቸውና ከላይ የጠቀስኳቸውን አገላለጾች ሰዎች መናገር ይችላሉ:: ነገር ግን፣ አንድን ነገር ስንናገር ወይም አቃልለን ስንገልጽ ግራና ቀኙን፣ ፊትና ኋላውን፣ ውስጥና ውጪውን በደንብ አገናዝበን ቢሆን አሳማኝነቱ ከፍተኛ ይሆናል::

የኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ እንቅስቃሴ በብዙ ውጣ-ውረዶች ውስጥ አልፎ ዛሬ ላይ ደርሷል:: አሁንም ቢሆን በብዙ መከራዎች መታነቁን በገሃድ የምናየው ሀቅ ነው::

በሀገራችን ከገዥው መንግሥት የተለየ የፖለቲካ አተያይ እና መንገድ ያላቸው ተቃዋሚም ሆኑ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊኖሩ የግድ ነው:: እነዚህ ፓርቲዎችም በራሳቸው በርካታ ችግሮች፣ ድክመቶች፣ እንከኖች፣ ወዘተ. አላቸው፣ ይኖራቸዋልም:: ጥቂት በማይባሉ ውስጣዊ ችግሮችም ተተብትበው የመዳከር ዕጣ ፈንታም ይገጥማቸዋል:: ከገዥው ፓርቲ የሚመጣውም ውጫዊ የማዳከም ክፉ እና አሳዛኝ ሥትራቴጂያዊ ሴራዎችም ሊዘነጉ አይገባም::

በግሌ፣ ለእውነተኛ ለውጥ የቆሙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ በራሳቸውም ሆነ ከእነሱ ውጪ ባሉ ችግሮች ምክንያት በብዙ ውጣ-ውረዶች፣ ዋጋ መክፈሎችና መከራዎች ውስጥ አልፈው ዛሬም ድረስ ለሰላማዊ ትግል መቆማቸው በቀላሉ መታየት ያለበት ጉዳይ አድርጌ አልቆጥረውም::

ችግሮች እና ስህተቶች ሲኖሩ ማረሙ፣ ማስተካከሉና ተገቢውን ነገር መምከሩ ወሳኝነቱ አሳማኝ ነው:: ይህንን ለማድረግ፣ ችግር አለባቸው ወደተባለባቸው ቦታዎች እና አካላት ቀረብ ብሎ ማየት እና መመልከትም ጉብዝና መሆኑ አያጠያይቅም::ነገር ግን፣ እንዲሁ የዳር ተመልካች ሆኖ፤ እንደአንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፣ ለለውጥ እንቅስቃሴ በተለያየ መንገድ ለመርዳት እና ለመደገፍ አንዲትም ጠጠር ሳያቀብሉ፤ ለእውነተኛ ለውጥ በሚንቀሳቀሱ አካላት ላይ ትችትን፣ ነቀፌታንና ጥላቻችን ማዝነብ፣ እንዲሁም አፍራሽ ተልዕኮን አንግቦ መንቀሳቀስ የሎሌነትና የደካማነት አንዱ ምልክት አድርጎ መውሰድ ይቻላል::

በሰላማዊ ትግል መርህ ላይ ቆመው፣ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ለውጥ ለማምጣት፣ ነጻነትን ለማጎናጸፍ፣ ፍትህን ለማስፈን ወዘተ. ከልባቸው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንዲሁ ‹‹አለን›› ለማለት ብቻ ከተቀመጡት ጋር በጥቅል ደርቦ፣ በስመ ተቃዋሚ ብቻ ‹‹ሀገር የመምራት ብቃት የላቸውም›› የሚል ታፔላ መስጠት ተገቢ ነው ብዬ አላምንም:: በውስጣዊ እና በውጫዊ ችግሮች ተወጥረው በመታገል ውስጥ በርካታ አቅምን የሚጎትቱ እና ተስፋ የሚያስቆርጡ ሁነቶች ሊስተናገዱ እንደሚችሉ ዕሙን ነው::

ብዙ መውጣት መውረዱ፣ መንገላታት መተከዙ፣ ተስፋ ቆርጠው በዕምነት ዳግም መነሳቱ፣ በጠበበው በር በጭላንጭል ማየቱ፣ ለኢ-ሕገ መንግሥታዊ መንግሥታዊ ምላሽ ‹‹ሕገ-መንግስቱ ይከበር!›› ብሎ ዘወትር መቆሙ፣ ኢ-ፍትሃዊ እስር፣ ስቃይ፣ ፍርድንና መስዋዕትነትን በየጊዜው ማስተናገዱ፣ የእውነተኛ ተቃዋሚዎች ዕጣ ፈንታ መሆኑን እንደአንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ እታዘባለሁ::

ከልባቸው፣ ለእውነተኛ የሰላማዊ ትግል መርህ የቆሙ ተቃዋሚዎችን ትናንትም ሆነ ዛሬ በበርካታ ውስጣዊ እና በክፉ ሴራ በታጀለ የውጫዊ ችግሮቻቸውን ነጸብራቅ በማየት ‹‹ሀገር የመምራት ብቃት የላቸውም›› የሚል ፍረጃን ማከናነብ አሳማኝ አይሆንም:: [ለእውነት የሰላማዊ ትግል መርህ የቆሙ ተቃዋሚዎች ውስጥ ለጥቂቷ ሥልጣናቸው የሚጨነቁ፣ አርቀው የማያልሙ፣ ከትግሉ ይልቅ ለዕውቅና የሚታትሩ፣ ለጥቅም ያደሩ እንደማይጠፉም አምናለሁ::]

እውነተኞቹ ሕዝብ ከመረጣቸው በመጀመሪያ መንግሥት ይሁኑ:: ከዚም መንግሥታዊ መዋቅሮችን ዘርግተው ትናንት ከትናንት በስቲያ …ለዓመታት ሲናገሩ የነበረውን በተግባር ያሳዩን:: ሥልጣን ከመጨበጣቸው በፊት ከሚናገሩት በተቃራኒው ተሰልፈው ከተገኙ ደግሞ ያው ሕዝብ እንዳወጣቸው ሕዝብ ሊያወርዳቸው ይችላል የዴሞክራሲያዊነት አንዱ እውነታ ይሄ ነውና::

እኛም ጋዜጠኞች ብንሆን፣ ያኔ ሀገርን እና ሕዝብን በሚጎዱ ተግባሮቶች ላይ መንቀሳቀስ መጀመራቸውን እያየን ዝም አንልም! ዛሬ የኢሕአዴግ ሥርዓት በምክንያታዊነት እንደሚተቸውና እንደሚብጠለጠለው ሁሉ እነሱም ከዚህ አያመልጡም! ሥልጣን በጨበጡ ማግሥት በያዙት ሥልጣን ሕዝብን ማገልገል እንጂ ራሳቸውንና ጥቂቶችን ያለመጥቀም መቆም እንደሌለባቸው እና ለእንዳንዱ የሥልጣናቸው ኃላፊነት ተጠያቂ መሆናቸውን በአንክሮ እናስገነዝባቸዋለን! ያኔ መላቀቅ የለም! ለምን? የኢትዮጵያ እና የህዝቦቿ መከራ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቆም ስላለበት:: መንግሥታዊ የሥልጣን ብልግናንና አምባገነንነትን ከእንጭጩ መቀጨት ስለሚኖርባቸው! ዴሞክራሲ ሕይወት ዘርቶ በነጻነት ሲንቀሳቀስ መታየት ስለሚገባው! ፍትህ በችሎት አደባባይ ተገልጣ መሰጠት ስለሚኖርባት! …ብዙ ነገሮችን መዘርዘር ይቻላል!

ግን ሥልጣን ላይ ወጥተው ሳናያቸው ገና ‹‹ተቃዋሚዎች ብቁ አይደሉም›› ብሎ በጅምላ መግለጽ በግሌ የማላምንበት ጉዳይ ነው:: ሕዝብ መርጧቸው ሥልጣን ይያዙና ያኔ በተግባር እንያቸው! እንገምግማቸው! ተፈትነው ይታዩ::

የተቃዋሚዎችን በዚህ ገታ ላድርገውና ወደገዥው ሥርዓት ሀገር የመምራት ብቃት አለው ወይስ የለውም ወደሚለው ግላዊ አስተያየቴ ላምራ::

እንደሚታወቀው ሕወኃት/ኢሕአዴግ ከጫካ ተነስቶ በመራራ ትግል ሥልጣን ከጨበጠ 23+ ዓመታት ሆኖታል::ተቃዋሚዎችን ሥልጣን ሳይዙ ገና ‹‹ሀገር የመምራት ብቃት የላቸውም›› ብሎ መግለጹ ‹‹ተገቢ አይደለም፤ በግሌ አላምንበትም›› እንዳልኩት ሁሉ፤ ለ17 ዓመታት ትጥቅ ትግል ላይ የነበሩትን ‹‹ነጻ አውጪዎች›› በትግላቸው ወቅት ‹‹ሀገር ለመምራት ብቃት የላቸውም›› የሚል ታፔላ ሊሰጣቸው ይገባል አልልም- በተግባራዊው ሥልጣን ላይ መታየት ስለነበረባቸው:: ያኔ ‹‹ገንጣይ››፣ ‹‹አስገንጣይ››፣ ‹‹ወንበዴ››፣ ‹‹ህጻናት›› ወዘተ. ሲባሉም ነበር::

ነገር ግን፣ ገና ከትግል ጥንስሱ ጀምሮ ጥርት ያለ አቋም እና የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም እንዳልነበራቸው አመጣጣቸውን እና ታሪካቸውን ወደኋላ ተመልሶ ለማወቅ እና ለማጥናት ከልቡ የሞከረ ሰው በግልጽ ይረዳዋል::

ትግራይን ነጻ ከማውጣት ኢትዮጵያን ከደርግ አገዛዝ ነጻ ወደማውጣት ተሸጋግረው ነበር:: በትግሉ መባቻ የአልባኒያ ሶሻሊዝምን ይዞ ወደሥልጣኑ ጫፍ ላይ ደግሞ አብዮታዊ ዴሞክራሲን የሙጥኝ በማለት የርዕዮተ - ዓለማት መገለባበጥን ሲያስተናግድ ነበር::በመካከል ተይዘው የተለቀቁ የፖለቲካ አቅጣጫዎችም ነበሩ::

የኢሕአዴግ የሥልጣን አገዛዝ ከሽግግር መንግሥቱ ጀምሮ የተለያዩ ምዕራፎችን አስተናግዶ ዛሬ ላይ ደርሷል:: ‹‹ከሕጎች በላይ የሆነው›› በሚል በሥርዓቱ የሚሞካሸው ህገ-መንግሥቱ በረቂቁ ጊዜ ሕዝብ ተወያይቶበት መጽደቁ በዚያን ወቅት በአደባባይ ቢነገርም ሕገ-መንግሥቱ ላይ ፈርመው መጽደቁን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ያደረጉት የያኔው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ‹‹በሕገ-መንግሥቱ ረቂቅ ላይ ሕዝብ በደንብ ተወያቶበት ነው ያልኩት ስህተት ስለሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ በይፋ ይቅርታ እጠይቃለሁ›› ማለታቸው ሊዘነጋ አይገባም::

‹‹ከሕጎች በላይ የሆነው›› እና ‹‹ሕዝብ በበቂ ሁኔታ ሳይወያይበት›› እንደጸደቀ በያኔው ፕሬዚዳንት የተነገረለት ሕገ-መንግሥትን ራሱ መንግሥት ለፈለገው ዓላማ አንዳንዴ ሲንድና ሲሸራርፍ፣ ከሕጉ ጋር የሚጣረሱ አፋኝ አዋጆችንም ሲያወጣ ከርሞ … ‹‹ሀገሪቷን ከእኔ በላይ የሚመራ የለም››፤ ‹‹ለሚቀጥሉት 20 ዓመታትም እኔ ነኝ ለዚህች ሀገር የማስፈልጋት››፣ ‹‹እኔ ከሌለው ሀገሪቷ ትበታተናለች፤ የሱማሊያ እጣ ፋንታ ይገጥማታል›› ወዘተ በማለት በድፍረት ይናገራል::

የእኩልነት፣ የነጻነት፣ የፍትህ፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል፣ መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት፣ የሰብዓዊ መብት፣ የዴሞክራዊ …እጦቶች በሥርዓቱ ላይ ከሚነሱ የዘወትር ጥያቄዎች መካከል ዋነኞቹ ናቸው:: እነዚህና ሌሎች በዝርዝር ያልተጠቀሱ ዕጦቶችንና ችግሮችን በበቂ ሁኔታ ለዓመታት መፍታት ያልቻለ፣ ወይም የተሳነው መንግሥት በምን መለኪያ ሀገርን የማስተዳደር ብቃት አለኝ ሊል ይደፍራል? ለዓመታት ታይቶ፣ ተመክሮና ተፈትኖ ‹‹ከድጡ ወደማጡ›› የሆነውን መንግሥት ሀገር የመምራት ብቃት ዜጎች እንዴት አምነን እንቀበል? ሀገሪቷንና ሕዝቦቿን በትክክል ያላማከሉ የኩረጃ ዕቅዶች፣ ሥትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች፣ አቅጣጫዎች፣ ሙከራዎች ወዘተ. ሀገሪቷን እና ሕዝቦቿን ቤተ-ሙከራ ከማድረግ በዘለለ ምንስ ፈየዱ? የትኛውንስ አመርቂ ለውጥ አመጡ? በብዙሃን ዜጎች ላይስ በተግባር የሚታዩ የኢኮኖሚ ዕድገቶችን መቼ አጎናጸፉ? ስንቶቹን ከአስከፊ ስደት መታደግ ቻሉ? ሥልጣንን የሙጥኝ የማለት የመንግሥት ክፉ አባዜ፣ የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓቱን የቱ ጋር መሰረተ?

ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፣ ያሉ እና የሚታዩ ሀቆችን በራስህ አረዳድ ተገንዝበህ፣ በነጻነት አስበህና አሰላስለህና ግራና ቀኙን በአንክሮ መርምረህ ‹‹በትክክል ሊመራኝ የሚችለውና የሚገባው ይሄ ነው›› በል በድፍረት!

# <<ኃይለማርያም የአንድ ፋብሪካ ማናጀር ቢሆን ውጤታማ ይሆን ነበር>>

**አቶ ኤርሚያስ ለገሠ/ የቀድሞ የመንግሥት ጉዳዮች ኮሙኑኬሽን ሚኒስትር ደኤታ/**

ከኢህአዴግ ጋር ለአስር ዓመታት ያህል አብረው ተጉዘዋል፡፡ በመረጨረሻው የሥልጣን ዘመናቸው የመንግሥት ጉዳዮች ኮሙኑኬሽን ጽ/ቤት ሚኒስትር ዴኤታ በመሆን አግልገው ነበር፡፡ ከሥርዓቱ ጋር ያላቸው ግንኙነት ከተቋረጠ በኋላ በስደት አሜሪካን ሀገር መኖር ከመጀሩ ጥቂት ዓመታትን አስቆጥረዋል፤ አቶ ኤርሚያስ ለገሠ፡፡

ከተወሰኑ ወራቶች በፊት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ በጣም አነጋጋሪ የሆነውንና ‹‹የመለስ ትሩፋቶች›› የተሰኘውን መጽሐፍ አዘጋጅተው ለንባብ አብቅተዋል፡፡ የአራተኛው ዕትም የ‹‹ሚሊየኖች ድምጽ›› ጋዜጣችን ላይ የሚሊዮኖች እንግዳ ከሆኑት አቶ ኤርሚያስ ለገሰ ጋር ባልደረባችን ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ ቃለ-ምልልስ አድርጓል፡፡ የቃለ-ምልልሱን የመጀመሪያው ክፍል እነሆ፡-

**ካልተሳሳትኩ ከሀገር ከተሰደዱ በኋላ ለሀገር ውስጥ ሚዲያ ቃለ-ምልልስ ሲሰጡ የመጀመሪያዎ ይመስለኛል፡፡ ...ለቃለ-ምልልሱ ፈቃደኛ በመሆንዎ በቅድሚያ በ‹‹ሚሊየኖች ድምጽ›› ጋዜጣ ሥም ለማመስገን እወዳለሁ፡፡**

እኔም አመሰግናለሁ፡፡

**ከመንግሥት ባለሥልጣንነት በገዛ ፈቃድዎ ተነስተው በአሁኑ ወቅት በስደት አሜሪካን ሀገር ይገኛሉ፡፡ ከሀገር ተሰድዶ መኖርን እንዴት አገኙት? ናፍቆቱ ...**



እንደ እውነቱ ከሆነ ከሀገር ርቆ መኖር ጉዳትም ጥቅምም አለው፡፡ ጉዳቱ ከሀገር፣ ከጓደኛ፣ ከቤተዘመድ... በየጊዜው አለመገናኘት ስላለው ሁልጊዜም የጐደለህ ነገር እንዳለ ይሰማሃል፡፡ በተቃራኒው ከምትኖርበት ሀገር እና አህጉር አንጻር ቢለያይም ጥቅሞች አሉት፡፡ ለምሳሌ፣ እኔ የምኖርበት አሜሪካ የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ሊከበርለት የሚገባው ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ የሚከበርበት ነው፡፡ ዜጋ ሆንክም አልሆንክ፣ ከአፍሪካ መጣህ ከእስያ እኩል መብት አለህ፡፡

ለረጅም ዓመታት ኢህአዴግ ውስጥ እንደቆየ ሰው ከጠየከኝ ደግሞ፣ ፓርቲው ሲሰብከን እና እኛም እንደወረደ ተቀብለን ስናስተጋባ የነበረው ምን ያህል ውሸት እንደሆነ ትረዳለህ፡፡ ለምሣሌ፣ ኢሕአዴግ ከሌላው የሚለየኝ ብሎ ከሚናገረው ውስጥ ‹‹የዜጐች ቀጥተኛ ተሳትፎ›› የሚል ቃል አለ፡፡ የሚገርምህ፣ በዚህ ሀገር በሚካሄድ የዳኝነት ሥርዓት ብቻ በየቀኑ ከግማሽ ሚሊየን ህዝብ በላይ በቀጥታ ይሳተፋል፡፡ በዚህ ሂደት መሳተፍ የዜግነት ግዴታ ሆኖ ምንያህል ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዳለ የምትመለከትበት ነው፡፡

ሌላም ልጨምርልህ፡- በቅርብ ቀን በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢብኮ) በፖሊስ ፕሮግራም ላይ አቶ አንዳርጋቸውን ጽጌን ሲያቀርቡት ስለ እስረኛ አያያዝ የተሻሉ እንደሆኑ ሲናገሩ ሰምቼ ‹‹አባይን ያላየ፤ ምንጭ ያመሰግናል...›› ሆኖብኛል፡፡

በዚህ ሀገር ጋዜጠኛ እስረኛን ላነጋግር ብሎ ወህኒ ቤት ከሄደ መከልከል አይቻልም፡፡ ለእስረኛው ከመንግሥት እና ከሚዲያ ተቋማት ደብዳቤ ቢላክለት የእስር ቤቱ አስተዳደር መክፈት አይችልም፡፡

**ከተወሰኑ ወራቶች በፊት ለንባብ የበቃው የ‹‹መለስ ትሩፋቶች›› የተሰኘው መጽሐፍዎ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጪ ሀገራት እጅግ አነጋጋሪ ሆኖ ነበር፡፡ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገራት እውነተኛ ግብረ-መልሱን ቢነግሩን?**

እንዳነበብከው የ‹‹መለስ ትሩፋቶች›› መጽሐፍ ትኩረቱ ተወልጄ ስላደኩባት እና ወግ ማዕረግ ስላየሁባት አዲስ አበባ የተጻፈ ነው፡፡ ትኩረቱም ለአዲስ አበባ (ኢትዮጵያ) ወጣቶች ነበር፡፡ መጽሐፉ ከወጣ በኋላ የታሰበው ቀርቶ የመላ ኢትዮጵያውያን መወያያ ሆነ፡፡ ብዙ አንባቢያን ማጠንጠኛውን ካጣጣሙ በኃላ ‹‹ለምን ስለዚህም አልጻፍክም?›› የሚል የፍላጐት ጥያቄዎች ተዥጐደጐዱ፡፡

በመጽሐፉ ዙሪያ ሁለት አይነት አሰላለፎችን መመልከት ችያለሁ፡፡ የመጀመሪያው የገዥው መደብ ሃይሎች እና ተላላኪዎቻቸው ናቸው፡፡ ሁለተኛው መረጃ የሚፈልገው የዴሞክራሲ ሀይሉ ነው፡፡ የገዥው መደብ ሐይሎች እና ተላላኪዎቻቸው እጅግ ከመደናገጣቸው የተነሳ ወደ ሽምጥጥ ያለ ውሸትና ፍረጃ (Character assassination) ተሸጋግረው ነበር፡፡

ወደ ገፅ 12 ይዞሯል

> አቶ ኃይለማሪያም የመንግሥት ዋና ተጠሪና የኢህአዴግ ቢሮ ምክትል ሐላፊ ሆኖ አብረን ሰርተናል፡፡ ከጥንካሬው ለመነሳት ሐይለማሪያም የዝርዝር (detail) ሰው ነው፡፡ ከዚህ ተነስቼ ኃይለማርያም የአንድ ፋብሪካ ማናጀር ቢሆን ውጤታማ ይሆን ነበር የሚል እምነት አለኝ፡፡ የሰው ልጅን ለመምራት ( Leadership) ግን ቦታው አይደለም

# የኢህአዴግ እና የምርጫ ቦርድ ቁልቁለቶች



ስለሺ ሐጎስ

እስከዛሬ በተካሄዱ ምርጫዎች ኢህአዴግ ህዝቡ እንደማይፈልገው ይወቅ እንጂ የትኛውንም የማጭበርበር ስልት ተጠቅሞ እንደሚያሸንፍ ግን ጥርጣሬ አድሮበት አያውቅም፡፡ በምርጫ 2007 ዋዜማ ላይ ሆነን የኢህአዴግን ጉልህ ተግባራት ያየን እንደሆነ የዘንድሮውን ምርጫ አጭበርብሮም እንኳ ማሸነፍ እንደማይችል መገንዘቡን ብቻ ሳይሆን፣ ምርጫውን በአሸናፊነት ለማጠናቀቅ ያስቀመጠውን ስትራቴጂ በግልጽ ያሳብቃሉ፡፡ እንደሚታወቀው የኢህአዴግ ተፈጥሯዊ ባህሪም ይሁን የሚከተለው ውል-የለሽ ርዕዮተ-ዓለም የመድብለ ፓርቲ ስርዓትን ለመሸከም የሚያስችል ትከሻም ሆነ ትዕግስት የላቸውም፡፡ ለኢህአዴግ የምርጫ ፖለቲካ ማለት ኢህአዴግ ብቻ የሚያሸንፍበት “ውድድር” ማለት ነው፡፡ ካለፉት አራት ምርጫዎች እንደተረዳነው፣ ኢህአዴግ ምርጫን ለማሸነፍ ከማጨበርበር እስከ መግደል ርምጃ ለመውሰድ ወደኋላ አይልም፡፡

ኢህአዴግ፣ ለዘንድሮው ምርጫ የነደፈውን ስትራቴጂ በግልጽ እየተገበረ ነው፡፡ በአቅም በቁርጠኝነትና በዕውቀት ሊፎካከሩት የወሰኑ ፓርቲዎችን ከምርጫ ፉክክሩ ውጪ አድርጎና ብቻውን ተወዳድሮ ለማሸነፍ እየሰራ ነው፡፡ ይህን ተግባር እንዲከውን ከኢህአዴግ ተልዕኮ የወሰደው “ምርጫ ቦርድ” የአስመሳይ ገለልተኛነት ጭምብሉን አውልቆ እነዚህን ፓርቲዎች ከምርጫው የፉክክር ሜዳ ውጭ ለማድረግ ቀን ከሌት በመባቸር ላይ ይገኛል፡፡

ጠቅላይ ሚንስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ፣ ባለፈው ወር፣ በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ላይ፣ መንግስታቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በሶስት ክፍሎ እንደሚያያቸው ከጠቆሙ በኋላ “የአጨዋወታቸው ሁኔታ ታይቶ ቢጫ ወይም ቀይ ካርድ የሚሰጣቸው ፓርቲዎች አሉ፡፡” ብለው ነበር፡፡ በወቅቱ ይህን አነጋገራቸውን እንደተራ የአፍ ወለምታ የቆጠሩት ሰዎች ያሉ ቢሆንም፤ በርካቶች መንግስት በፓርቲዎች ላይ ሊወስድ ያሰበው ርምጃ እንዳለ የሚያመላክት ንግግር እንደነበር ተስማምተውበት አልፏል፡፡ አሁን የበርካቶቹ ግምት እውን እየሆነ ነው፡፡ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) እና የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የቀዩ ካርድ ሰለባ ለመሆን የተቃረቡ ፓርቲዎች ሆነዋል፡፡ ሰማያዊ ፓርቲም ለጊዜው ከቀዩ ካርድ የራቀ ቢመስልም ከታማኝ ምንጮች እየተሰማ ያለው መረጃ የሰማያዊ ዕጣ ፈንታ ከነአንድነት የተለየ እንደማይሆን ነው፡፡

የአቶ ኃ/ማርያም ማስጠንቀቂያን ተከትሎ ምርጫ ቦርድ ተልካሻ ምክኒያቶችን እያግተለተለ እነዚህን ሀቀኛ ፓርቲዎች ከውድድሩ ሜዳ ውጪ ለማድረግ እንገፍ እንገፍ ማለት መጀመሩ የሚያሳየው አንድ እውነት፣ እንደሚባለውም ቦርዱ የኢህአዴግ አምስተኛ አባል ፓርቲ መሆኑን ነው፡፡

የሆነው ሆኖ ኢህአዴግ በዘንድሮው ምርጫ ብቻውን ለመወዳደር ወስኗል፡፡ ስለዚህ ዋናው ጥያቄ እንዲህ አይነቱ የፈሪ ውሳኔ ከሽንፈት ያድናል ወይ? የሚለው ነው፡፡ ኢህአዴግ እንዲህም አድርጎ ምርጫውን መቀልበስ ቢችል እንኳ ይህ አካሄድ ብቻውን ከሽንፈት እንደማያድነው መረዳቱን የሚጠቁሙ ምልክቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ ያህል ሰንደቅ ጋዜጣ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች አገኘሁት ብሎ ጥር 6 ቀን 2007 ዓ.ም የሰራውን ዜና መጥቀስ ይቻላል፡፡

በዜናው መግቢያ ላይ “በ2007 ዓ.ም በግንቦት ወር በሚደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ ሕገ-ወጥ፣ ያልተፈቀዱ ማንኛውም አይነት ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎችን የምርጫውን ፀጥታና ደህንነት ከማወካቸው በፊት ፈጥኖ የሚደርስ አዲስ ኮማንድፖስት እና ልዩ ግብረኃይል መቋቋሙን የሰንደቅ ምንጮች ገለፁ፡፡” ይልና ወደ ውስጥ ሲገባ ዜናው “ከምርጫ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ችግሮችና በምርጫው ሂደት ጋር በተያያዘ በሚፈጠሩ ችግሮች ላይ መረጃና ማስረጃ ወደማሰባሰብ የተግባር ስምሪት በመግባት ሥራውን እየሠራ እንደሚገኝ ምንጮች አረጋግጠዋል፡፡… ይህ የተቋቋመው ኮማንድፖስትና ልዩ ግብረኃይል ከመንግስት ትዕዛዝ ሲደርሰው አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ የመውሰድ ሙሉ ስልጣን እንደተሰጠው ታውቋል፡፡” የሚሉ ሀተታዎችን እናገኛለን፡፡ ይህ ምን ማለት ነው?

ብዙ መመራመር የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡፡ እነዚህ ተገፍተው ከምርጫ የሚወጡ ፓርቲዎች እጃቸውን አጣጥፈው እንደማይቀመጡ ግልጽ ነው፡፡ በተለይ አንድነት ፓርቲ ያሉትን የሰላማዊ ትግል አማራጮች በሙሉ አሟጦ ለመጠቀም በቃልም በተግባርም አረጋግጧል፡፡ ከላይ ያየነው የሰንደቅ ጋዜጣ ዜና ይህ የአንድነት አቋም ገዢው ፓርቲን እያባነነው እንደሆነና አንዳች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ቢከሰት በጉልበት ለመግታት ያለውን ፍላጎት የሚያሳይ ነው፡፡ በተለይ “አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ የመውሰድ ሙሉ ስልጣን እንደተሰጠው ታውቋል፡፡” የምትለዋ ዓ.ነገር፣ ኢህአዴግ የጅምላ እስርና ግድያ ውስጥ ለመዘፈቅ መቁረጡን የምታሳይ ነች፡፡

እንዲህ አይነቱ “ስልጣን ወይም ሞት” አይነት ፍጹም አምባገነናዊ አካሄድ በአለም ላይ ማንንም ሲያዋጣ አልታየም፡፡የኢህአዴግ አካሄድ ለሀገርና ለህዝብ ብቻ ሳይሆን ለራሱ ለኢህአዴግም ቢሆን አውዳሚ መንገድ በመሆኑ ስርዓቱ ቆም ብሎ ማሰቢያ ጊዜው አሁን መሆኑን መጠቆም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ሰሚ ከተገኘ!

# አስቴር በዳኔ፣ ኢህአዴግና አርቲስቶች



ዳዊት ሰለሞን

አርቲስት አስቴር በዳኔ ከኢሳት ሬዲዮ አዘጋጅ ተቦርነ በየነ ጋር ቅልብጭ ያለች ቃለ ምልልስ አድርጋ ብዙ መልዕክት አስተላልፋለች፡፡ ይህች አጠር ያለች ጽሑፍም ቃለ ምልልሱን ተከትላ የተከተበች ነች፡፡ ቃል በቃል ባይሆንም አርቲስቷ ተቦርነ ለወረወረላት ጥያቄ ከሰጠችው መልስ ውስጥ ‹‹ከጥያቄዬ በኋላ ጄነራል ሳሞራ የኑስ እኔ ወዳለሁበት በመምጣት ‹‹ብዙዎቹ አፋቸውና ሆዳቸው አንድ አይደለም አንቺ ግን ያመንሽበትን ስለተናገርሽ አመሰግንሻለሁ፡፡ እንደአንቺ አይነቶቹን እኛ እንፈልጋለን፡፡ ›› ያሉኝ ሲሆን የትግራይ የሙዚቃ ቡድን አባላት አድንቀውኝ ‹‹እኛ የተዋጋነው እንዳንቺ ሰዎች የሚያምኑበትን እንዲናገሩ ነው›› አሉኝ የሚል ዐረፍተ ነገር እናገኛለን፡፡

አስቴር ከዝግጅቱ በኋላ አብረዋት የተጓዙ አርቲስቶች አብረዋት ለመቆም እንኳን ሳይደፍሩ እቤቷ መግባቷንም ተናግራለች፡፡እርግጥ ነው፣ ኢህአዴግ ወታደራዊ ድርጅት ነው፡ ፡ እነአስቴር ሄደው እንዲያዩ የተደረገውም የኢህአዴግን መካነ ልደት (የውልደት ቦታ) ነው፡፡ ቦታው የሚያወራው በሀሳብ፣ በአይድኦሎጂ አልያም በፕሮግራም ስለተወለደ ድርጅት አይደለም፡፡ በመግደልና በመሞት መስዋዕትነት ሀይለኛውን በሀይል ስለጣሉ የጦር ሜዳ ጀግኖች የሚናገር ቦታን ነው እነአስቴር የጎበኙት፡፡ ከዚህ ቦታ የፈለቁ ተጋዳላዮች የሚያውቁትና በቀላል ቋንቋ የሚረዱት መግደል እና መሞትን ነው፡፡ ገጠመኞቻቸው ከዚሁ ከመግደልና ከመሞት ምንጭ የተቀዱ ናቸው፡፡ ለእነርሱ ያለው ዓለም በሁለት የተከፈለ ነው በጠላትና በወዳጅ፡፡ በእነርሱ ካምፕ የተገኘ ጓድ በሌላኛው ካምፕ የተሰለፈ ደግሞ ጠላት ነው፡፡ ሁልግዜም ልባቸው የተሰፋችው በዚያኛው ካምፕ የሚገኙትን አልሞ ስለመምታት ነው፡፡ ለዚህ ድርጅት አመራሮች ‹‹መቼ በምርጫ ትወርዳላችሁ? … ተቃዋሚዎች ከሚለው ቃል ይልቅ ለምን ተፎካካሪዎች የሚል ቃል አትጠቀሙም?›› በማለት መጠየቅ ግፉ ቢል የሚታያቸው የአርቲስቷ ድፍረት ነው፡፡ ከዚያ ባለፈ ጥያቄው ገብቷቸው ጥያቄው የሚፈልገውን ምላሽ ሊሰጧት አይችሉም፡፡

አቶ በረከት ስምኦን በ‹‹የሁለቱ ምርጫዎች›› ወግ መጽሐፋቸው፣ ቅንጅቶች በ1997 ዓ.ም ሀገር ዓቀፍ ምርጫ ያገኙትን የህዝብ ድምጽ ‹‹ንፋስ ሰጣቸው›› በማለት ለመቀለድ የሞከሩትም ድርጅታቸው በምርጫ ሥልጣን ለመልቀቅ ፍላጎቱም ዝግጅቱም እንዳልነበረው ከማወቃቸው የተነሳ ነው እንጂ ወደ ውድድር የገባ ፓርቲ ማሸነፍና መሸነፍ የጨዋታው ህግ መሆኑን ሊስተው አይችልም፤ ንፋስ መርጧል ለማለት እስካልደፈርን ድረስ፡፡ በረከትና ጓዶቻቸው ግን በቅንጅት ከፍተኛ ድምጽ ማግኘት በመደናገጥ ከድምጽ ናዳው ነፍጥ አንጋቹን ኢህአዴግን ለመታደግ የብዙዎችን ህይወት ቀጠፉ፡፡ ከዚያ ጊዜም በኋላ በስፋት ‹‹እንዴት በምርጫ ካርድ ሥልጣን እናስረክባለን›› የሚሉ ድምጾች በኢህአዴግ ቤት በስፋት መደመጥ ጀመሩ፡፡ሥልጣኑን ያገኘነው በብረት ትግል በመሆኑ ሥልጣኑን የፈለገ በእኛው መንገድ መምጣት ይገባዋል አሉን፡፡

አስቴር በደደቢት በረሃ ለደደቢት ልጆች ያነሳችውን አይነት ጥያቄ ከእርሷ ቀደም ብለው ብዙዎች ተደራጅተውም ይሁን በነጠላ ኢህአዴግን ሲጠይቁ ቆይተዋል፡፡ ለምሳሌ ሳሞራ ‹‹እንደአንቺ አይነት እንፈልጋለን›› ቢሏትም እውነታው ግን ይህ እንዳልሆነ አስቴርም ሳሞራም ያውቃሉ፡፡ለዚህም ነው አስቴር ተቦርነ ሲደውልላት በመጀመሪያ ‹‹እፈራለሁ… እናንተ ሰዎች ወደማልፈልገው ነገር እንዳትከቱኝ›› ያለችው፡፡ምን አስፈራት? ሳሞራ ያወሩትን ሳይሆን እንደ እርሷ ጥያቄያቸውን የወረወሩ፣ ለሀገራቸው በጎ ያሰቡ ሴቶችና ወንዶች የት እንደሚገኙ በማወቋ ይመስለኛል፡፡ መቼም አስቴር የመድረክ ሰው በመሆኗ ፍርሃቷ የመናገር አይመስለኝም፡፡ እነበረከት ከድርጅታቸው ውጪ የሚናገሩና የተለየ አቋም ላራመዱ ዜጎች በመድረክ፣ በሀሳብ እየታገሉ እዚህ የደረሱ አይደሉም፡፡ ቢሆንም ‹‹ተናገሪ›› ይሏታል ስትናገር የሚያደምጧት ይመስል!

በአንድ ወቅት ዛሬ በወህኒ ቤት የሚገኘውን ወጣቱን ፖለቲከኛ ሐብታሙ አያሌውን ‹‹ለምን ከኢህአዴግ ቤት ወጣህ?›› የሚል ጥያቄ አቅርቤለት ነበር፡፡ ሐብታሙ ምክንያቱን ሲያስቀምጥ ‹‹ኢህአዴግ ቤት ሀሳብ በመሸጥ መቀጠል ባለመቻሌ ወጥቻለሁ›› ነበር ያለኝ፡፡ (ላይፍ መጽሔት ቅጽ 7 ቁጥር 113 ላይ ቃለምልልሱን ያገኙታል) ኢህአዴግ ለተለየ ሐሳብ ስፍራ የሚሰጥ የዜጎችን የማሰብ ነጻነት የሚያከብር ድርጅት ባለመሆኑ የራሱን አባላት ጭምር የማሰብ ነጻነት በመጋፋቱ ዛሬ ከድርጅቱ መስራቾች የሚበዙት ከኢህአዴግ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በፍቺ በማቋረጥ ድርጅቱ የሰዎችን የማሰብ ነጻነት እንዲያከብር እየታገሉት ይገኛሉ፡፡

ጥያቄው የዜጎችን የማሰብ ነጻነት የማያከብር ድርጅት ስለ ምን እንደ አስቴር በዳኔ ያሉትን ‹‹እኛ የምንፈልገው የምታስቡትን እንድትናገሩ ነው›› ይላቸዋል የሚለው ነው፡፡ በእኔ እምነት ‹‹ተናገሩ›› የሚሉት የህዝቡን አሰላለፍ ከማወቅ በመነሳት ይመስለኛል፡፡ለዚህ ግምቴ መደገፊያ የሚሆነኝ ጄነራል ሳሞራ ‹‹ብዙዎች ሆዳቸውና አፋቸው አይገናኝም›› በማለት መናገራቸው ነው፡፡ሳሞራና ጓዶቻቸው ስቃይ ውስጥ ናቸው፡፡ከእነርሱ ጋር የምር የተሰለፈውንና እያሳሳቀ ጊዜውን የሚገፋውን በመለየት ቅርቃር ውስጥ እየዳከሩ ይገኛሉ፡፡ እናም እንደ አስቴር ያሉት ራሳቸውን ገልጠው የፍርሃቱን ጠርሙስ ሰብረው ሲናገሯቸው ልባቸው ጮቢ ትረግጣለች፡፡ ስለዚህ የአርቲስቱም፣ የጋዜጠኛውም፣ የነጋዴውም፣ የኢንቨስተሩም ወዘተ. ጀርባ ይጠና ዘንድ የሚናገሩ አንደበቶች ይበረታታሉ፡፡

አንድ ለመውጫ ሳሞራ የኑስ ደደቢት በረሃ ድረስ ከተጓዙ አርቲስቶች የሚበዙት ሆዳሞች እንደሆኑ የሚያምኑ ይመስላሉ፡፡ አንዳንዶቹም ደርግን ያገለገሉና አፋኙን ሥርዓት ሲያንቆለጳጵሱ የነበሩ መሆናቸውን ሳያስታውሱ አልቀረም፡፡እነዚህ አርቲስቶች ነገ ኢህአዴግ ሥልጣኑን ቢለቅ አዲሱን የሚያወድሱና የወደቀውን የሚረግጡ እንደሚሆኑ ስለገባቸው ‹‹ሆዳቸውና አንደበታቸው የተለያየ ነው››ብለዋታል፡፡ እንደውም ሳሞራ ይህንን ያሉት ሰራዊት ፍቅሬን አጠገባቸው ስላገኙት ሁሉ ይመስለኛል፡፡ ይህ ንግግር ህሊናን አንድ ቀን ለሚያገኟት አርቲስቶች ህመም ነው፡፡ ‹‹ሆዳቸውና አንደበታቸው የተለያየ ነው›› ደስ የሚለው ነገር የኢህአዴግ መሪዎች በላተኛ ብቻ እንደሚያጨበጭብላቸው መገንዘባቸው ነው፡፡ አስቴርም የጓደኞቿ ነገር አግራሞት ፈጥሮባት ‹‹ከዝግጅቱ በኋላ አንዳቸውም አብረውኝ ለመታየት አልፈለጉም›› ብላለች፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬም መንግሥትን በአደባባይ መተቸት እግዜሩን ወይም አላህን እንደ መስደብ የሚቆጠርባት ሀገር ለመሆኗ የጥበብ ሰዎቻችን ድርጊት ይመሰክራል፡፡

ይህ ‹‹ለህዝቦች ነጻነት ታግያለሁ›› ለሚለውና ለ24 ዓመታት በምኒሊክ ቤተ-መንግሥት ለተቀመጠው ኢህአዴግ ትልቅ ስድብ ነው፡፡ አርቲስቶቹ አስቴር አንድ ጥያቄ ፈራ ተባ እያለች በመጠየቋ ለህይወታቸው፣ ለክብራቸውና ለሆዳቸው በመስጋት ተለይተዋታል፡፡ ኢህአዴግ ‹‹የመናገር ነጻነት እንዲከበር አድርጌያለሁ›› ቢልም ድርጅቱ በተወለደበት ቦታ የተገኙ ሰዎች በፍርሃት ቆፈን መጨራመታቸውን አስቴር ወለል አድርጋ አሳይታናለች፡፡

ማናቸውም ማኅበራዊ ጉዳዮችን በማህበራዊ ህይወት ላይ ሚና ያላቸው ፍሬ ነገሮች የያዙ ጽሁፎች በዚህ አምድ ይስተናገዳሉ፡፡

# አማካዩን ፍለጋ


## (የብሌን ሳህሉ ጥያቄ፣ የትውልዱ ጥያቄ!)



በሪሁን አዳነ

ብዙዎቻችን ወ/ሮ ሕይወት ተፈራን ‹‹Tower in The Sky›› በተሰኘው ግሩም መጽሐፏ እናውቃታለን፡፡ በየካቲት 66ቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት ወቅት በልዩ ልዩ ጎራ ተሰልፈው በእንቅስቃሴው የተሳተፉ ብዙ ሰዎች መጻሕፍት ጽፈዋል፡፡ ገና ብዙ ሥራዎች እንደሚታተሙም ይጠበቃል፡፡ እስከ አሁን ከተጻፉት መጻሕፍት መካከል የሕይወት ተፈራ መጽሐፍ በብዙ መልኩ የተለየ ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የበቀል፣ የመከላከል ወይም ወገንተኛ የመሆንና በሌሎች ላይ ጣት የመቀሰር አካሄድን የተከተለ አይደለም፡፡ ይልቁንም በዚህ መጽሐፍ ሕይወት አብዝታ የምትነግረን ስለመቻቻልና የተለየ ሐሳብን ስለማስተናገድ አስፈላጊነት፣ ‹‹ትክክሉ እኔ የያዝኩት ወይም የእኔ ድርጅት የሚያራምደው አቋም ብቻ ነው›› የሚለው አስተሳሰብ ችግር ያለው ስለመሆኑ፣ ግራ ቀኙን ማየት አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ መጽሐፉ ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ አንባቢ ተደራሽ ይሆን ዘንድ ‹‹ማማ በሰማይ›› በሚል ርዕስ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ቀርቧል፡፡የአማርኛው ትርጉም መውጣቱን ተከትሎም ባለፉት አርብ እና ቅዳሜ ዕለታት ውይይት ተደርጎበታል፡፡ጸሐፊዋ የውይይቱ ተሳታፊዎች የዚህ ትውልድ አባላት እንዲሆኑ በመወሰኗ በዋቢ ሸበሌ ሆቴል በተከናወነው ሥነ-ሥርዓት አርብ አምስት፣ ቅዳሜ ዕለት ደግሞ አራት ‹‹ወጣቶች›› መጽሐፉን በተመለከተ የተሰማቸውን ሀሳብ አቅርበዋል፡፡










በዚህች አጭር ጽሑፍ፣ በውይይቱ ላይ የተነሱትን ሐሳቦች በሙሉ ለመዳሰስ አንሞክርም፡፡ ዓላማችን የሕግ ባለሙያዋ ወ/ሪት ብሌን ሳህሉ ባነሳቻቸው ነጥቦች ላይ ተመርኩዘን የተወሰኑ ነገሮችን ለመሰንዘር፣ ከተቻለም የውይይት መድረክ ለመክፈት ነው፡፡ ወ/ሮ ሕይወት ለውይይቱ ታዳሚዎች ባደረገቸው ንግግር ስለመቻቻል፣ የተለየ ሐሳብ የሚያራምዱ ሰዎችን ስለማስተናገድና ግራ ቀኙን ስለማየት አስፈላጊነት አጽንኦት ሰጥታ የገለጸች ሲሆን የወ/ሪት ብሌን ሐሳብም ይህንን መሠረት ያደረገ ነበር፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ፣ የሕግ ባለሙያዋ በልዩ ልዩ የፖለቲካ መስመሮች የተሰለፉ ኃይሎች በመካከላቸው የአመለካከት ልዩነቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ (ወይም አይቀሬ እንደሆኑ) በመገንዘብ የተለየ ሐሳብ የሚያራምዱ ወገኖችን ከመፈረጅ ተቆጥበው ልዩነቶቻቸውን በሰለጠነ መንገድ መፍታት እንዳለባቸው አስገንዝባለች፡፡

በሀገራችን በተለይ በአብዮቱ ዘመን የፖለቲካ ተቀናቃኞችን በተለያየ መንገድ በመፈረጅና ስም በመስጠት ከሰውነት ተራ የማውረድ (ዲሂውማናይዝ የማድረግ) አካሄዶች በሰፊው እንደተሰራባቸው እናውቃለን፡፡ብሌን እንዳለችው በየትኛውም ሀገር የሰውን ነብስ ማጥፋት የሚወገዝ ነገር በመሆኑ መሰናክል ነው ተብሎ የሚታሰበውን አካል ከሰውነት ተራ ማውረድ የመጀመሪያው እርምጃ ይሆናል፡፡ በሀገራችንም ቢሆን ‹‹ፀረ-አብዮት››፣ ‹‹ፀረ-ሕዝብ››፣ ‹‹ፀረ-ልማት››፣ ‹‹አምስተኛ ረድፈኛ››፣ ‹‹ግልገል ፊውዳል››፣ ‹‹ወንበዴ››፣ ‹‹ተላላኪ›› … ወዘተ የሚሉትን ስያሜዎች መለጠፍ የተለመደ እንደነበር የሚዘነጋ አይደለም፡፡

አሁንም ከአርባ ዓመታት በኋላ ካለፉት ጥፋቶች ተመክሮ ቀስመን ከዚህ የጥፋት መንገድ አለመሰብሰባችን ነው፡፡ ዛሬም ‹ፀረ-ልማት››፣ ‹‹ፀረ-ሠላም››፣ ‹‹አሸባሪ››፣ ‹‹ትምክህተኛ››፣ ‹‹ጠባብ››፣ … ወዘተ የሚሉትን ስያሜዎች እስኪሰለቸን እንሰማቸዋለን፡፡ የተለየ ሐሳብ ያላቸው ወገኖች ሁሉ ይፈረጃሉ፤ ይሳደዳሉ፡፡ አሁንም ‹‹ትክክሉ እኔ የያዝኩት አቋም ብቻ ነው፤ ከእኔ ውጪ ያለው የማይረባ ብቻ ሳይሆን መጥፋት ያለበት ነው›› ይባላል፡፡

ዛሬም እንደ ትናንቱ የተለየ ሐሳብ ያላቸው ሰዎች በሰለጠነ መንገድ አይስተናገዱም፡፡ በጠላትነት ይፈረጃሉ፡፡ ለዚህ አስረጅ ይሆነን ዘንድ ኢሕአዴግ ‹‹ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ አንድነት በኢትዮጵያ›› በሚለው ሰነዱ ያስቀመጠውንና ደጋግመን የምንጠቅሰውን ጽሑፍ አሁንም በድጋሚ እንየው፡- ‹‹በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት የተደቀነው ምርጫ ግልጽና ቀላል ነው፡፡ አንድም በጥገኝነት መንገድ ተጉዞ ወደ ፀረ-ዴሞክራሲ፣ ወደ እልቂትና ብተና መጓዝ ነው፤ አሊያም ጥገኝነትን መክቶ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጎዳና ወደ ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ መራመድ ነው፡፡ ሌላ ምርጫ የለም፡፡ምርጫው የሕልውና ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መሀል ሰፋሪና ታዛቢ ሆኖ ሊያልፈው የሚችል አይደለም፡፡አንድም የሰላም የልማትና የዴሞክራሲ ወገን ሆኖ ይሰለፋል፣ አሊያም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የጥፋትና የጥገኝነት ኃይል ይሆናል፡፡ ወጣቱ በተለይም ወጣቱ ምሁር የሀገር ተረካቢና መሪም በመሆኑ የሚሻለውን መርጦ ሚናውን መለየት ይጠበቅበታል፡፡››ይላል አገዛዙ፡፡

ብሌን፣ ወ/ሮ ሕይወት ግራ ቀኙን ስለማየት አስፈላጊነት ያስገነዘበችውን እንደምትቀበል ከገለጸች በኋላ ግራና ቀኙን ማየት የሚቻለው ግን ግራና ቀኝ ሲኖር መሆኑን ጠቁማለች፡፡ ‹‹ዛሬ በሀገራችን የዚህ ዓይነት፣ ‹ግራ ቀኝ› አለ ወይ?›› ስትል ጠይቃለች፡፡ ጓደኞቿ (የዞን ዘጠኝ ጦማሪዎች አባላት ናቸው) ኤዶምና ማህሌት በእስር ቤት እንደሚገኙም እንባ እየተናነቃት ተናግራለች፡፡ በዕለቱ የተሰማትን ነገር በመናገሯ ‹‹ምን ይደርስብኝ ይሆን?›› ብላ እየሰጋች እንደምትናገርም ጠቁማለች፡፡ የብሌን ጥያቄ የአንዲት ወጣት ጥያቄ አይደለም፤ የትውልዱ ጥያቄ ነው ሊባል የሚችለውም በዚህ ምክንያት ይመስለናል፡፡ብሌን የተሰማትን በመናገሯ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ ከተገኙት የአገዛዙ ካድሬዎች በኩል በስብሰባ መሪዋ በኩል ተግሳጽ ተልኮባታል፡፡ እነኚህ የትናንቱን አፋኝ ሥርዓት ሲቃወሙ የነበሩ ኃይሎች ሌላ አፋኝ የሆነ ሥርዓት መትከላቸው እጅግ የሚያስገርምና የሚያሳፍር ነው፡፡

ወጣቱ ካለፈው ትውልድ ስህተቶች ትምህርት ቀስሞ ግራ ቀኙን እንዲመለከት፣ አክራሪ የሆነ አቋም ከማራመድ እንዲቆጠብና አማካዩን እንዲፈልግ፣ አማካዩን ለመፈለግ የሚያስችል ከባቢ ያስፈልገዋል፡፡ አሁን የተያዘው ‹‹ወይ እኔን ትደግፋለህ፣ ካልሆነ ጠላት ነህና ትጠፋለህ›› የሚለው አካሄድ ግን ምርጫን የሚያሳጣ የአፈና አገዛዝ ነው፡፡ አንባገነኖች ሥልጣንና ከሥልጣን የሚገኘው ሀብት አዕምሯቸውን ስለሚደፍነው ከታሪክ አይማሩም፡፡በመሣሪያ ኃይል፣ ልዩ ልዩ ፍርፋሪ በመስጠትና ተላላኪዎችን በመፈልፈል ሁሉንም ዜጋ ሰጥ ለጥ አድርገው መግዛት የሚችሉ ይመስላቸዋል፡፡ ደግነቱ ይዋል ይደር እንጂ ለጓዶቻቸውና ለወገኖቻቸው የታመኑ አገር ወዳድ ዜጎች በመኖራቸው የአንባገነኖች ከንቱ ምኞት ሁልጊዜም እንደተቀበረ ነው፡፡

ይህ አምድ እናንተ አንባቢያንን ጨምሮ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በምርጫ 2007 ጉዳይ ላይ የሚወያዩበት ነፃ መድረክ ነው፡፡

# የሕግ ባለሙያዎች ስለ ምርጫ 2007



ጠበቃ ተማም አባቡልጉ

‹‹ሕዝብ ሁሉም የእሱ መሆኑን ማወቅ አለበት››



የሕግ አማካሪ ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ወሰኔ

‹‹ፍርድ ቤት …በገለልተኝነት ይሰራል የሚል እምነት የለኝም››



ዳኛ ፀጋዬ ደምሴ

‹‹የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ራስን በራስ ሳንሱር እንድታደርግ ያስገድዳል››

በምርጫ 2007 ዙሪያ የዚህ ዕትም እንግዶች ያደረግናቸው የሕግ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ጠበቃ ተማም አባቡልጉን፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ረዳት ዳኛ የሆኑትን አቶ ፀጋዬ ደምሴንና በአንድ የግል ድርጅት ውስጥ የህግ አማካሪ ሆነው በመስራት ላይ ያሉትን ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ወሰኔን ባልደረባችን ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ እንዲህ አወያይቷቸዋል፡፡

## አምስተኛው ብሄራዊ ምርጫ ለማካሄድ ሂደቱ ተጀምሯል፡፡ ምርጫ የሚካሄድባቸው የሕግ ማዕቀፎች ምን ያህል ፍትሃዊ ናቸው?

### ተማም አባቡልጉ

ምርጫን ፍትሃዊ የሚያደርገው የመራጩ ህዝብ ፍላጐትና ፍትሃዊ መሆን እንጂ የሚካሄድባቸው የሕግ ማዕቀፎች ፍትሃዊነት ብቻ አይደለም፡፡ ሁለቱም (ምርጫም ሆነ የሕግ ማዕቀፍት) የሚዘጋጁትና የሚቆሙት ለሕዝቡ እስከሆነ ድረስ የሚኖሩት ሕዝብ እስከፈለጋቸው ሲሆን የሚመልሱትም የሕዝቡን ፍላጐት ነው፡፡ የሕዝቡ ፍላጐት መሻሻል የሁሉንም መሻሻል የሚወስን ይሆናል፡፡

### ፀጋዬ ደምሴ

በመሠረቱ ምርጫን በተመለከተ በሕገ-መንግሥቱ ላይ ተቀምጧል፡፡‹‹በየጊዜው የሚደረግ ነጻ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ይካሄዳል›› ይላል፡፡ ሕገ-መንግሥታችን ያንን መሠረት በማድረግ ደግሞ በተወካዮች ምክር ቤት የወጡ ህጐች አሉ፡፡ በዋነኘነት ያንን የምርጫ ሕግ መሰረት በማድረግ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጡ ደንቦች አሉ፡፡ ማንኛውም 18 ዓመት የሞላው ኢትዮጵያዊ በሕግ ወይንም በፍ/ቤት እንዳይመርጥ ያልተከለከለ ማንኛውም ሰው በምርጫው ላይ መሳተፍ ይችላል፡፡ በሕገ-መንግሥቱም ሆነ በአዋጁ ላይ የመምረጥ መብትን ያረጋግጣል፡፡

‹‹የሕግ ማዕቀፉ ምን ያህል ምቹ ነው/ አይደለም›› ለማለት ሌሎች ህጐችን ማየት አለብን፡፡ ለምሳሌ፣ ‹‹ምርጫውን የተሳካ እንዳይሆን ላያደርጉ ይችላሉ›› ተብለው የሚታሰቡ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ አሁን ግን እያወራሁ ያለሁት ‹‹አንድ ሰው፤ አንድ ዜጋ ለመምረጥ መብት አለው ወይ)›› በሕገ-መንግሥቱ የሚለውን ልመልስ ብዬ ነው፡፡

### ኤልሳቤጥ ወሰኔ

አሁን ያሉት የህግ ማዕቀፎችም ምርጫ ለማካሄድ ብቻ ሳይሆን ዜጎች በዕለት ተዕለት የሚኖራቸውን ግንኙነት እና የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ለመፍታት አልቻሉም፡፡ ይህም የሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው ሕጎቹ ያሉባቸው ክፍተቶች ሲሆን ሁለተኛው ገዥው ፓርቲ የሕግ ማዕቀፎችን በመሳሪያነት የሚጠቀም በመሆኑ ከይስሙላነት ያለፈ ተግባር የሌላቸው በመሆኑ ነው፡፡

ሌላው ክፍተት፣ በአንድ በኩል ሕገ-መንግሥቱን ጨምሮ ሌሎች ሕጎች የወቅቱን ማኅበረሰብ ወቅታዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የተቀመጡ አለመሆናቸው ነው፡፡ የአፍሪካን ጨምሮ በርካታ ሀገራት ለዴሞክራሲያዊ ግንባታ በሚያመች መልኩ ሕገ መንግሥቶቻቸውን አሻሽለዋል፡፡ አብዛኛዎቹ ሕገ መንግሥታቸው ላይም ሆነ ሌሎች አዋጆቻቸው ላይ ያሉትን አንቀጾች ያሻሻሉት በምርጫ ወቅት በተፈጠረባቸው ግርግር ምክንያትና ፍትሓዊ ምርጫ ለማካሄድ የማያስችሉ በመሆናቸው ነው፡፡ …

ሕገ መንግሥቱ የህጎች ሁሉ የበላይ እንደመሆኑ ህዝብ አምኖ ሊገለገልበት ይገባዋል፡፡ ሕገ-መንግሥቱ ስለ አንድ ሀገር ቁልፍ እሴቶች የሚያስተምርና የሚደነግግ ካልሆነ ለምርጫ ይቅርና የሀገሪቱን ህዝብ የዕለት ተዕለት መስተጋብር ለመዳኘት ሳይቻለው ይቀራል፡፡ በሀገራችን ህዝቡ ሕገ-መንግሥቱ ላይ እምነት ስለማይጥል ተመሳሳይ ችግሮች ይታያሉ፡፡ የአንድን ህዝብ የዕለት ተዕለት መስተጋብር ለመዳኘት ያልቻለ ሕገ-መንግሥት ምርጫን ያክል ትልቅ ፋይዳ ያለው ሁነት ሊዳኝ አይችልም፡፡

## እንደ የጸረ-ሽብርተኝነት፣ የመያዶችና የፕሬስ አዋጆችን የመሳሰሉ አወዛጋቢ ሕጎች በምርጫው ላይ የሚኖራቸው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

### ተማም አባቡልጉ

ሁሉም ሰው ራሱን ካወቀበት ዕለት አንስቶ እየመረጠ ነው ያለው፡፡ ወደፊትም እየመረጠ ይቀጥላል፡፡ ምርጫው ግን ከተፈጥሮ ሕግ (ከመርህ) ጋር የተስማማ ከሆነ ይበለጽጋል፡፡ ካልሆነ ደግሞ እንደዚያው፡፡ በምርጫችን ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችለው ጉዳይ ይህ ብቻ ነው፡፡ የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጁ ሕገ-መንግሥቱ ላይ የተደነገገውን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ይደፈጥጣል፡፡ አዋጁ 38 አንቀጾች አሉት፡፡ በጣም ብዙ ነው፡፡ ሌሎች ሕጉ ያላቸው ሀገራት በቁጥር አነስተኛ አንቀጾች ነው ያላቸው፡፡ አዋጁ በፖለቲከኞች፣ በጋዜጠኞችና በዜጎች ላይ ትልቅ ጫናን የሚፈጥር ነው፡፡ አዋጁ በሰላም ወጥቶ መግባትን እንኳን አስቸጋሪ የሚያደርግ ነው፡፡ የመያዶችም ሆነ የፕሬስ አዋጆቹ አፋኞች ናቸው፡፡

### ፀጋዬ ደምሴ

የፕሬስና የበጐ አድራጐት አዋጆች ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲያከራክሩ ነበር፡፡ ተቃዋሚዎች የሚያነሱት መከራከሪያ አለ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት ሕጉን ሲያወጣ ‹‹በቂ ምክንያት አለኝ›› ብሎ ይከራከራል፡፡ እንደ ህግ ባለሙያ በግሌ የተረዳሁትን ነው የምናገረው፡፡

መምረጥ መብት ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሥርዓት መኖሩ ከሚረጋገጥባቸው ምክንያቶች ዋነኛው ምርጫ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ምርጫ ለመምረጥ ደግሞ ወይንም በሕገ-መንግሥቱ የተቀመጠውን የመምረጥ መብት ለመጠቀም ተስማሚ ምኅዳር ሊኖር ይገባል፡፡ የእነዚህ ሕጐች ተፅዕኖ ምንድን ነው) ለሚለው ጥያቄህ፣ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁን በሁለት መንገድ ማየት እንችላለን፡፡ በመጀመሪያ ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ ከአሁን በፊት በነበረው ምርጫ ላይ የተሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ ሚዲያዎች ይህን አዋጅ መሰረት በማድረግ ምን ችግር ደረሰባቸው) ወይም የደረሰባቸው ነገር በአሁኑ ምርጫ ላይ ያለውን ሕጉ ራሱ (የሕጉ አገላለፅ በአሁኑ ምርጫ ላይ ምን ያስከትላል)) የሚለውን ለማየት እፈልጋለሁ፡፡አዋጁ ከወጣ በኃላ ብዙዎች ታስረዋል፣ ተከሰዋል፣ ያልተፈረደባቸውም አሉ፡፡ ብዙ የፕሬስ ድርጅቶች ከገበያ ውጭ ሆነዋል! ያህንን መሰረት በማድረግ፣ አሁን ላይ በሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሚዲያዎች ላይ ተፅዕኖ ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ፡፡

መንግሥት ይህን አዋጅ ሲያወጣ ሕጋዊ የሆነ መሰረት አለው፡፡ መንግሥት ሀገሪቱን፣ ህዝቡንና ዜጋውን ከሽብር የመጠበቅ ኃላፊነት አለው፡፡ ሆኖም አወጁን መሠረት በማድረግ የተደረጉ ነገሮችን መገምገም የዳኞች ሥልጣን ነው፡፡ ዳኛው ሕጉን መሰረት አድርጐ፣ ‹‹በቂ ማስረጃ አለኝ›› ብሎ ካመነ ይፈርዳል፡፡ ነጻም ሊለቅ ይችላል፡፡ አዋጁን መሰረት አድርጐ የተመሰረቱ ክሶች አሁን ላይ ባለው ምርጫ በሚሳተፉት የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ ስለ ምርጫው በሚዘግቡ የፕሬስ ድርጅቶችን ላይ አሉታዊ በሆነ መልኩ (በሚያቀርቡት ነገር) እንዲቆጠቡ ፍርሃትን ሊፈጥር ይችላል፡፡

ሁለተኛው፣ የሕጉን ይዘት ስናይ፣ በተለይ አንቀፅ 6 ምንድን ነው የሚለው፡- ‹‹አንድ የፕሬስ ድርጅት (ብሮድካስት የሚያደርግ ድርጅት የሚያሰራጨው መረጃ በሚያደምጠው ማኅበረሰብ ላይ የሽብር ተግባር በቀጥታም ሆነ፤ በተዘዋዋሪ ሽብር እንዲፈፅሙ የሚገፋፋ ከሆነ ያስቀጣል›› ይላል፡፡ እንደኔ ማንኛውም የምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከዚህ ሊዘሉ አይችሉም! የፈለግከውን ነገር ወደ እዚህ ነገር ማስገባት ትችላለህ፡፡ ራስን በራስም ሳንሱር እንድታደርግም ያስገድዳል እላለሁ፡፡ ይህ ደግሞ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል፡፡ ሚዲያው መረጃውን ከማሰራጨቱ በፊት ስለ መረጃው ይዘት እና ስለ አድማጭ/ አንባቢዎች ማወቅ እንዳለብህ ያስገድዳል፡፡ ከምርጫ ጋር ስናያቸው ይህም አሉታዊ ተፅዕኖ አለው፡፡ ህዝቡ እንዲመርጥ ደግሞ የገዢውንም ሆነ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን ጠንካራ እና ደካማ ጐን ምንድን ነው) የሚለውን በሚፈልገው መልኩ ለመራጩ ህዝብ እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡ ይህ የግል አቋሜ ነው፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ ህዝቡ የሚመርጠውን አካል ጠቀሜታ እንዳያይ ያደርገዋል፡፡

አንቀፅ 29ኝ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ሙሉ በሙሉ ልቅ አያደርገውም! ወይንም ፍጹማዊ አያደርገውም! በተወሰነ ይገድበዋል፡፡ ይህን ደግሞ በአዋጅ ስትመለከተው በጣም ሰፍቷል፡፡ በመርህ ደረጃ ክልከላ በጠባቡ መታየት ነው ያለበት፡፡አንቀጽ 29 ደግሞ በነጻ የመናገር መብትን አስፍቷል፡፡ የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጁ ደግሞ የፈለገከውን ወደ እዚያ ውስጥ እንድትከት ይረዳል፡፡

የፕሬስ አዋጅ አንቀፅ 43/7፡- ላይ ‹‹መገናኛ ብዙሃን የሚያወጡት የሕግ አውጭ፣ የሕግ ተርጓሚ፣ የሕግ አስፈጻሚን ስም የሚያጠፉ ከሆነ እነሱ እንኳን ‹‹ስማችን ጠፋ›› ብለው ባያመለከቱም መንግሥት ይከሳቸዋል›› ይላል፡፡ ካለ ከሳሽ (እነሱ ባያመለክቱም የሚያስተላልፈው የሚድያ አካል ይከሰሳል)፡፡ ስለዚህ ድርጅቶቹን ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል፡፡ ነገር ግን በግለሰብ ደረጃ ስም ማጥፋት ከተፈጸመ ስሙ እንዲጠፋ የተደረገው ሰው ሊያመለክት ይገባል ይላል፡፡ሚዲያን በተመለከተ፣ የህዝብ መረጃ የማግኘት መብት ታይቶ ሊስተካከል ይገባው ነበር፡፡ ቅጣቱን በተመለከተም እስከ መቶ ሺህ ብር እስራት ያስከትላል፡፡ ይህ ደግሞ ትንሽ ይብዳል - በግሌ!

የበጐ አድራጐትን 10 በ 90 አዋጅ በተመለከተ፣ የውጭ ድርጅቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያደርጉት የፓለቲካ እንቅስቃሴዎች አይሳተፍም፡፡ ይህ ማለት ማስተማርም ሆነ እንዲመርጡ ማድረግ አይችሉም፡፡

ሁለተኛው፣ ደግሞ ሀገር ውስጥ ያሉት መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ይህም ሁለት ተፅዕኖዎች አሉት፡- አንደኛው፣ የሚያደርጉት ቅስቀሳና ማስተማር ዴሞክራሲያችንን ያሳድግልን ነበር፡፡እኔ ግን መንግሥት እንዳይሳተፉ ከማድረግ ይልቅ ሌላ አይነት አማራጮችን ማየት ይችል ነበር፡፡ ጣልቃ በመግባት መቆጣጠር ይችል ነበር፡፡ ሁለተኛው፣ በራሳቸው ገንዘብ ነው የሚንቀሳቀሱት፡፡ስለዚህ አስገብቶ መቆጣጠሩ የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ሀገር በቀሎቹ ግን መሳተፍ ይችላሉ፤ ነገር ግን 10% ነው ማስገባት የሚችሉት የሚለው፡፡ የሀገራችን ህዝብ በእንደዚህ አይነት ነገር የመሳተፍ አቅሙም ደካማ ነው፡፡ ስለዚህ ገቢያቸውን ይጎዳዋል፡፡ ይህም በሥራቸው ላይ የፋይናንስ ችግር ያስከትላል፡፡ የፋይናንስ ችግር ደግሞ በሥራቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ያ ማለት ህዝቡን ቢያስተምሩትና ቢያነቃቁት ኖሮ ህዝቡ መብቱን በደንብ ይጠቀም ነበር፡፡

# ምርጫ 2007

ይህ አምድ እናንተ አንባቢያንን ጨምሮ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በምርጫ 2007 ጉዳይ ላይ የሚወያዩበት ነፃ መድረክ ነው።

## ኤልሳቤጥ ወሰኔ

የፀረ ሽብር፣ የበጎ አድራጎትና የፕሬስ አዋጆች ላይ ተቀናቃኞችን ለማጥቃት የሚያስችሉና በቀላሉ የሚጠመዘዙ አንቀጾችን አካተዋል። እነዚህ አንቀጾችም ሥርዓቱ በሀገር ደህንነት ስም በሕግ እንዲገዛ የሚመቹ፣ ለዴሞክራሲያዊ ግንባታና ለምርጫ የማይመቹ በመሆናቸው ለቀጣዩ ምርጫም ላይም አሉታዊ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

## አሁን ያለው የፍትህ ሥርዓት ከምርጫው በፊትና በኋላ ሊኖሩ የሚችሉ ቅሬታዎችን በነጻነት የመዳኘት አቅም አላቸው?

### ተማም አባቡልጉ

የፍትሕ አካላት የሚለኩት በሌላ ጉዳይ በሚደረግ ምርጫ ብቻ አይደለም፤ የሚቋቋሙ ናቸው። የሚለኩትም በዚህ እንጂ በሌላ አይደለም። ራሳቸው የሚመረጡ መሆን በመቻላቸው ነው። ፍትሕ በራሱ አንድ መርሕ ነው። ፍትሕ የህዝብን ሰላምና መረጋጋት በማረጋገጥ ነው የሚታየው።ምርጫ በፍትህ ውስጥ አንዱ ጉዳይ ነው።ምርጫ ለሕጉ አንድ ነገር ነው። ሕግ ግቡና አካሄዱ ሊታይ ይገባል። የሕግ አካሄዱ ትክክል ካልሆነ ግቡ ምርጥ ሊሆን አይችልም። ሰው ተገርፎ መረጃ በመስጠቱ ትክክለኛ ፍትህ አያገኝም። የሕጉ ሂደቱ ውጤቱ ነው። አፈጻጸሙ እና አካሄዱ ትክክል ከሆነ ፍትሑም ትክክል ይሆናል።

### ፀጋዬ ደምሴ

ምርጫውን በተመለከተ ‹‹የፍ/ቤቶችን ነጻነት ገለልተኛነታቸው ምን ያህል ነው)´ የሚለውን ስናይ ነጻ የሚያደርጋቸው የሕግ መዋቅር አለ። በዚህ ሕግ መሰረት፣ ሁሉም ዳኛ ፍርድ እየሰጠ ነው ማለት አይደለም። የራሳቸውን መብት አሳልፈው ሊሰጡ የሚችሉ ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን መብታቸውን መጠቀምና ከማንም ተፅዕኖ ነጻ መሆናቸውን ማሳየት ይችላሉ። በተለይ የፀረ-ሽብርተኛነት አዋጁ ሰፊ ነው። የዳኛውን ውሳኔ ሕገ-መንግሥትን የሚጋፋ ከሆነ በህገ-መንግሥት ተርጓሚ አካል ይታያል።ይህን ስንል የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሥልጣኑ አለው። የዜጐች ሕገ-መንግሥታዊ ሥልጣንን ገዥው መንግሥትም ሆነ የፍትህ አካላት ሕገ-መንግሥቱን እንዳይጥሱ ዋስትናቸው ነው። እዚህ ጋር ስትመጣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስትገባ የትምህርት ብቁነት መስፈርት የለውም። ዝም ብለህ ነው የምትገባው። በክልል ምክር ቤት ነው የሚመረጡት። ያ ማለት ያልተማሩም ሊሆኑ ይችላሉ። ያ ደግሞ እንደዚህ አይነት ቴክኒካል የሆነ ነገሮችን አይቶ ‹‹ሕገ-መንግሥቱን ጥሷል) አልጣሰም)›› ብሎ የማለት አቅሙ የላቸውም። ሊኖራቸውም አይችልም። ግን የሕግ አማካሪዎች አሏቸው። እነሱ ያግዟቸዋል ይባላል። የተለያዩ የዓለም ሀገራትን ልምድ ስናይ የጣሊያን፣ የጀርመን፣ የኦስትሪያና የደቡብ አፍሪካ በቦታው የሚተኩት በጣም ምሁራን ናቸው። ወደኢትዮጵያ ስንመጣ ፖለቲካ እንጂ በእውቀቱ አይደለም። ይህም ከምርጫው በፊትና በኃላ ‹‹አቤት›› የሚባልበት ቦታ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው። ይህ ደግሞ ከላይ በጠቀስነው ምክንያቶች ጥርጣሬን ያስነሳል።

### ኤልሳቤጥ ወሰኔ

አሁን ያለው የፍትሕ ሥርዓት ከሙያ ይልቅ ታማኝነት፣ ከሕግ ይልቅ ፖለቲካዊ ይዘቱ ያመዘነ በመሆኑ በዚሁ ከቀጠለ ‹‹ፍትሓዊ፣ ነጻ ምርጫ ለማድረግ ያስችላል›› የሚል እምነት የለኝም። በተለይ ለገዥው ፓርቲ ስጋት የሆኑ ተቃዋሚና ሌሎች አካላትን ከስሶ ፖለቲካዊ ውሳኔን ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኘው ፍርድ ቤት ከምርጫ በፊትም ሆነ ከምርጫ በኋላ በገለልተኝነት ይሰራል የሚል እምነት የለኝም። በመሆኑም ከምርጫው በፊትም ሆነ በኋላ የሚነሱ ቅሬታዎችን በነጻነት ይዳኛል የሚል እምነት የለኝም። ከዚህ ይልቅ የገዥውን ፓርቲ ጥቅምና ሥልጣን ለማስጠበቅ በመሳሪያነት የሚያገለግልበት አጋጣሚ ሰፊ ነው።

## ከምርጫው በፊትና በኋላ መስተካከል አለባቸው የሚሏቸው የሕግ፣ ወይም አዋጅ ወይም መመሪያ አለ?

### ተማም አባቡልጉ

‹‹መሻሻል አለባቸው የምትላቸው ሕጎች›› ላልከኝ፣ ሁሉም የሕዝብ እና የሀገር የሆኑትንና የእነዚህ መሆን የሚገባቸውን ለመንግሥት የሰጡ ሕጐች ሁሉ መሻሻል ብቻ ሳይሆን ይህንን የፈጠረውም አስተሳሰብና ሐሳብ ሙሉ በሙሉ መለወጥ ይኖርበታል፤ ለሁሌም!

### ፀጋዬ ደምሴ

ፕሬስን የሚገድቡት ሕጎች በተወሰነ መልኩ ትንሽ ጠበብ ቢሉ የተሻለ ነው። ሀገሪቱ ላይ የሽብር ተግባር የማፈፅሙ ድርጅቶች ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንድ በትክክል የሚሰሩ ሚዲያዎች ይኖራሉ።ይህን ሚዛናዊ ለማድረግ በፕሬስ አዋጁ አንቀፅ 43 እና የፀረ-ሽብርተኛነት አንቀፅ 6 በመጠኑም ቢሆን የሚዲያ ሰዎችን በተመለከተ ለቀቅ ቢደረግ የሚል አቋም አለኝ።

መያዶችን በተመለከተ መንግሥት ራሱ 90% ከውጭ እንዲያስገቡ ፈቅዶ ነገር ግን እዚህ ቢቆጣጠር የተሻለ ነው። ገንዘቡ ቢገባ ለሀገር ዕድገት ጠቃሚ ነው። ፀረ-ሽብር አዋጅ አንቀፅ 6 አሁን ካለው የፍ/ቤትም ሆነ የሰዎች አቅም በጣም ልጥጥ ያለ ስለሆነ በተለይ ከሚዲያ ጋር በተያያዘ ያለው ትንሽ ጠበብ ቢል ጥሩ ነው። አዋጁ የዳኛውን የግል ብቃት እስከመጠየቅ ይሄዳል።በፓርላማ የሚወጣው ሕግ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የሚዲያ ድርጅቶችን ለማገዝ ትንሽ ጠበብ ቢል የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ።

### ኤልሳቤጥ ወሰኔ

የፀረ-ሽብርተኛነት፣ የበጎ አድራጎትና የፕሬስ አዋጆች በያዟቸው አንቀጾችም ሆነ በአተገባበራቸው ሕገ-መንግሥቱን (ከእነ ድክመቱም ቢሆን) ሲጻረሩ ይታያል። የጸረ ሽብርተኛነት አዋጁ በሕገ-መንግሥቱ ተረጋግጧል የተባለውን የመደራጀት፣ የመጻፍና የእምነት ነጻነት መብት በሽብርተኛነት ይፈርጃል። የፕሬስ ሕጉ፣ በሕገ-መንግሥቱ የተከለከለውን ቅድመ ምርመራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይፈቅዳል። የበጎ አድራጎት አዋጁም በሕገ-መንግሥቱ ተፈቅደዋል የሚባሉ ዴሞክራሲያዊ፣ የባህልና የኢኮኖሚ መብትን የሚያስጠብቁ ተቋማት እንዳይፈጠሩ የሚከለክል አዋጅ ነው። በመሆኑም ከሕገ-መንግሥቱ ቀድሞ እነዚህ አዋጆች ቢቻል ቢሰረዙ፣ ካልተቻለ ደግሞ ቢሻሻሉ ለምርጫው የራሳቸው አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

በእርግጥ አዋጆቹ ካካተቷቸው አንቀጾችም ባልተናነሰ አተገባበራቸው ለዴሞክራሲ፣ በተለይም ለምርጫ ሂደቱ እንቅፋት በመሆናቸው ገዥው ፓርቲ በሕግ ከመግዛት ይልቅ በሕግ የበላይነት እንዲያምን ማድረግም ለምርጫው ቀላል የማይባል ሚና ይኖረዋል። በተለይ ሕገ- መንግሥቱን እስከነድክመቱም ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ተቀብሎ ቢተገብር በምርጫው ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወት ይችላል። ምንም እንኳ በዚህ አጭር ጊዜ ሕገ-መንግሥቱን ማሻሻል ባይቻልም በቀጣይነት ሕገ-መንግሥቱ እንዲሻሻል ጥረት ቢደረግ በምርጫ ሥርዓትና በዴሞክራሲ ግንባታ ቀላል የማይባል ለውጥ ይኖራል።

## ከምርጫው በፊትና በኋላ መስተካከል አለባቸው የሚሏቸው የሕግ፣ ወይም አዋጅ ወይም መመሪያ አለ?

### ተማም አባቡልጉ

‹‹መሻሻል አለባቸው የምትላቸው ሕጎች›› ላልከኝ፣ ሁሉም የሕዝብ እና የሀገር የሆኑትንና የእነዚህ መሆን የሚገባቸውን ለመንግሥት የሰጡ ሕጐች ሁሉ መሻሻል ብቻ ሳይሆን ይህንን የፈጠረውም አስተሳሰብና ሐሳብ ሙሉ በሙሉ መለወጥ ይኖርበታል፤ ለሁሌም!

### ፀጋዬ ደምሴ

ፕሬስን የሚገድቡት ሕጎች በተወሰነ መልኩ ትንሽ ጠበብ ቢሉ የተሻለ ነው። ሀገሪቱ ላይ የሽብር ተግባር የማፈፅሙ ድርጅቶች ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንድ በትክክል የሚሰሩ ሚዲያዎች ይኖራሉ።ይህን ሚዛናዊ ለማድረግ በፕሬስ አዋጁ አንቀፅ 43 እና የፀረ-ሽብርተኛነት አንቀፅ 6 በመጠኑም ቢሆን የሚዲያ ሰዎችን በተመለከተ ለቀቅ ቢደረግ የሚል አቋም አለኝ።

መያዶችን በተመለከተ መንግሥት ራሱ 90% ከውጭ እንዲያስገቡ ፈቅዶ ነገር ግን እዚህ ቢቆጣጠር የተሻለ ነው። ገንዘቡ ቢገባ ለሀገር ዕድገት ጠቃሚ ነው። ፀረ-ሽብር አዋጅ አንቀፅ 6 አሁን ካለው የፍ/ቤትም ሆነ የሰዎች አቅም በጣም ልጥጥ ያለ ስለሆነ በተለይ ከሚዲያ ጋር በተያያዘ ያለው ትንሽ ጠበብ ቢል ጥሩ ነው። አዋጁ የዳኛውን የግል ብቃት እስከመጠየቅ ይሄዳል። በፓርላማ የሚወጣው ሕግ የፖለቲካ ድርጅቶችንና የሚዲያ ድርጅቶችን ለማገዝ ትንሽ ጠበብ ቢል የተሻለ ነው ብዬ አስባለሁ።

### ኤልሳቤጥ ወሰኔ

የፀረ-ሽብርተኛነት፣ የበጎ አድራጎትና የፕሬስ አዋጆች በያዟቸው አንቀጾችም ሆነ በአተገባበራቸው ሕገ-መንግሥቱን (ከእነ ድክመቱም ቢሆን) ሲጻረሩ ይታያል። የጸረ ሽብርተኛነት አዋጁ በሕገ-መንግሥቱ ተረጋግጧል የተባለውን የመደራጀት፣ የመጻፍና የእምነት ነጻነት መብት በሽብርተኛነት ይፈርጃል። የፕሬስ ሕጉ፣ በሕገ-መንግሥቱ የተከለከለውን ቅድመ ምርመራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይፈቅዳል። የበጎ አድራጎት አዋጁም በሕገ-መንግሥቱ ተፈቅደዋል የሚባሉ ዴሞክራሲያዊ፣ የባህልና የኢኮኖሚ መብትን የሚያስጠብቁ ተቋማት እንዳይፈጠሩ የሚከለክል አዋጅ ነው። በመሆኑም ከሕገ-መንግሥቱ ቀድሞ እነዚህ አዋጆች ቢቻል ቢሰረዙ፣ ካልተቻለ ደግሞ ቢሻሻሉ ለምርጫው የራሳቸው አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

በእርግጥ አዋጆቹ ካካተቷቸው አንቀጾችም ባልተናነሰ አተገባበራቸው ለዴሞክራሲ፣ በተለይም ለምርጫ ሂደቱ እንቅፋት በመሆናቸው ገዥው ፓርቲ በሕግ ከመግዛት ይልቅ በሕግ የበላይነት እንዲያምን ማድረግም ለምርጫው ቀላል የማይባል ሚና ይኖረዋል። በተለይ ሕገ- መንግሥቱን እስከነድክመቱም ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶችን ተቀብሎ ቢተገብር በምርጫው ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወት ይችላል። ምንም እንኳ በዚህ አጭር ጊዜ ሕገ-መንግሥቱን ማሻሻል ባይቻልም በቀጣይነት ሕገ-መንግሥቱ እንዲሻሻል ጥረት ቢደረግ በምርጫ ሥርዓትና በዴሞክራሲ ግንባታ ቀላል የማይባል ለውጥ ይኖራል።

## ምርጫውን አስመልክቶ ለሕዝብ፣ ለመንግሥት፣ ለተቃዋሚዎች፣ ለሚዲያና ለሕግ ባለሙዎች የሚያስተላለፉት መልዕክት?

### ተማም አባቡልጉ

ለመንግሥት፣ ለተቃዋሚዎች፣ ለሕግ ባለሙያዎችና ለሚዲያ የማስተላልፈው መልዕክት፤ ‹‹ሕዝቡ ስላለ ነው ያላችሁት›› የሚል ሲሆን ለሕዝቡ የማስተላልፈው መልዕክት ደግሞ ‹‹ሁሉም ያለው በአንተ፣ ስላንተ፣ ካንተና ላንተ ብሎ መሆኑን ተረድተሃል። ‹‹ከእኔ ወደያ ላሳር›› ማለት እንደምትችልስ ተረድተሃልን? የሚል ነው። ሕዝብ አይሆንም ሲል ከህዝብ ውጪ ምንም አይሆንም። ሕዝብ ሁሉም የእሱ መሆኑን ማወቅ አለበት። ሕዝብ ከሌለ መንግሥት፣ ተቃዋሚ፣ ጋዜጠኛ፣ የህግ ባለሙያ … ወዘተ. የለንም። የእኛ ትርጉም ህዝብ ነው።

### ፀጋዬ ደምሴ

የምርጫ ዓመት ሲሆን መንግሥት ሀሳቦች በነጻነት እንዲንሸራሸሩ ከዓለም ዓቀፍ ፍልስፍና አንጻር ትንሽ ለቀቅ ቢያደርግና ሰዎች የመምረጥ መብታቸውን እንዲጠቀሙ ቢያደርግ ጥሩ ነው።

ተቃዋሚዎች ደግሞ፣ ሁኔታው ቢከብድም በሀገራቸው አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣት ሕጋዊ በሆነ መልኩ ኅብረተሰቡ ስለ ማንነታቸው በግልፅ እንዲያውቅ ዴሞክራሲያዊ ሆነው ቢንቀሳቀሱ ጥሩ ነው እላለሁ።

ኅብረተሰቡ በራሱ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ያለማንም ተፅዕኖ መብቱን የሚያስከብርለትን በመምረጥና ግጭቶችን ገለል በማድረግ መብታቸውን ተጠቅመው እንዲመርጡ መልዕክት አስተላልፋለሁ።

ፕሬሶች ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ምንም ተፅዕኖ ቢኖርም መረጃን ከማድረስ አንጻር እንደ ዜጋ ትልቅ ሚና ይጠበቅባቸዋል።

ፍትህ አካላት በበኩላቸው፣ አቃቤያን ህጐች ያሉን ትንሽ ውስብስብ ስለሆኑ በቂ ማስረጃዎችን አይተው ክሰ እንዲመሰርቱ፣ ዳኞችም በትክክለኛ ዳኝነት የዜጐችን መብት ማስጠበቅ አለባቸው።

### ኤልሳቤት ወሰኔ

ለመንግስት፡- ተቋማትን ነጻ በማድረግ፣ የመግዣ ህጎችን በማሻሻልና ሕገ-መንግሥቱን ከነድክመቱም ቢሆን በማክበር ምርጫው ፍትሓዊ እንዲሆን መጣር አለበት። በእነዚህ አፋኝ ህጎች በመጠምዘዝ፣ የታሰሩት ዜጎችን በመፍታት፣ እስከአሁን የተፈጸሙ ወንጀሎችን የሚያጣራ ኮሚሽን በማቋቋምና ከተቀናቃኞች ጋር በመነጋገር ብሄራዊ እርቅ መፍጠር አለበት። ፍርድ ቤት፣ ሚዲያ፣ ወታደርና ደህንነት ከአንድ ፓርቲ ጥቅም ይልቅ ለሕግ ተገዥ ሆነው ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ ተቋማዊ ነጻነት መፍቀድና ማረጋገጥ አለበት።

ተቃዋሚዎች በመካከላቸው ያለባቸውን ልዩነት ፈትተው ኢህአዴግ ላይ ጫና ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አፋኝ አዋጆች እንዲሰረዙ አሊያም እንዲሻሻሉ፣ የውጭ መንግሥታት፣ ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ ተቋማትን ተጠቅመው በገዥው ፓርቲ ላይ ጫና ማድረግና በህዝብ መካከል ክፍፍል እንዳይኖር መሥራት አለባቸው።

ህዝቡ ለሀገር፣ ለህዝብና ለራሱ ይጠቅመኛል የሚለውን አካል በገንዘብ፣ በእውቀትና በቻለው አቅም መርዳት፣ ከምንም በላይ ራስን ነጻ ማውጣት ይቀድማልና የራሱን መብቶች እንዲከበሩ በየደረጃው ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል።

የሚዲያ ባለሙያዎች፣ የተከለከሉት ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ሊረጋገጥ የሚችለው ሌሎች መብቶች ሲረጋገጡ በመሆኑ ሌሎች መብቶች እንዲረጋገጡ፣ የህዝብ ጩኸት እንዲሰማ ድምጽ ለሌላቸው ድምጽ ለመሆን መጣር አለባቸው።

የፍትህ አካላት ደግሞ፣ ፍትሕ ለአንድ ሀገር ዴሞክራሲያዊ ግንባታ በተለይም ለምርጫ ሂደት ትልቅ ሚና ይጫወታል። ይህ የሚሆነው ግን እያንዳንዱ የፍትሕ ተቋማት፣ እንዲሁም በእነዚህ የፍትሕ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ኢትዮጵያውያን የሙያ ሥነ-ምግባራቸውን፣ ቀጣዩን የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ አስበው ሲሰሩ በመሆኑ ከፖለቲካ ይልቅ ህጋዊ ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ መጣር አለባቸው።

# <<የእናቶች ወግና ሁለቱ ሰልፎች>>



ምስክር አወል

እናት እንደልቤ እንደወትሮው ሁሉ ሌሊቱን በሃሳብ ሲሸበሩና ሲጨነቁ ካደሩ በኃላ ረፈድፈድ ሲል በአካባቢው ወደሚገኘው ሸማቾች ማኅበር አመሩ፡፡ ከዘይትና ከስኳር መጥፋት በተጨማሪም ያገኟትን የዕለት ጉርስ ለቤተሰቡ የሚያበስሉበት መብራት በተደጋጋሚ እየጠፋ በቤት ውስጥ የመኖር ህልውና ላይ የተደቀነባቸውን አደጋ እያብሰለሰሉ ሸማቾች ማኅበር ደረሱ፡፡

ልክ እንደደረሱ ሁለት ረዣዥም ሰልፎችን በቅርብ ርቀት ተመለከቱ…… እናት እንደልቤ‹‹የትኛው ነው የዘይቱ ሰልፍ)›› ሲሉ ቁጣም ንጭንጭም የተቀላቀለበትን ጥያቄ ለተሰለፈው ህዝብ አቀረቡ፡፡ በሁለቱም መስመር ላይ ከተሰለፉት ሰዎች መካከል ብዛት ያላቸው እናቶች ሲሆኑ አልፎ አልፎ ወጣቶችም ይታያሉ፡፡ ‹‹ይሄኛው ሰልፍ የምርጫ ካርድ ለመውሰድ ነው፤ ያኛው ሰልፍ ደግሞ የዘይት ነው›› አሉ ሌላኛዋ እናት በምሬት፡፡ ‹‹ድንቄም ምርጫ! መምረጤ ከሰልፍ ላያድነኝ ለምንድን ነው የምመርጠው)›› አሉ እናት እንደልቤ የልባቸውን አውጥተው፡፡

ሰልፉን የሚያስተባብሩት የቀበሌው ሰዎች በንዴት! እናቶች ደግሞ በፍርሃትዞረው አፈጠጡባቸው፡፡ ‹‹አንቱ ሴትዮ ምን አለ የሚናገሩትን ቢያውቁት፤ ከመንግሥት ጋር ተጣልተው እስር ቤት እንዳይገቡ፤ ለልጆችዎ ሲሉ እባኮዎትን ዝም በሉ!›› አሏቸው፡፡ እናት አለሚቱ ፍርሃት በተቀላቀለበት የሹክሹኩታ ድምፅ፡፡ ‹‹አንተ ልጅ ወረፋየ ከአንተ ቀጥሎ ነው፡፡ ፀሐዩን አልቻልኩትም ከቶ በስንቱ ልቃጠል፡፡ ደሞ እዚህም መጥቼ በፀሐይ ልንደድ)›› እያሉ እያጉመተመቱ ከጽዱ ሥር ካለው ሳር ቁጭ አሉ፡፡

እናት አለሚቱ ብዙ ከመቆማቸው የተነሳ ተስፋ በመቁረጣቸው ‹‹ወ/ሮ ማዘንጊያ ተራዬ ሲደርስ እመጣለሁ ትንሽ አረፍ ልበል›› ብለው ወደ ወ/ሮ እንደልቤ አቅጣጫ ሲያመሩ ምርጫ አስፈጻሚ ተብሎ የተመደበ የቀበሌው ሰው ‹‹ሰልፉን አታፍርሱ ቶሎ ቶሎ ነው ምዝገባው ይደርስሻል›› የሚል ቁጣ አዘል መልዕክት ሰጣቸው፡፡ እናት አለሚቱም በማሳዘንና በፍቅር አይን ‹‹ እባክህን የእኔ ልጅ ከጠዋት ጀምሬ ቁሜ ነው ያረፈድኩት›› እግሬንም አመመኝ ፀሐዩም አቃጠለኝ ምናለ ተራዬ ሲደርስ ብመጣ)›› አሉት በተማጽኖ ልጁም ተማጽኗቸው ገባውና ፈቀደላቸው እናት አለሚቱም ከእንደልቤ ጎን ቁጭ አሉና ‹‹እህህህህህህህህ…… አይይ ወገቤን አሁንስ እርጅናውን አየተጫጨነኝ ነው መሰለኝ መነሳትም መቆምም አልቻልኩም ›› አሉ፡፡ ‹‹ ምን እርጅና ነው ብለሁ ነው! ለዚሁ ጉልበት ለሚሰበር ዘይት አይደል ይሄ ሁሉ ሰልፍ ይብላኝ ለዚህ ትውልድ እንጂ እኛስ በደህናው ጊዜ ቅቤውን ማሩን፤ ማኛ ፤ጤፉን ፤እንደልብ በልተነዋል፡፡ ይኸው ለልጄ ግን ወጥ ላይ ጠብ የማደርግለት ዘይት ታጥቷል›› አሉ በምጸት ንግግር ‹‹ ግን እርሶ እንዴት የታደሉ ሰው ኖት) ሲናገሩ አንዳችም ፍርሃት አይታይቦትም እኮ›› አሉ እናት አለሚቱ በአግራሞት የእንደልቤን ፊት እየተመለከቱ ‹‹እንዴት ደፋር አልሆንም ስንቴ ልቤ አሯል መሰለሽ ለእኔ የጃንሆይና የደርጉ ጊዜ ይሻለኝ ነበር›› አለች እንደልቤ ወደኃላ ያለፈውን ጊዜ ለማስታወስ እየሞከረች ‹‹እዲያ ከደርግስ ይሄው ይሻላል መሰለኝ አንቺው›› አለች እናት አለሚቱ ‹‹አንቺ ደግሞ እንዲያው ዝም ብለሽ ነው በደርጉና በጃንሆይ ጊዜ እንደዚህ ሰልፍ ነበረ እንዴ) እንደፈለግን አልነበረ ስንዴና ስኳር ስንወስድ የነበረው) ዘይትም ቢሆን እድሜ ለሃገሬ ገበሬ እንጂ መቼ ወተትና ቅቤው፤ ንጉና ሰሊጡ ከማሳ ጠፍቶ ነው፡፡ እንዲህ እንደአሁን ተሰልፌ ፀሐይ ቅንጥ ቅንጤን የሚያዞረኝ በይ)››

‹‹ እሱስ ልክ ነሽ የዛኔ ሁሉም ነገር ጤና ነበር ይኸው ዘይቱንም እንውሰደው እንጂ ጉልበት የሚሰብርና ለበሽታ የሚዳርግ ነው መድረሻ ማጣትና ድህነት ነው እንጂ ቅቤውንማ አሁንም እየበሉት ውሃ በመሰለ መኪና እየተንፈላሰሱ ቤተ-መንግሥት የመሰለ ቤት ሰርተው የንጉስ ኑኖ የሚኖሩ አሉ›› አሉ እናት አለሚቱ በሰፈራቸው ደልቷቸው የሚኖሩትን ባለወቅት ሰዎችም በዓይነ ህሊና እየሳለች፡፡እኔስ ትውልዴም እድገቴም ውቤ በረሃ አካባቢ ነበር ቤትሽ ለልማት ተፈልጓል ተብዬ ነው፡፡ ወደሰፈራችሁ እስከ ልጆቼ ጥገኝነት የጠየኩት!›› አሉ እንደልቤ ደስ በሚል እናታዊ ፈገግታ፡፡ ነገር ግን ፈገግታቸው በጥገኝነት መጠጋት የሚለው ቃል ሃፍረት ዘራባቸውና ፈገግታቸውን ወዲያው ነጠቃቸው፡፡

‹‹እሱማ ታዲያ ብዙ የለመዱ ነው ማለት ነው) አይ ውቤ በረሃ ስንት እንዳልተባለበት እንዳልተጠጣበት ዋ! ጊዜ ድሮ የመኳንንቱ ሁሉ መዝናኛ ነበር እንደ አሁኑ ሃብታምና ባለሥልጣን ቦሌ መዋል ሳይጀምር አንቱዬ ዋ! አይ ጊዜ ስንቱን ያሳየኛል)›› አሉ እናት አለሚቱ ‹‹ኑ ሰልፉ እየተጠጋ ነው ተነሱና ተጠጉ›› የሚል የወጣቱ ድምፅ ጨዋታቸውን ለአፍታ አኮላሸው፡፡ እንጠጋ እንጂ አንቱ ከዘይቱ ኖት እስኪ እኔም ካልተመዘገባችሁ አትመርጡም እየተባልን አይደል ልመዝገብና ደግሞ ወደ ጉልቴ ሄጄ ትንሽ ገበያ ቢቀናኝ አሉ ሃዘን በተቀላቀለው ቅላጼ ‹‹ምን የሚመረጥ አለ ብለሽ ነው፡፡ ትላንት ማታ ከዩንበርስቲ ተመርቆ ሥራ ፈቶ ቤት የሚውለው ልጄ ማታ 3 ሰዓት ሲሆን የአማሪካ ራድዮ ከፍቶ ይከታተላል፡፡ ታድያ መንግሥት ሆኖ ለመግዛት የሚመጡትን አስመረጭ ቦርድ አግዳለሁ እያለ ሲያወራ ነበር፡፡ አቤት አነጋገር አቤት ለዛ እንዴት ነው ፖለቲካውን የሚያብጠረጥሩት በይ ) ደግሞ በስልክ እያገናኙ ያሟግቷቸዋል ምን አለ የእኛ ሃገር ራዲዮኖች እንደዛ ቢሆኑ በይ ከጠዋት እስከ ማታ ለዛ የሌለው ዘፈን ሲያዘፍኑና ሲለፈልፉ ከሚውሉ ›› አሉ እንደልቤ ፍፁም ሚዛናዊ በሆነ ንፁህ ህሊና እነሱስ በመጡ ግን ከዘይት ሰልፍ ፤ከታክሲ ሰልፍ ያድኑናል) q$ም ነገር አላቸው)

q$M ngRS x§cW መሰል መንግሥትና ያ አስመራጭ የሚባለው ሊበታትኗቸው ነው እንጂ ለሃገሬ ህዝብ እሰራለሁ እያሉ ሲያወሩ ሰምቻቸው ነበር ግን ምን ዋጋ አለው በየት በኩል ተሩጦ ››፡፡

‹ቁጭ ብለው ያወራሉ እንዴ ) አለ ወጣቱ የቀበሌ ሰው በይ እስኪ እንነሳና አንቺም ተመዝገቢ እኔም ዘይቴን ይዤ እልሂድ አሉ ሁለቱም ከተቀመጡበት እየተነሱ ከቀሚሳቸው ጋር የተጣበቁትን ሳሮች እያባረሩ በይ ደህና ዋይ! ደህና ዋይ ! ተባብለው ተለያዩ እናት አለሚቱ ወደ ምርጫ መመዝገቢያ..እናት እንደልቤ ደግሞ ወደ ዘይቱ ሰልፍ.. እንደልቤም ከዘይቱ መክፈያ ጋር ሲደርሱ በደረታቸው የወሸቁትን ቦርሳቸውን አውጥተው ብር ሊክፍሉ ሲሉ ‹‹ መታወቂያ ›› አለች አይዷ እንደ እቶን እሳት የሚጋረፍ ገንዘብ ተቀባይ፡፡

እናት እንደልቤ ቢፈልጉ ቢፈልጉ መታወቂያ ከየት ይምጣ ‹‹የእኔ ልጅ አልያዝኩትም ረስቼው መጣሁ መሰለኝ ….. ውይ አስታወስኩ ልጄ ትላንትና ፊልም ሲከራይ አስይዞት ነው አስታወስኩ! አስታወስኩ! አሉ አንገታቸውን ደፋ ቀና እያደረጉ ‹‹እማማ አሁን መታወቂያ ነው የጠየኮት ካልሆነ ይልቀቁ ለተረኛ ›› አለቻቸው ገንዘብ ተቀባይዋ ‹‹እረ ተይ ልጄ ተይ እሺ አሁን ልውሰድና በኃላ አመጣለሁ እባክሽ ይህን ሁሉ ሰዓት እዚህ ተጎልቼ ባዶ እጄን አልመለስ እረ ተይ ››ሲሉ ለመኑ፡፡

ነገር ግን ገንዘብ ተቀባይዋ በሃሳቧ ፀናች እናት እንደልቤም ተስፋ በመቁረጥ ስሜት ነጠላቸውን እያጣፉ ክፍሉን ለቀው ወጡ ‹‹አይምረጡኝ ! ልቤ እንዳረረ እንደው ማን ባየልኝ ተሰልፌ የምመርጠው ተሰልፌ ዘይት እንድገዛ ነው? አሁን እኮ ማን ይሙት በምርጫው ምዝገባው ሰልፍ ብሆን ዝም ብለው ይመዘግቡኝ ነበር! አቃጣሪ ሁላ የት ሂጄ ልኑር?›› እያሉ እያጉተመተሙ ብቻቸውን የግቢውን ቅጥር ለቀው ወጡ፡፡

ከበሩ እንደወጡ ዋናውን የኮብልስተን መንገድ ይዘው ቁልቁል ሲጓዙ ተፈንቅላ የወጣች አንድት ኮብልስቶን ድንጋይ እግራቸውን መትታ መሬት ላይ ዘፍፍፍፍፍ አደረገቻቸው፡፡ ሰው አየኝ አላየኝ በሚል ሃፍረት ደመ ነፍሳቸውን አፈፍ ብለው ተነስተው ዙሪያ ገባውን ቃኙት ቃኙት አድርገው ‹‹እህህህህህ ኤድያ ይህ መንገድ ነው? የእንቧይ ካብ?›› ብለው በራሳቸው ፈገግ ብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡

ቸር እንሰንብት!

# የሬዲዮ ፋና ቅሌት (ትዝብት)

በሪሁን አዳነ

ሬዲዮ ፋና ባለፈው እሑድ ‹‹ሞጋች›› በተሰኘው ፕሮግራሙ ላይ የአንድነት አመራሮችን ጋብዞ ነበር፡፡ የፕሮግራሙ አዘጋጅና የጣቢያው ምክትል ኃላፊ አቶ ብሩክ ከበደ እንደተለመደው የገዥውን ኃይል አጀንዳ ለማስፈጸም ደፋ ቀና ሲል ተስተውሏል፡፡ እስኪበቃን እንደታዘብነው ኢሕአዴጋውያን ላለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለማዳከም፣ ከተቻለም ለማጥፋት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ አሁንም በሽምቅ ተዋጊነት ሥነ-ልቦና የሚመሩ ናቸውና፣ በተቃዋሚው ኃይል ውስጥ ሰርገው ይገባሉ፡፡ በተቃውሞው ኃይል ውስጥ ልዩነት ሲከሰት ይፈነድቃሉ፤ በሕዝብ ሀብት በተቋቋሙት ነገር ግን በገቢር የአንድ አፋኝ አገዛዝ መሣሪያዎች በሆኑት ሚዲያዎች አማካኝነት እጅግ አጋንነው ያራግቡታል፡፡ በገዥው ቡድን ውስጥ የሐሳብ ልዩነት ተከስቶ እንደማያውቅ ወይም የሐሳብ ልዩነት የተቃዋሚ ፓርቲዎች መገለጫ እንደሆነ በድፍረት ሊነግሩን ይሞክራሉ፡፡ ገዥው ቡድን የልዩነት ሐሳብ ያላቸውን አባሎቹን በኃይል ሰጥ ለጥ እንደሚያደርጋቸው የሚታወቅ ቢሆንም እንደነ ሬዲዮ ፋና ያሉት ሚዲያዎች ትንፍሽ ሲሉ ሰምተናቸው አናውቅም፡፡ ለዶ/ር አረጋዊ በርሄ፣ ለአቶ አስገደ ገ/ሥላሴና አቶ ገብሩ አሥራት ምስጋና ይግባቸውና በዚህ በኩል ብዙ እውቀት ገብይተናል፡፡

አቶ ብሩክ ከበደ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች የሚናገሩትን እየቆራረጠ በማቅረብ በሕዝብ ዘንድ የተሳሳተ ግንዛቤ ለመፍጠር ብዙ ሲደክም ተስተውሏል፡፡ ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች መለያየት የሚሰብከውን ያህል ኢሕአዴግ የተለየ ሐሳብ በሚያነሱ አባላት ላይ የሚወስደውን እርምጃ ቢጠይቅልን ወይም ቢያስረዳን መልካም ነበር፡፡ ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች የገንዘብ ምንጭ ለማጣራት የሚራወጠውን ያህል ኢሕአዴግ በኢንዶውመንት ስም ከተደራጁት ግዙፍ የንግድ ድርጅቶች ጋር ስላለው ትስስር የሚመለከታቸውን ሰዎች ቢጠይቅልን መልካም ነበር፡፡ የአንድነት ማተሚያ ማሽን መግዛቱ አንገብግቦት አሜሪካ ድረስ ሄዶ ለማጣራት አደረግኩት የሚለውን ሙከራ ያህል ኢሕአዴግ ከብድርና ቁጠባ ተቋማት፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ማኅበራት፣ ከሴቶችና ወጣቶች ማኅበራት፣ ከዕድሮችና ከፎረሞች ጋር ስላለው ግንኙነት የሚመለከታቸውን አካላት ቢጠይቅልን ወይም እርሱም ራሱ የድርጅቱ ሰው ነውና ቢነግረን ምንኛ መልካም ነበር፡፡

አቶ ብሩክ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን ለማፋጠጥ ይሞክራል፡፡ከኢሕአዴግ አመራሮች ጋር ሲሆን ግን እንደ ብዙዎቹ ካድሬዎች አፉ ይተሳሰራል፡፡ ይህን አቋም ይዞ ጋዜጠኛ ነኝ ማለት እንዴት ይቻላል? ድርጅቱስ የተለመደውን አድሏዊ ተግባሩን ሳያሻሽል ስሙን ቢቀያይር ምን ዋጋ አለው? ቅሌት ብቻ!

## ሀሳቤ

ሀሳብ አለኝ የሚል ማንኛውም ሰው ለሚሊዮኖች ድምፅ በሚልከው ጽሁፍ ይህ አምድ ተሰጥቷል::

# የጨለማ ውስጥ . . . ብርቅርቅ ብርሃኖች !

"ከአንድም ሁለት ግዜ ልደቴን በ እስር ቤት ውስጥ አሳልፌያለሁ:: የአንደኛው እስር ምክንያት የፖሊስ ኮሌጅን እንከኖች በማጋለጤ (እነሱ በመዳፈሬ ነው የከሰሱኝ)፤ ሁለተኛው ደግሞ ወረዳ 24 ውስጥ ስለተገደለ ወጣት በመቆርቆሬ በቆርቆሮ እስር ቤቶች ውስጥ ቆይቻለሁ:: በተለይ ከሁለቱ እስሮች በሁለተኛው ጓደኞቼ እና ቤተሰቦቼ አሰርተው ያመጡትን ኬክ ለመቁረስ በቅቻለሁ:: የኛ ግዜ አለፈ:: ዛሬ እነርዕዮት አለሙ፣ እስክንድር ነጋ፣ ውብሸት ታዬ እና ተመስገን ደሳለኝ - እውነትን ስለጻፉ የእስር ቤት በሮች ተከርችመውባቸዋል:: በልደት ቀናቸውን - ካባ ለብሰው፣ ሻማ ለኩሰው ወይም ኬክ ቆርሰው አይደለም የሚያሳልፉት:: ልደታቸውን አስበው ይውላሉ:: አንገታቸውን ደፍተው ሳይሆን ቀና አድርገው ይሄዳሉ:: እነሱ ለመቁረስ ያልታደሉትን ኬክ፤ ስለነሱ ፍቅር እንቆርሳለን:: ስለጀግንነታቸው ሻማችንን እንለኩሳለን:: ስለክብራቸውም ጽዋችንን እናነሳለን::



**(ዳዊት ከበደ ወየሳ - ከአትላንታ)**

ከእለታት በአንዱ ቀን… በወረዳ 24 ውስጥ እስረኛ ነበርኩ:: የእስሩ መነሻ በአካባቢው የሚገኝ አንድ ወጣት በፖሊስ ተደብድቦ ስለመገደሉ በጻፍኩት ጽሁፍ የተነሳ ነው:: መርማሪ ኮሚሽኑም ሆነ መርማሪዎቹ የሚሉኝ፤ "እኛ ካንተ ምንም ጉዳይ የለንም:: ይህን መረጃ የሰጠህን ሰው ንገረንና ከእስር ቤት ትፈታለህ::" ይሉኛል::

እኔ ደግሞ፤ "ሲጀመር… በህጉ መሰረት እኔን የማሰርም ሆነ የመጠየቅ መብትና ህጋዊ ስልጣን ያለው ፌዴራል ፖሊስ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ በፕሬስ ህጉ አዋጅ ቁጥር (18 ወይም 21 መሰለኝ) መሰረት መረጃዬን ለፍርድ ቤት እንጂ፤ ለፖሊስ አልሰጥም::" አልኳቸው:: በዚህ ምክንያት ወደ እስር ቤት ተገፍትሬ ስጣል 24ኛ አመቴን ለማክበር 3 ቀናት ብቻ ነበር የቀሩኝ:: ምናልባት ፖሊሶቹ የጠየቁኝን ፈጽሜ ብሆን አንድ ለሊትም ቢሆን፤ በእስር ባላሳለፍኩ ነበር:: እግረ መንገዴን መጨረሻዬን (በቅንፍ ውስጥ) ላውጋችሁና ወደዋናው ርዕስ እመለሳለሁ::

(የጭቦ አምላክ እንዲሉ - ከታሰርኩ በኋላ - እዛ እስር ቤት ውስጥ ስለሚቹ ጉዳይ በቅርብ የሚያውቁ ጓደኞቹን አግኝቼ፤ ጭራሽ ሌላም ሌላም ሚስጥር ጨመሩልኝ:: በታሰርኩ በሳምንቱ ፖሊስ አዛዡ ጋር በድጋሚ ቀርቤ ስነጋገር፤ "እኛ እኮ ይሁን ብለን እንጂ፤ ሌላም ሚስጥር እናውቃለን" በማለት እነዛን ሚስጥሮች እንደተጨማሪ መረጃ አድርጌ ወደፊት በፍርድ ቤት እንደምከራከር ስገልጽለት - ተረጋግቶ ሊያረጋጋኝ ሞከሩ:: በሚቀጥለውም ቀን ስፈታ - እኔ ሳልሆን እውነት እንደተፈታ በመቁጠሬ ደስ አለኝ::)

ርዕዮት አለሙ፣ እስክንድር ነጋ፣ ውብሸት ታዬ፣ ተመስገን ደሳለኝ እና የዞን ዘጠኝ ጦማርያን ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ነገር አንድ ነው:: ሁሉም ለእውነት ስለቆሙ፣ እውነትን ስለመሰከሩ "አሸባሪ" የሚል የክብር ኒሻን ሰጥተው አሰሯቸው… ይህ ሁሉንም ያመሳስላቸዋል:: ሌላም የሚያመሳስላቸው ነገር አለ:: ሁሉም ከመታሰራቸው በፊትም ሆነ ከታሰሩ በኋላ እንዲፈጽሙ የተጠየቁት ነገር ተመሳሳይ ነው:: 'ሌላውን አጋልጠው ራሳቸውን ነጻ እንዲያወጡ' ሲጠየቁ፤ ሁሉም "አሻፈረኝ" ብለዋል::

እነዚህ ጋዜጠኞች በእስር ከመንገላታት ይልቅ፤ ታስረው እንዳልታሰሩት ህዝቦች - ቢያንስ በነጻነት መንከላወስን ማንም አይነፍጋቸውም ነበር:: ነገር ግን እንደወርቅ… በእሳት የተፈተነው ህሊናቸው በቀላሉ ለመንበርከክ እምቢኝ አለ:: ዋሽቶ እና ቀጥፎ ከመኖር ይልቅ እውነትን ተናግሮ መታሰርን መረጡ:: ህሊናን ሸጦ ክብርን ከማዋረድ ይልቅ - አንገታቸውን ቀና አድርገው - በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ የሃቅ ችቦን አበሩ:: እነሆ በነዚያ ድቅድቅ ጨለማዎች ውስጥ፤ ለአይናችን ብርሃን ለእግራችን መንገድ ሆነውን፤ እያየን እንድንራመድ ረዱን:: ሆዳቸው ሳይሆን ህሊናቸው ስላሸነፋቸው - በውርደት ከመኖር ይልቅ በክብር መታሰርን መረጡ:: ይህ ራሳቸውን ያስከበሩበት ክብር እና ሞገሳቸው ኩራቱ ለነሱ ብቻ ሳይሆን፤ ለኛ ለሙያ ጓደኞቻቸው ብሎም ለእውነት ለቆሙ ኩሩ ኢትዮጵያውያን ጭምር ነው:: ኮርተው አኩርተውናልና ክብር እና ምስጋናችን ይድረሳቸው::

ዛሬ በእስር ላይ የሚገኙትን የነጻ ፕሬስ ጋዜጠኞች ስናስብ፤ ልባችን በኩራት ይሞላል:: በአዘቦቱም ሆነ በልደታቸው - "እንኳንም ተወለዳችሁልን" እንላቸዋለን:: "የአሸባሪነት ኒሻን ወርቃቸው ከእውነት ተራራ ጫፍ ላይ፤ የማንነታቸው መገለጫ ክብርም ከተራው ሰው በላይ… እላይ ሆኖ ይታየናል:: እነሆ እውነትን ለመመስከር እንደተላከ መሲህ - ህሊናቸውን አልሸጡምና ሊከበሩ እንጂ በእናታቸው የእሾኽ አክሊል ሊደፋባቸው አይገባም" እንላለን!

(እዚህ ላይ አንድ ገጠመኝ እንጨምር)

በአንድ ወቅት ውጭ አገር መጥቶ ከነበረ "ጋዜጠኛ" ጋር ሙግት ገጠምን:: ስሜ ስሙ ነው - ከነአባት ስሜ:: ከእውነት የግስጋሴ ጎዳና ወጥቶ በኮሮኮንቹ መንገድ ላይ ጉዞ ሊጀምር ሲል ዳግም ተገናኘትን:: በሃሳብ ተፋጨን:: ከፕሬስ ህልውና እስከ ጋዜጠኝነት ፍልስፍና ድረስ ብዙ ተሟገትን:: በመጨረሻ ግን … "ስማ ሞክሼ" አለኝ:: ጆሮዬን ሰጠሁት::

"ሞክሼ አንድ ነገር ልንገርህ:: እኔ እኮ አገር ቤት ገብቼ ለመኖር መንገዱ - አንድ እና አንድ - ቀላል ነገር ነው::" አለኝ::

"እንዴት?" አልኩት በመገረም::

"ቀላል ነው:: የኢህአዴግን መስመር እንዳናልፍ እነበረከት ስምኦን ያሰመሩት መስመር አለ:: እሱን አለማለፍ ነው ከኛ የሚጠበቀው::" ሲለኝ በወቅቱ ፈገግ አልኩ:: አሁን ወደ አገር ቤት ከተመለሰ በኋላ ስራዎቹን ስከታተል ግን ፈገግታዬን ወደ ሳቅ ቀየረው:: ኢህአዴግ ካሰመረው መስመር ውጪ ሆነው ከህሊናቸው ጋር እየተጣሉ የሚኖሩ እና መስመሩን ጥሰው ገብተው፤ እውነትን ስለመሰከሩ "አሸባሪ" ተብለው የታሰሩ ሰዎችን በግልጽ ለማየት የቻልንበት አጋጣሚ ተፈጠረ:: ይቺም እድሜ ሆና ለመታዘብ በቃን::

ቢሆንም ግን… ከነዚህ ጋዜጠኞች መታፈን ጀርባ የታሰሩት እውነት እና ፍትህ ናቸው:: እውነት ደግሞ በጨለማ ውስጥ የሚያንጸባርቅ ብርሃን ነው:: እውነት ታስሮ አይቀርም!

በኢትዮጵያ የፕሬስ ታሪክ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ የፕሬስ ውጤቶች ፈልተው ወጥተው - ፈርተው የቀሩ፤ ሞተው የኖሩ ወይም ደፍረው እስከቀራንዮ የተጓዙ - ሁሉም በየራሳቸው የየራሳቸው ታሪክ አላቸው:: ዛሬ የፍርድ ቤት ዶሴ ብናገላብጥ - በነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ላይ የተመሰረቱ በሺህ የሚቆጥሩ መዝገቦችን እናገኛለን:: እነዚያ መዝገቦች - እውነትን ተናግረን ጠመንጃ አንጋቾችን ያሸበርንባቸው ታሪኮቻችን ናቸው:: ወደ ቃሊቲ፣ ወይም ዝዋይ አልያም ቅሊንጦ እስር ቤት ብንሄድ የጋዜጠኞቻችን አሻራ ያረፈበትን ምድር እናገኛለን:: እነዚያ ለእውነት የቆሙ ትንታግ ጋዜጠኞቻችን በጨለማ ውስጥ የሚበሩ ብርሃን ናቸው፤ እንኮራባቸዋለን:: እንኳንም ተወለዳችሁልን፤ እንኳንም ለኢትዮጵያ ብርሃን ሆናቹህ::

(ይህ ጽሁፍ በተለይ ለርዕዮት አለሙ የልደት በአል ተዘጋጀ::

ሆኖም መታሰቢያነቱ ልደታቸውን በእስር ቤት ለሚያሳልፉት

ለሁሉም ጋዜጠኛ ጓደኞቻችን ይሁን)

ርዕዮት - መልካም ልደት::



## ኃይለማርያም... ከገፅ 5 የዞረ

የጫካ ሕግ የሆነው ‹‹ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት (Democratic centralism›› እንዳለ ነው። ሙስና እና ፀረ- ዴሞክራሲያዊነት የሥርዓቱ ዋነኛ መገለጫ ነው። ተቃዋሚዎችን እንደ ጠላት በመፈረጅ ጠባቦች፣ ትምክተኞች ማለት የነበረና ያለ ነው። ኢትዮጵያ ፍትህ የተረገጠባት ሀገር ሆናለች። የሲቪክ ማኅበራት፣ የፕሬስ፣ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ እንዳለ ነው። ስለዚህ ጠለቅ ብሎ ላየው ሰው በአቶ መለስ ጊዜ ይሻል ነበር ብሎ ማለት አይችልም። እርግጥ አቶ መለስ የሥልጣን ጥማቱ እየተነፈሰ በመሄዱና ሙልጭልጭ ሳሙና ስለሆነ ይገለባበጣል። ችግር ሲፈጠርም በሌላ ላይ ያላክካል። የአሁኖቹ ይህን ጥበብ በደንብ የተማሩት አይመስለኝም።

ለምሣሌ፣ ጌታቸው ረዳ የሚባል ሰው በአሜሪካን ድምፅ ገብቶ ‹‹ባለቤቱ አስቀድማ አሜሪካ ስለነበረች አስገድዳ አስቀረችው›› ብሏል። እግዜር ያሳይህ፣ ባለቤቱ ወደ አሜሪካ የመጣችው እኔ ከመጣሁ ሁለት ዓመት በኋላ ነው። የሚገርምህ፣ እነዚህ ፀረ-ዴሞክራሲ ሀይሎች መጽሐፉን ተረባርበው ቢገዙትም አስተያየት መስጠት አልቻሉም። በአሜሪካን እና በእንግሊዝ የሚገኙት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ብቻ ከመቶ በላይ ገዝተዋል። ወደ ሀገር ቤት ሌላውን ከልክለው በገፍ ሲያስገቡ የነበሩት እነሱ ናቸው። ይህም ሆኖ ‹‹ቂሱም ዝም፣ መጽሐፉም ዝም›› እንደሚባለው ሆነዋል።

በበኩሌ እነዚህ ሀይሎች በይዘቱ ላይ ቢከራከሩ ደስ ይለኛል። የአዲስአበባ መሬት የተዘረፈው ‹‹መንግሥታዊ ሌብነት›› ስለተፈፀመ ነው። መመሪያ ቁጥር አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ ‹‹ሁከት ይወገድልኝ›› አዋጅ በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው። የእምነት ተቋማት ችግር የገጠማቸው በኢህአዴግ ጣልቃ ገብነት ነው። መጅሊሱን ጠፍጥፈን የፈጠርነው እኛ ነን... ወዘተ. እነዚህ ሰዎች በዚህ ዙሪያ ትንፍሽ አላሉም።

ሁለተኛው አሰላለፍ መረጃ የሚፈልገው ነው። ይሄ ሀይል መጽሐፉን ካነበበ በኋላ የመቆጨት ስሜት ታነብበታለህ። አዲስአበባ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያም በሚጠሏት ሰዎች እጅ ወድቃለች ሲሉ ትሰማለህ። እስከ አሁንም ድረስ መወያያ አድርገውታል።

ቀጣዩን መጽሐፌንም በጉጉት እየጠበቁት እንደሆነ ነግረውኛል። የፖለቲካ እስረኛ ለሆነው የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ምክትል ፕሬዚደንትና የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ለነበረው አቶ አንዷለም አራጌ አጋርነቴን በማሳየቴ አክብሮታቸውን ነግረውኛል። [አቶ ኤርሚያስ፣ ከመጽሐፉ ሽያጭ 20 በመቶውን ለአቶ አንዷለም አራጌ አጋርነታቸውን በማሳየት 95 ሺህ ብር በቅርቡ ሰጥተዋል] በዚህ አጋጣሚ ይህ የሆነው በእኔ ሳይሆን በኢትዮጵያ ህዝብ በመሆኑ ምስጋናውን መውሰድ ያለበት የኢትዮጵያ ህዝብ ነው። እባክህን አድርስልኝ።

**አቶ መለስ በሕይወት ቢኖሩና መጽሐፍዎን ቢያነቡት ምን ይሰማቸው ነበር ብለው ያስባሉ? በመጽሐፍዎ ውስጥ ስማቸው በጉልህ ከተጠቀሱት ባለሥልጣናት መካከል መጽሐፉን አንብበው ያደረስዎት ገንቢም ሆነ አሉታዊ ምላሽ አለ? ካለ ቢጠቅሱልን?**

አቶ መለስ ዜናዊ በሕይወት ኖሮ መጽሐፉን ቢያነበው፣ የሚያውቀውን ነገር ስለጻፍኩ ብዙ ይገረማል ብዬ አላስብም። ጋዜጠኞች ቢጠይቁት ግን እንደተለመደው ‹‹አዲስ ዘመንንና አዲስ ነገርን እንደማላነባቸው ሁሉ ይህንንም አላነበብኩትም›› በማለት የበታችነት ስሜቱን ለመደበቅ የሚሞክር ይመስለኛል።

ሌሎች ባለሥልጣናት ተረባርበው እንዳነበቡት ሰምቻለሁ። አንድ ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው የኦህዴድ ሚኒስትር አፍ አውጥቶ ‹‹ከመቀበል ውጭ አማራጭ የለም›› እንዳለ ነግረውኛል።

**ከጠ/ሚ/ር ኃይለማርያም ደሳለኝ ጋር በቅርበት እንደመስራትዎ የእሳቸውን መንግሥታዊ አመራርነት በትክክል እንዴት ያዩታል?**



አቶ ኃይለማሪያም የመንግሥት ዋና ተጠሪና የኢህአዴግ ቢሮ ምክትል ሐላፊ ሆኖ አብረን ሰርተናል። ከጥንካሬው ለመነሳት ሐይለማሪያም የዝርዝር (detail) ሰው ነው። ከዚህ ተነስቼ ኃይለማርያም የአንድ ፋብሪካ ማናጀር ቢሆን ውጤታማ ይሆን ነበር የሚል እምነት አለኝ። የሰው ልጅን ለመምራት ( Leadership) ግን ቦታው አይደለም። መሪ ለመሆን የራስህ ርዕይ ሊኖርህ ይገባል። መሪ ለመሆን ውሣኔ ሠጪ መሆን አለብህ። መሪ ለመሆን ማንንም መምሰል ሳይጠበቅብህ በራስ መተማመን ሊኖርህ ይገባል። መሪ ለመሆን ችግሮችን በመረዳት የመፍትሔ ሐሳቦችን ማመንጨት ያስፈልጋል። መሪ ለመሆን ከአድርባይነት የተላቀቀ መሆን ያስፈልጋል። ኃይለማርያም የእነዚህ ሁሉ ባለቤቶች አይደለም።

**ከአቶ መለስ በኋላ ያለው ኢህአዴግ ወደጫካ ማንነቱ በመመለስ በወደኃይል እርምጃ ይበልጥ እየገባ ያለበት ሁኔታ መኖሩ የሚገልፁ ወገኖች አሉ። እውነት ነው? ከሆነስ ዋነኛ ምክንያቱ ምንድን ነው?**

የኢህአዴግ መሰረታዊ ባህሪ እና መርሆ ተቀይሯል የሚል እምነት የለኝም። መንግሥታዊ ፓሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች እንዳሉ ናቸው። ድርጅቱ የሚመራበት ዘር ላይ የተሞረኮዘ አደረጃጀት አልተቀየረም። የጫካ ሕግ የሆነው ‹‹ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት (Democratic centralism›› እንዳለ ነው። ሙስና እና ፀረ- ዴሞክራሲያዊነት የሥርዓቱ ዋነኛ መገለጫ ነው። ተቃዋሚዎችን እንደ ጠላት በመፈረጅ ጠባቦች፣ ትምክተኞች ማለት የነበረና ያለ ነው። ኢትዮጵያ ፍትህ የተረገጠባት ሀገር ሆናለች። የሲቪክ ማኅበራት፣ የፕሬስ፣ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ እንዳለ ነው። ስለዚህ ጠለቅ ብሎ ላየው ሰው በአቶ መለስ ጊዜ ይሻል ነበር ብሎ ማለት አይችልም። እርግጥ አቶ መለስ የሥልጣን ጥማቱ እየተነፈሰ በመሄዱና ሙልጭልጭ ሳሙና ስለሆነ ይገለባበጣል። ችግር ሲፈጠርም በሌላ ላይ ያላክካል። የአሁኖቹ ይህን ጥበብ በደንብ የተማሩት አይመስለኝም።

ከአቶ ኤርሚያስ ለገሠ ጋር የተደረገውን ቀጣይ ቃለ-ምልልስ በሚቀጥለው ሳምንት ይቀርባል።

# ለህዝብ ጥያቄ ዱላ መልስ አይሆንም !



መስከረም ያረጋል

ከጓደኞቼ ጋር ተገናኝተን ሻይ፣ ቡና ስንል ብዙ ርዕሰ ጉዳዮች እያነሳን እናወራለን:: ስለ ግል ህይወታችን፣ ስለ ጓደኞቻችን፣ አዳዲስ ስለሰማናቸው ወይም ስለአየናቸው ጉዳዮች፣ ብቻ ምን አለፋችሁ የማናነሳው የማንጥለው ጉዳይ የለም:: ታዲያ አንዳንዴ ነገርን ነገር አንስቶት ፖለቲካዊና ሀገራዊ ጉዳዮች በጨዋታችን መሃል መነሳቱ አይቀርም፣ ያኔ ታዲያ ድምጻችንን ቀነስ አድርገን፤ ዙሪያችንን ቃኝት እያደረግን ነው የምናወራው:: ይህ ታዲያ በእኔና በጓደኞቼ መካከል ብቻ ሳይሆን ብዙ ሰው ላይ ያስተዋልኩት ነባራዊ ሁኔታ ነው:: ግን ለምን) ፖለቲካዊ ጉዳይ በነፃነት ማውራት በህዝብ ዘንድ እንደጦር ተፈራ?

በአሁኑ ወቅት አብዛኛው ወላጅ ቢጠየቅ ልጁ ወደ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ እንዲቀላቀል የሚፈልግ የለም፣ በተለይ ከተቃዋሚ ጎራ ከሆነ ለወላጆችም ሆነ ለቅርብ ሰዎች ስጋትን ይፈጥራል:: ይህ ለምን እንደሆነ ግልጽ ነው፣ ፍርሃት ነው!:: መንግሥት ተቃዋሚዎች ላይ ሲያደርስ የነበረውና አሁንም እያደረሰ ያለውን አፈና፣ እስር፣ ድብደባና የመሳሰሉትን ሁሉም ስለሚያውቀው ይህ ነገር በልጆቻቸው ወይም በቅርብ በሚያውቁት ሰው ደርሶ ማየት ስለማይፈልጉ ነው:: ሌላ የተደበቀ ምሥጢር የለውም::

ገዢው ፓርቲ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ካሉበት ብዙ የአስተዳደር ችግሮች አንዱ ከህዝብ ጋር ተቀራርቦና ተነጋግሮ አለመሥራቱ ነው:: ዴሞክራሲ ሰፍኖባታል እያሉ የመንግሥት ልሳን የሆኑ ሚዲያዎች በተደጋጋሚ በሚናገሩባትም ሃገር ውስጥ ማንኛውም ከመንግሥት የተለየ አመለካከትን የያዘን ሰው ያለግብሩ በመፈረጅ እንደጠላት ይታያል::

የነገረ ኢትዮጵያ ምክትል ዋና አዘጋጅ የሆነው ጋዜጠኛ በላይ ማናዬ ባለፈው ዓመት አሳትሞት በነበረው ‹‹ይህ ትውልድ›› የሚል ተወዳጅ መጽሃፉ ላይ ያሰፈረው አንድ ፅሁፍ በአሁኑ ግዜ ያለውን አጉል ፍረጃ በደንብ ይገልጸዋል:: ብዬ አስባለሁ::ጹሁፉ እንዲህ ይላል፡- አዎ ይህ ትውልድ ነኝ! ሥራ ባጣ አደገኛ ቦዘኔ፣ ብፅፍ አሸባሪ፣ ስለ ዴሞክራሲ ብሰብክ የኒዎ-ሊብራሊዝም አቀንቃኝ፤ታሪኬን ባወሳ የድሮ ስርዓት ናፋቂ፤ ሃይማኖቴን ብል አክራሪ፤ መብቴን ብጠይቅ ፀረ-ልማትና ፀረ-ሰላም፤ ስለ ሃገሬ ብወያይ የጥፋተኞች ተላላኪ፤ብደራጅ ተበተን፤ ብበተን ተደራጅ የተባለኩኝ የዚህ ትውልድ አባል:: በዚህ ከንቱ ፍረጃ መንግሥት ከተቃዋሚ ጎራ የህዝብን ተቀባይነትን ያገኙ ፖለቲከኞችን፣ ጋዜጠኞችን፣ ጦማሪያንን የተለየ አቋም በመያዛቸው እና መንግሥትን በግልፅ በመተቸታቸው ‹‹አሸባሪ›› የሚል ከግብራቸው ጋር የማይገናኝ ክስ እያቀረበ በማጎሪያ እስር ቤቶቹ አስሯቸው ይገኛል::

ከዚህ በተጨማሪ ህዝቡ ላይ ለሚታየው ፍርሃት ሌላ መንስኤ የሆነው ጉዳይ የመንግሥት አላስፈላጊ የሃይል እርምጃ ነው:: የህዝቡን ጥያቄ በዱላ መመለስ የለመደው መንግሥታችን በተደጋጋሚ ጊዜ እንዳየነው ጥያቄውን አንግቦ ገፍቶ አደባባይ የወጣ ህዝብ ላይ ባሰማራቸው የፖሊስ ኃይሎች በመደብደብ አልፎ ተርፎም ተኩስ በመክፈት በማቁሰልና እስከመግደል የደረሰባቸው አሰቃቂ ጊዜያቶች እንደነበሩ ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ነው:: ሌላውን ሁሉ እንተወውና በቅርብ ከነበሩት ውስጥ እንኳን የተወሰኑ ምሳሌዎችን መጥቀስ እንችላለን:: ባሳለፍነው ዓመት የሙስሊሙ ህብረተሰብ በመጅሊስ አመራረጥ ላይ የነበራቸውን ተቃውሞ በየሳምንቱ አርብ በአንዋር መስጊድ እየተገኙ ጨዋነት በተሞላውና ለሌሎች ምሳሌ ሊሆን በሚችል መልኩ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሟቸውን ሲገልፁ በነበረበት ወቅት መንግሥት ሴት፣ ወንድ፣ ወጣት፣ አዛውንት ሳይል በእነዚህ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ከፍተኛ ድብደባና ስቃይ እንዳደረሰባቸው እናስታውሳለን:: በሌላ በኩል በዚሁ አመት ሰማያዊ ፓርቲ ከሌሎች 8 ፓርቲዎች ጋር በመተባበር ጠርቶት ለነበረው የአዳር ሰልፍ ገና የሰልፉ ሰዓት እንኳን ሳይደርስ ፖሊሶችንና የደህንነት ሃይሎችን የተቃውሞ ሰልፉ ሊደረግ ታስቦበት ወደነበረው መስቀል አደባባይና የሰማያዊ ፓርቲ ጽህፈት ቤት አካባቢ በብዛት በመገኘት ደፍረዉ ሰልፉን ሊያደርጉ ያሰቡትን እንዲሁም በአካባቢዉ የነበሩ ሰዎችን በጅምላ በማሰር በተጨማሪም ከሰማያዊ ፓርቲ ፅ/ቤት ወደ ሰልፉ ቦታ ለመሄድ በጋራ የተንቀሳቀሱ የፓርቲዉ አመራሮች አባላት እንዲሁም ደጋፊዎች ፍፁም ጭካኔ በተሞላበት መንገድ ከባድ ድብደባ ደርሶባቸዋል:: የመጨረሻ ምሳሌዬን ልጥቀስ በቅርቡ በባህር ዳር ከተማ ላይ የተፈጠረውን ስንመለከት ‹‹ለጥምቀት በዓል የታቦታት ማረፊያ የሆነዉ ቦታ ከልማት ጋር በተያያዘ ምክንያት ይፈርሳል!››:: መባሉን ተከትሎ ተቃዉሟቸዉን ሊያሰሙ የወጡ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ላይ በከፈተው ተኩስ የቆሰሉ፣ የሞቱ ሰዎች እንደነበሩ የቅርብ ጊዜ አሳዛኝ ትውስታ ነዉ::

መንግሥት ሆይ ትሰማ እንደሆነ ስማ! ለህዝብ ጥያቄ ዱላ መልስ አይሆንም:: ይህ ህዝብ፡- ለጊዜዉ ዱላውን፣ እስሩን፣ ግድያዉን ፈርቶ ጥያቄዉን በውስጡ አፍኖ እየተብሰለሰለ ዝም ሊል ይችላል:: ነገር ግን ይህ ዝምታ ዘላቂ አይደለም:: ጥያቄዉ እና ብሶቱ ከፍርሀቱ የበለጠ ቀን ምንም የሚመልሰዉ ነገር አይኖርም:: ስለዚህ መንግሥት ሆይ ለራስህ ብለህ ስማኝ! ለህዝቡ የሚገባዉን ክብር ስጡ! ከህዝቡ ለሚነሱ ጥያቄዎች ተቀራርቦ ለመፍታትና መልስ ለመስጠት ሞክሩ!::ህዝብን እያስከፋችሁና ቂም እንዲይዝ እያደረጋችሁ ምንም ያህል ርቀት ልትጓዙ አትችሉም!:: መከባበርንና መደማመጥን የመሰለ ትልቅ ነገር የለም!:: እናንተ ህዝቡ እንዲያከብራችሁ እንደምትፈልጉት ሁሉ ህዝቡንም አክብሩት! በሥራችሁ እንጂ በጉልበታችሁ እንከበራለን:: ብላችሁ አታስቡ! በዱላ ተከብሮ የሚያዉቅ የለምና!::

# እየራበው ተመስገን የሚል ህዝብ !



ሀብታሙ ምናለ

ሀበሻ ‹‹ከታደላቸው›› የአፍ ፀጋዎች መካከል ለማም፣ ከፋም፤ ነጋም ጠባም፤ ከፋውም ደስ አለውም፤ አላለውም ‹‹ተመስገን!›› ማለት ነው:: ለነገሩ እኔም ተመስገን እላለሁ:: አዎ ተመስገን ቃላት የለውም ተመስገን፡- ለነጻው ፕሬስ በራሱ መንገድ፤ በራሱ ጥረት ለሙያው ግርማ ሞገስ የሰጠ፤ ጀግንነት ያስተማረ፣ አንዳንዶች በፍራቻ ቋት ውስጥ ገብተው ሲሸሸጉ ምንም ሳይፈራ የወጣ፣ ወጣቱን በሀገሩ ላይ ጭቆናን፣ አፈናን በመቃወም ለውጥ እንዲያመጣ በብዕሮቹ ያነቃ፣ በፍርሃት ውስጥ ያለውን የድፍረት መጣጥፎችን እንዲያነብ ያደረገ ‹‹ብርቱ ጋዜጠኛ›› ነው::

ዛሬ ላይ በብዕር፡- ማንነታቸውን እየነገረ ‹‹እባካችሁ ታረሙ›› በማለቱ እሱም እንደ ሌሎች አጋሮቹ እስር ቤት ተወርውሮ የሶስት ዓመት እስራት ተፈርዶበት በእስር ቢገኝም የባሰ ነገር ባለመምጣቱ እንደ ባህላችን ተመስገን! ብያለሁ ብዬም አላበቃም ተመስገን ጀግና ነው!

አይ የኔ ነገር፣ ተመስገን የምትለውን ስም ሳነሳ በነጻው ፕሬስ ላይ ለሰራው ሥራ ክብርን ስለምሰጠው ስለእሱ ሳልናገር አላልፍም ብዬ እኮ ነው:: ለወገናቸው ሲሉ ሞትን የሚደፍሩትን ማድነቅና ለሀገራቸው ክብር የቆሙትን ሰዎች ክብር መስጠቴ ልማድ ሆኖብኛል:: በዚህች ሰዓት ስሙን ካነሳሁ አይቀር አክብሮቴን በአጭሩ ልግለጽ ብዬ ነው:: ወደዋናው ነጥብ ልቀጥል፡-

‹‹ሀበሻ ለምን ‘ተመስገን’ ይላል?›› ብዬ ሳሰላስል ከራሴ ጀምሬ አጠገቤ ያሉትን ሰዎች ማጥናት ጀመርኩ:: ሁሉም እንደ ደላው ቤተሰብ፤ በአንድ አይነት ዜማ ከአንድ ነገር በኃላ ስለሁኔታው ብትጠይቁ መልሳቸው ቢሳከም ባይሳካም ተመስገን ነው! ‹‹ተመስገን ማለት በቃ ልማድ ነው? ወይስ ከልብ ነው)›› ለራሴም አይገባኝም:: በተለይ ተመስገን የምትለው አምስት የምስጋና ቃል ለእናቶቻችን በአንደበታቸው ልክ የተሰራች ነው:: የምትመስለው እናቶቻችን እየተበደሉ ስላመሰገኑባቸው የስቃይ ዓመታት በጥቂቱ እያጣቀስን እንመልከተው::-

ወደኃላ እንመለስና ጨካኙ ደርግ የሰውን ነፍስ ለማጥፋት ግድ የማይሰጠው፣ በሰው ደም ግዛቱ የሚጠነክር ይመስል ዘር ማጥፋቱን እንደ ጀግንነት በሚቆጥርበት ወቅት የኢትዮጵያ እናቶች ማኅፀኖቻቸውን የባታሊዮን ጦር ያደራጁ ይመስል የሚወልዱት ‹‹ጀግና ጀግና›› ብቻ ነበር::ታዲያ ደርግ መራሹ መጣና መጀመሪያ ልጆቻቸውን በኢህአፓና በቀይ ሽብር እያመካኘ የቀለሃ ቀለብ ያደርጋቸው ጀመር::በሀገራቸው ልማድ መሰረት ‹‹የልጆቼን ሞት አታሳየኝ›› ብለው የፀለዩ እናቶች የልጆቻቸውን እንደወጡ በሜዳ መቅረት፤ በየአደባባዩ መረሸንና ሬሳቸውን ፀሐይ ሲሞቅ እንደዋለ ሲሰሙ የእናትነት አንጀታቸው አልችል ብሎ ደረታቸውን እየደቁ ፊታቸውን እየነጩ ማልቀሱን ተያያዙት:: ህዝቡም በዕለቱ በለቅሶ ቢያግዛቸውም ቆየት ብሎ በቃ ተዉ! እንጂ ተመስገን በሉ! ብሎ ማጽናናቱን ተያያዙት እነሱም እውነትም ነገ ምን እንደሚመጣ አወቅን) ብለው ተመስገን!!! አሉ:: የዋሆች ነበሩና ተመስገን በማያስብለው ተመስገን አሉ::

አሁንም በድጋሚ ብዙም ሳይገፋ ደም ያሰከረው መንግሥት ወጣት የተባለን እየለቀመ ወደ ጦር ሜዳ ማጓጓዝ ጀመረ:: ልጆቻቸው ከቤት ከወጡ አንድም በጠላት ጦር ያለርህራሄ እንደሚሞቱ፤ ሲቀጥልም ደርግ ራሱ እንደሚረሽናቸው ስለሚያውቁ እንባቸው በፊታቸው ላይ ከመውረድ አልፎ ቀሚሳቸውን አራሰ:: አስር ጊዜ ፊታቸው ላይ ያለውን እንባ ስራ በጎዳው፤ ልስላሴ በጎደለው እጃቸው እየሞዢቁ አለቀሱ:: የጠነከሩትም ውስጣቸው ሃዘን ገብቶት እንኳን ቢሆን በግልጽ ጥንካሬ መጉደሉ የሚታይባቸው ‹‹ተዉ እንጂ ሃዘን አታብዙ›› ብለው ሃዘን የበዘባቸውን፤ መቋቋም ያቃታቸውን አጽናንተው ተመስገን! አስባሏቸው::

ተመስገን ነው እንጂ የሚባለው ታሞ

ያማረሩት እንደው ይጨማራል ደግሞ

እያሉ በመጨረሻም የኢትዮጵያ እናቶችን ጸሎታቸውን ፈጣሪ ሰማቸው መሰለኝ የሚናድ የማይመስለው ደርግ ሽፍቶቹ እያለ በሚጠራቸው ተገርስሶ በኢትዮጵያ ድጋሚ እንኳን ወጣቶችን መሬት ላይ ሊዘርር ቀርቶ አንድም ድንጋይ ከመሬት ማንሳት እንዳይችል ተደርጎ ሲወድቅ ኢትዮጵያን ሲቆጣጠር እኒህ እናቶች የልጆቻቸው ሞትን የሚያስረሳ ደስታ መጣ ተመስገን! አሉ:: ይሄኛው መንግሥት፡- ‹‹የኢትዮጵያ እናቶች ውለዱ ክበዱ›› አለ:: የወለድነው ይበቃል! ያሉት ኢትዮጵያውያን ብዙም ሳይገፉት ጥቂቶች ሀገሯን እየበዘበዙ ብዙኃኑ ህዝብ ልጆቻቸውን በሥራ እጦት እያሰቃየ መንገድ ዳር ቁጭ በማለት የሚቀመጡባትን ድንጋይ ፀሃይ እንደከለሉ ውለው፤ አምሽተው ማታ ለመኝታ እቤታቸው ይገባሉ! በነገታውም እዛው ቦታ ላይ ያለ ጥይት ያሰጣቸው ጀመር::

እኒህ እናቶች ታዲያ ደርግ ገድሎ በክፍያ እሬሳ ከፍላችሁ ውሰዱ እያለ ከሚያስለቅሰን ይሻላል ብለው ተመስገን! አሉ::ቆይቶ ደግሞ በምርጫ ሰበብ ልጆቻቸውን ባንክ ሊዘርፉ ያላቸውን ወጣቶች አልፎም ተርፎም ልጃገረዶችን ከየትምህርት ቤቶች አውጥቶ በጥይት ሲያሰኘውም እህል ውሃ በማያሰኝ ሰደፍ ቀጠቀጣቸው:: በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶም ተሰምቶ በማይውቅ ሁኔታ ከልጆች አልፎ እናቶችን ገደለ:: አሁንም ደግሞ ለልጆቻቸው ብቻ ሳይሆን ጎረቤቶቻቸውም ሲገደሉ እያለቀሱ በዚህ ይለፍ ብለው ተመስገን! አሉ:: አሁን ደግሞ ልጆቻቸውን ለምን መንግሥትን ተቃወሙ ብሎ አንዴ አሸባሪ፣ አንዴ አብዮት ጠሪ እያለ ያስራል:: አሁንም ህዝቡ ተመስገን! እያለ ነው:: በመጨረሻ ኢህአዴግ ሲወድቅና እንደ ጉሬዛ በየገደሉ በየድንበሩ እግሬ አውጪኝ ብሎ ሊያመልጡ ሲሯሯጥ ቢያዩ ተመስገን! ሳይሉ ይቀራሉ)

ተመስገን! ማለት የለባችሁም ብዬ አልቃወምም:: ነገር ግን በችግር ውስጥ ሆነን ተመስገን ማለት ምን ማለት ነው) ለብዙ ዓመታት በኢትዮጵያ እናቶች ተመስገን እዚህ ደርሰናል:: ሁላችንም በጭቆና ውስጥ ብንወለድ ጥፋቱ የእኛ አይደለም:: ‹‹በጭቆና ውስጥ ሆነን ብንሞት ጥፋቱ የእኛ ነው››:: ምክንያቱም እናቶቻችን እኛን ወልደው፤ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ አሟልተው አሳድገውናል:: እነሱ ፊደል ባይቆጥሩ እንኳን የትምህርት ትርጉም ገብቷቸው ፊደል አስቆጥረውናል:: ስለዚህ እኛ ከበፊቱ ትውልድ በእውቀት አንድ እርምጃ ቀድመናል:: የጥንቱ ኢትዮጵያውያን ነጻነታቸውን ሊጋፋ ከሚሞክር ሀገርም ሆነ ግለሰብ ጋር መደራደር በፍፁም አይፈልጉም:: አድርገውትም አያውቁም! እኛም አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ተመስገን እያልን ከመማቀቅ ይልቅ እመር ብለን ተነስተን ችግር ፈጣሪውን ማስወገድ፤ የተሻለ ለውጥና ተስፋ ማምጣት አለብን:: ያለበለዚያ ተቸግረንም ተመስገን! እያልን በጥቂቶች ተጨቁነንና ተረግጠን፡- እነሱ ሲበሉ እኛ አይናችን እያቁለጨለጭን፤ እነሱ ፍርድ ቤት እጃቸውን ዘርግተው ረብጣ ሰጥተው እኛ ላይ ሲያስፈርዱ እኛ ደግሞ እጃችንን አስግገን ለካቴና ሰጥተን እንታሰራለን፤ እነሱ እንደፈለጉ ውስኪ ሲራጩ እኛ ደግሞ የምንጠጣውን ውሃ አጥተን ባኃይለኛ ጥም እንሰቃያለን:: ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል ብቻ እንዲህ እንዲህ እያልን በሀገራችንም በግላችንም ለውጥ ሳናመጣ ያለምንም ትርጉምና ፋይዳ እንኖራለን::

# ሂስ ግለ - ሂስ እና ይቅርታ በሕወሐት ፖለቲካ



ወርቅነህ ማሞ ተሰማ

> **የሕወሐት ባለስልጣን ሆኖ በሰብአዊ ፍጥረት ላይ የአካል እና የሞራል በደል አድርሶ የተወነጀለ አንድም ሰው አላውቅም፡፡ሌላው ቀርቶ እንዲህ ያለው ወንጀለኛ ለስርአቱ አልመች ብሏል ተብሎ ሲገመት ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት የማጥቃት እርምጃ ሲወሰድበት የሚገለጥበት የጥፋት መዝገብ ሁሉም ባለስልጣናት እንደተዘፈቁበት የሚገመተው የሙስና ወንጀል ነው**

ማንኛውም ድርጅት ሆነ ተቋም ቡድን ሆነ ግለሰብ ለሚሰራው ስራ ለሚያከናውነው ተግባር አጋዥ የሆነ ማሽን ወይም የአተገባበር ስልት ወይም ሁለቱም ሊኖሩት ይችላል፡፡ ይህ ማሽን ወይም የአተገባበር ስልት ሌሎች ሰዎችን የሚጐዳ እንኳን ቢሆን የሚገለገልበትን ተቋም ወይም ግለሰብ እስከ ጠቀመ ድረስ የጀርባ አጥንቴ ብሎ ሊመካበት ይችላል፡፡

ከዚህ አንፃር "ሕወሐት" ከጫካ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሲተገብረው የኖረ አንድ የአስራር ስልት አለው ግምገማ፡፡ ይህ ስርአቱ የደም ዝውውሬ ማሳለጫ ነው ብሎ የሚመካበት ግምገማ በውስጡ ሁለት መሠረታዊ ጭብጦችን ይዟል፡፡ ሂስ እና ግለሂስ፡፡ ሂስ እገሌ የእንቶኔን ሐጥያት በስብስባ መሀል የሚዘከዝክበት ሲሆን ግለስ ደግሞ እንቶኔ ሂሱን ውጦ እራሱን እንዴት መርገም እንደሚችል የሚያሳይበት ነው፡፡

ይህ የመረጋገም ስትራቴጂ የድርጅት ሕልውናዬን ጠብቆ እዚህ አድርሶኛል ለሚለው ሕወሐት ትርጉም እንደሚኖረው እንረዳለን ነገር ግን የሐገር እና የህዝብ ስልጣን በእጁ ነው እና ይህ ስልት ለሀገር እና ለሕዝብ ምን ጥቅም አመጣ ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን፡፡

ቀደም ብዬ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የሕወሐት የግምገማ ታሪክ ከደደቢት በረሀ የጀመረ እንደመሆኑ በርካታ የመወነጃጀል እና የመጠላለፍ ታሪኮች እንደሚኖሩት እሙን ነው፡፡ ካልተሳስትኩ በዚህ የታሪክ ሂደት ውስጥ በሰፊው ሕዝብ ጆሮ በመግባት የታምራት ላይኔ ሂስ እና ግለ ሂስ የመጀመሪያው ይመስለኛል፡፡

ይህ የግምገማ ስልት በእኔ እምነት መስሪና ጉልበታም ሆኖ ድርጅቱን በባለቤትነት ይዞ ለሚወጣው ቡድን ካልሆነ በስተቀር ለሀገር እና ለህዝብ ምንም ፋይዳ የሌለው ስለመሆኑ የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር ታምራት ላይኔ የተመዘነበትን መስፈርት ማየት ብቻውን ጥሩ ማስያ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህ ሰው ከስልጣን በመውረጃው ዋዜማ በመረጋገሚያው መድረክ ላይ እሱም ሆነ እረጋሚዎቹ መዘወሪያ ነጥባቸው ሰውየው በሰብአዊ ፍጥረት ላይ ያደረሰውን ግፍ፤ ያፈስሰውን ደም እና ያጠፋውን የሰው ሕይወት የሚጠቃቅስ አልነበረም፡፡ የግምገማው ነጥብ ባከማቸው ቁሳዊ ሀብት እና በላሰው የስኳር መጠን የተገደበ ነበር፡፡ ይህ ነው እንግዲህ የሕወሐት ግምገማ ለራሱ ካልሆነ በቀር ለሐገር እና ለህዝብ ረብ የለሽ ነው የሚያስኘው፡፡የሕወሐት ባለስልጣን ሆኖ በሰብአዊ ፍጥረት ላይ የአካል እና የሞራል በደል አድርሶ የተወነጀለ አንድም ሰው አላውቅም፡፡ ሌላው ቀርቶ እንዲህ ያለው ወንጀለኛ ለስርአቱ አልመች ብሏል ተብሎ ሲገመት ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት የማጥቃት እርምጃ ሲወሰድበት የሚገለጥበት የጥፋት መዝገብ ሁሉም ባለስልጣናት እንደተዘፈቁበት የሚገመተው የሙስና ወንጀል ነው፡፡

በዚህ መልኩ በሚከናወን ግምገማ ሕወሐት በአንድ በኩል ጐረበጡኝ የሚላቸውን አባላቶቹን ሲጠርግበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለህዝብ ስል የመንግስት ሌቦችን እለቅማለሁ በሚል ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን ለማደናገር እየተጠቀመበት ይገኛል፡

በተለያዩ ጊዜያት እንዲህ አይነት መሰሪ የአተገባበር ስልቶችን ስራ ላይ በማዋል የኦክስጂን እጥረቱን ለማመቻመች የሚታትረው ይህ ስርአት፤ይቅርታን የሚያህል በሃሳብ የተለዩትን ሁሉ የሚመታበት ስልት አግኝቶ ያውቃል ማለት ግን ዘበት ይመስለኛል፡፡

## ‹‹ይቅርታ›› ከቅንጅት እስከ ርዕዮት!!!

ካልተሳሳትኩ በሕወሓት ፖለቲካ ውስጥ ይቅርታ ጎላ ብላ መታየት የጀመረቸው በመጀመሪያው የድርጅቱ የመስንጠቅ አደጋ ወቅት ይመስለኛል፡፡ የስርአቱ የይቅርታ ስልት ይበልጥ የደመቀው እና አነጋጋሪ እየሆነ የመጣው ግን ከምርጫ 97 ወዲህ ሳይሆን አይቀርም፡፡ በዚህ ጊዜ "ይቅርታ" ከአፈጣጠሯ ውጪ ቅርፅእና ይዘቷን ቀይራ ዳግም ተሰራች፡፡የበደለ፤ በደል የሚፈፅምበትን መሳሪያ ስለያዘ ይቅርታ የሚጠይቅበት እንዲሁም የተበደለ በደሉን ውጦ በዳዩን ይቅርታ የሚጠይቅበት ሆና ዳግም ተስራች፡፡ስለሆነም ሕወሐት እራሷ ባወጣችው ሕግ የተካሄደውን ምርጫ እንደ አሜሪካኑ ላስቬጋስ እና እንደጣሊያኑ ሲሲሊያ ጉልበታም ቁማርተኞች፤ አሸናፊዎቿን በሞትና በጭንቅ ጎዳና በማሳደድ ያወጣችውን ሕግ ጣሰች፡፡በዚህም ምክንያት ከማሸነፋቸው ውጪ ምንም አይነት በደል ያልነበረባቸውን የቅንጅት አምራሮች ደገፊዎች እና አባላት በግፍ አሰረች፡፡ ሕግ ጥሳ ንፁህንን በግፍ እና በገፍ ያስረቸው ሕወሐት ለመፍታት ሲሆን ግን ሕግ መጣስ ይችግረኛል አለች፡፡ በዚህ ሳቢያ ካሳና ይቅርታ ይገባቸው የነበሩ እስረኞች በሕዝብ እና በሀገር ላይ ባደረሰው ግፍ እና በደል መጠን መቀጣት ለነበረበት ስርአት ይቅርታ እንዲጠይቁ ተደረገ፡፡ ይህ ሁላችንም የምናውቀው እና የቅርብ ጊዜ ታሪካችን በመሆኑ የይቅርታውን ሂደት ለመተንተን አልሞክርም፡፡ ነገር ግን ይህ ቀልድ የሚመስል የታሪክ እውነት በሀገሪቱ የተቃራኒ ፖለቲካና ፖለቲከኞች ላይ ጥሎ ያለፈው ጠባሳ አለና እሱን ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

የሀገሪቷን ሕዝቦች ከዳር እስከዳር አነቃንቀው አንድ ቋንቋ ያናገሩ የፖለቲካ አመራሮች የይቅርታ ፎርም ሞልተው ከወጡ በኃላ ወደ ቀደመ የሞራል ልዕልናቸው ለመመለስ ምን ያህል ጊዜ ፈጀባቸው? በእርግጥ ይህንን የይቅርታ ፎርም የሞሉ በሙሉ ወደ ቀደመ በራስ የመተማመን መንፈስ ተመልሰዋል? አንድ ሆነው በምርጫ ተሳትፈው አንድ ሆነው ታስረው፤ ሲወጡ ብዙ መሆን የፈለጉበት፤ ወደቀድመ እናት ድርጅታቸው መመለስ ወይም አዲስ ፓርቲ ለማቋቋም የመገደዳቸው፤ ምንጭ መተማመን የማጠታቸው ምክንያት ይህ የሞሉት የይቅርታ ፎርም ያስከተለባቸው የሞራል ስብራት አንዱ ምክንያት ሆኖ ሊጠቀስ አይችልም ብሎ የሚከራከር ይኖር ይሆን?

ከዚህ አንፃር ይህ የይቅርታ ፎርም ስርአት ያለመለትን ግብ የመታበት የመሰሪነት ጥግ ሲሆን በሌላ በኩል ለተቃራኒው የፓለቲካ እንቅስቃሴ መልአከ -ሞት ሆኖ እስከ ዛሬ ዘልቋል፡፡

ለዚህ ማስረገጫ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ትልቅ ተስፋን ጭራ የይቅርታ ፎርም እንዳትሆን እንዳትሆን ያደረጋትን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን መጥቀስ በቂ ይመስለኛል፡፡

ይህ ማለት ሕወሐት "ይቅርታን" ከሱ በተቃራኒ የቆሙ እና በሀሳብ የተለዩትን ሁሉ ያለወንጀላቸው አስሮ ፅፎ የሚሰጣቸውን በሚያነቡ ዳኞች አስፈርዶ የይቅርታ ፎርም በማቅረብ የሞራል ልዕልናቸውን ነጥቆ የፕሮፓጋንዳ ቋቱን የሚሞላበት፤ የፖለቲካ ቁማር ነው፡፡

ታሪክ ያስተዋለ ከጠቢብ ይልቃል እንዲሉ አበው፤ የቀደሙት የሄዱበት መንገድ ላይ ታሪክ ያቆማት ወጣቷ ጋዜጣኛ ርዕዮት አለሙ፤ በኢትዮጵያው ጓንታናሞ በማእከላዊ እስር ቤት ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ ፤ይህ የይቅርታ መንገድ ስፋቱ፤ ምቾትና ጥራቱ በቱባ ባለስልጣናት በሚያጓጉ ቃላቶች ቢነገራትም በምድሪቱ ላይ ባሉ ማስፈራሪያዎችና የዛቻ ቃላቶች ተጠቅመው ቢያስፈራሩና ቢዝቱባትም፤ ከዚህም አልፈው የሚሉትን ባታደርግ ወደፊት ሊገጥማት ከሚችለውና ከተዘጋጀላት የመከራ ገፈት ቢያቀምሷትም፤ውስጣዊ እምነትን፤ ነፃነትን እና ሞራልን የሚገፍ ጨዋታ እንደሆነ ከቀደሙት አይታ የማስተዋል እድል ነበራት እና በዚህ ይቅርታ በተባለ ቁማር ተሳታፊ ላለመሆን በጽናት ቆመች፡፡

ይህ ጽናቷ በየጊዜው ተጨማሪ ግፍ እና በደል ቢወልድም የምትወዳቸው እህትና ወንድሞቿን፤ እጮኛዋን፤የቅርብ ዘመድ እና ወዳጅ ጓደኞቿን የማየት በነሱም የመጐብኘት መብቷን የገፈፈ ቢሆንም፤ የዘወትር ስንቅ የማቀበል ተግባር እድሜያቸው በጋፍና ጤና ባጡት ወላጆቿ ትከሻ ላይ መውደቁ የህሊና እረፍት ቢነሳትም፤ በራሷ ላይ እለታዊ እና እጅግ ጥብቅ የሆነ የህክምና ክትትል የሚያስፈልገው የጤና እክል ገጥሟት፤ ተገቢውን ሕክምና በወቅቱና በተገቢው ጊዜ ማግኘት ባትችልም፤ ይልቁንም ሞቷን በሚመኙ የማርሚያ ቤቱ ነርሶች አጅ የመታከም ግዴታ ቢወድቅባትም፤ የመማር መብቷ ከመገፈፉም በላይ የሚነበብ መፅሐፍ እንዳይገባላት ብትከለከልም፤ እራሷ በተለያዩ አታጣሚዎች እንደ ገለጸችው ሌሎች እስረኞች እንዳይቀርቧት ቢደረግም፤ በአጭሩ ርዕዮት በእስር ቤቱ ውስጥ በድጋሚ የታስረች ቢሆንም ከስርአቱ የቁማር ይቅርታ ይህንን ሁሉ ግፍ መቀበልን መርጣ በአቋም እና በእምነቷ ፀንታ ባልሰራችው ወንጀል ከተወሰነባት የአምስት አመት ፍርድ ሶስት አመት ከሰባት ወራት በዚህ ሁኔታ አሳለፈች፡፡

በስርአቱ ወይም ርዕዎት ሲፈረድባት ከተጠቀሰው የሕግ አንቀጽ አንፃር ከአምስት አመቱ የእስር ጊዜዋ ‹‹በማረሚያ ቤቱ››መቆየት የሚገባት ሶስት አመት ከአራት ወር ብቻ ሆኖ አንድ አመት ከስምንት ወር በአመክሮ መነሳት የነበረበትና ይኽም ጊዜ የሚያበቃው ባለፈው ጥቅምት 14 ቀን 2007 የነበረ ቢሆንም ይህንን መፈፀም ለስርአቱ ሽንፈት ሆኖ በመቆጠሩ እሷን ማሸነፍ አስፈላጊ ነው የሚል አቋም የተያዘ ይመስላል፡፡

በመሆኑም ርዕዮት በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ አልሞክረውም ያለችውን እና ይህንን ሁሉ ግፍ ለመቀበል ምክንያት የነበረው የይቅርታ ሰነድ መልክ እና ስሙን ቀይሮ የአመክሮ ፎርም ሆኖ መጣ፡፡

ይህ ሰውን የማዋረድ እና የማንኳሰስ አባዜ የተጠናወተው ስርአት ይህንን ሁሉ ጊዜ ለቁጥር የሚታክቱ በደልና ግፍ ሲፈጸምባት ለነበረችው ሰው "በታሰርኩበት ጊዜ ታርሜአለሁ ተጸፅቻለሁ" ብለሽ ፈርሚ የሚለው በፍፁም ትምክህተኝነት ነው፡፡ ርዕት እንዲህ አይነት የመሞዳሞድ ስብእና ቢኖራት ኖሮ ሦስት አመት ቀርቶ ሦስት ወርም ባልታሰረች ነበር፡፡ ይህ ስርአት ያልተረዳውም ይሄንን ይመስለኛል፡፡ ላለፉት ሦስት አመታት ከመንፈቅ አስቀያሚ የመከራ ጊዜ የገፋችው ርዕየት አንድ አመት ከስምነት ወር ለማትረፍ ክብሯን በስድባቸው እንድትለውጣቸው ሀፍረተ-ቢስ ጥያቄያቸውን ይዘው ከፊቷ ቆሙ ፡፡

የንጽህናዋን መጠን ስለምታውቅ ብቻ ሳይሆን የስርአቱ የይቅርታ ቁማር በሰላማዊ ትግሉና ታጋዮቹ ላይ የሚያስከትለውን የሞራል ስብራት በመገንዘብ፤ ክፉ ልምድ ሆኖ እንዳይቀጥልና አንድ ቦታ መቆም አለበት በሚል እምነት፤ በአቋሟ ለጸናችው ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ ክብር ይገባታል፡፡

# ዜና

# የአንድነት አመራሮች በራዲዮ ፋና ላይ ቅሬታ አቀረቡ

✓ "ራዲዮ ፋና እውነተኛ የህዝብ ሚድያ ቢሆን ኑሮ፣ በህዝብ ገንዘብ 20 እና 30 ፎቅ የሰሩ የኢህአዴግ ባለ ስልጣናትን መጠየቅ ይገባው ነበር" **የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ የአንድነት ም/ፕሬዚደንት**

✓ "የሬዲዮ ፋናው ፕሮግራም "ሞጋች" ሳይሆን "ለኢህአዴግ ብቻ ተሟጋች" ተብሎ መቀየር አለበት፡፡" **አቶ ስዩም መንገሻ የአንድነት ዋና ፀሐፊ**





የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አመራሮች "ከሬዲዮ ፋና ጋር ጥር 10 2007 ዓ.ም ያደረግነው ቆይታ የጋዜጠኝነትን ስነ ምግባር እጅግ የጣሰና አሳፋሪ ነበር" ሲሉ ለሚሊዮኞ ድምፅ ጋዜጣ ገለፁ፡፡ የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድት) አመራሮች የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉና አቶ ስዩም መንገሻ ስለራዲዮ ፋና ቆይታቸው ለጋዜጣችን ሲገልጹ፣ "ስለ ፓርቲው ትክክለኛና ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን በድምፅ ሰጥተን ብንመለስም ተቆርጦና ተቀጥሎ እጅግ ከጋዜጠኝነት ሙያ ስነ ምግባር ውጭ የሆነ ደባ እና በደል ተሰርቶብናል" ብለዋል፡፡ "በተለይም የፕሮግራሙ አዘጋጅ አቶ ብሩክ መኮንን ከአንድ ጋዜጠኛ የማይጠበቅና እጅግ የሰነ ምግባር ዝቅጠት የታየበት ስራ በመስራት፣ የታዘዘውን ፕሮፕጋንዳ ለማስፈፀም የተቀጠረ መሆኑን በተግባር አሳይቷል" ብለዋል፡፡ ለዚህም ማሳያ "ጋዜጠኛው እኛን የአንድነት ፓርቲ አመራሮችንና አኩራፊዎቹን ግለሰቦች ሲጠይቅ የነበረበት ሁኔታ በጣም አሳፋሪ ነበር" ሲሉ አክለዋል፡፡

"ድሮውንም ቢሆን ሬዲዮ ፋና ለኢህአዴግ እንጂ ሌሎችን ፓርቲዎች ለማጠልሸት የሚታትር የተንኮልና የሴራ ቦታ ነው፡፡ ለሬዲዮ ፋና ብቻ የሰጠነውን ቃል-ምልልስ በቪዲዮ በመቅረፅ ያለ እኛ ፈቀድ ለገዥው ፓርቲ ሚድያ ኢቢሲ(ኢቲቪ) መስጠቱ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡" ያሉት የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ "የሙያው ስነ ምግባር ከሚፈቅደው ውጪ ለግል ጥቅም በአድርባይነት የቆመ ሚዲያ መሆኑን በግልፅ ያሳየ ነው፡፡" ሲሉ አስታወቀዋል፡፡ አቶ ግርማ አክለውም "ጋዜጣኛው ካለ ምንም መረጃ የፓርቲውን ብሎም የእኛን የአመራሮችን ስም ለማጥፋት ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም ለምሳሌ እኔን በግል ስምህ ከውጭ የፓርቲው ደጋፊዎች ገንዘብ ይላክልሃል እስከ ማለት ደርሷል፡፡" ብለዋል፡፡

በተመሳሳይም አቶ ስዩም መንገሻ የአቶ ግርማን ሃሳብ ተጋርተው ስለ እርሳቸው ጋዜጣኛው ያለውን እንዲህ አስረድተዋል፡፡ "ጋዜጠኛው ወደ ጥያቄና ወደ ህዝብ ጆሮ ከመድረሱ በፊት ስራውን በደንብ ጠንቅቆ አውቆ መረጃ ማቅረብ እያለበት በእንዝህላልነትና በአጯፋሪነት ስሜን ለያጠፋ ሞክሯል፡፡" ካሉ በኋላ "ለለዚህም ማሳያ እኔ ብርሃን ፓርቲን የተቀላቀልኩ ከ3 አመት በፊት ሲሆን አንድትን የተቀላቀልኩት ከ1 አመት በፊት ሆኖ እያለ ጋዜጠኛው ያለምንም ማስረጃ በቀላሉ ንግድ ሚኒስቴር ሂዶ ማረጋገጥ እየቻለ ከ10 አመት በፊት በስሜ ተመዝግቦ የሚገኘውን ንብረት ‹በፓርቲው ገንዘብ የተገዙ ናቸው› እስከ ማለት የደረሰ መረጃ ያጠረው ጋዜጠኛ ነው፡፡" ብለዋል፡፡ "ሆኖም ግን ሬዲዮ ፋናን እንደጠበቅነው ነው ያገኘነው ከዚህ የተለየ እንደማይሰራ እናውቅ ነበር፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያን ህዝብ መረጃ የማግኘት ነፃነት አክብረን ተገኝተናል፡፡ ጣቢያው ትክክል እንደማይሰራልን ስለምናውቅ ራሳችን ቀርፀን ያስቀረነው የውይይቱ ድምፅ በዕጃችን ስለሚገኝ ባገኘነው አጋጣሚ ለህዝብ በማድረስና የሬዲዮ ፋናን የሴራ ጥንስስ እናከሽፋለን፡፡" በማለት ጠቁመዋል፡፡ አቶ ስዩም ሲያጠቃልሉ "የፌዲዮ ፋናው ፕሮግራም "ሞጋች" ሳይሆን "ለኢህአዴግ ብቻ ተሟጋች" ተብሎ መቀየር አለበት፡፡" ብለዋል፡፡

አቶ ግርማ በበኩላቸው "ራዲዮ ፋና እውነተኛ የህዝብ ሚድያ ቢሆን ኑሮ እኛን በሃሰት መረጃ ፎቅ ሰራችሁ፣ መኪና ገዛችሁ እያለ የሌለ ነገር ለመለጠፍ ከሚለፋ 20 እና 30 ፎቅ የሰሩ የኢህአዴግ ባለ ስልጣናትን መጠየቅ ይገባው ነበር፡፡ ነገር ግን አላማው ያ አያደለም፡፡" ሲሉ በራዮ ፋና ላይ ትችት ሰንዝረዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ግርማ፡፡ "በተለያዩ የገዢው ፓርቲ ሚዲያዎች የማያባራ የስም ማጥፋት ዘመቻ የሚደረግብን እኛ አንድነቶች ከወትሮው በተለየ የምርጫ ቦርድን "ባለህበት እርገጥ" ስትራቴጂ አለመቀበላችንና ለምርጫ ቦርድም፣ ለኢህአዴግም እንቅልፍ የሚነሳ መነቃቃት በፓርቲያችን ስለተፈጠረ ነው" ብለዋል፡፡

## ቢቢሲ አፍሪካዊ ጋዜጠኛ እየፈለገ ነው

**በምስክር ዓወል**

ቢቢሲ ባለፈው ዓመት በድንገተኛ የልብ ህመም ምክንያት በሞት የተለየውን ጋናዊ ጋዜጠኛ ኩሙላ ዱሞርን ሌጋሲ የሚያስቀጥልልኝ አፍሪካዊ ጋዜጠኛ እፈልጋለሁ ሲል ገለጸ፡፡

የሶሾሎጂ ፕሮፌሰር ከሆነው አባቱና የማስኮሚኒኬሽን ባለሙያ ከሆነችው እናቱ የተወለደው ኩምላ፣ በአጭር ጊዜ የህይወት ቆይታው ወቅት ሀገሩ ጋናን ብሎም አህጉሩ አፍሪካን በዓለም አቀፍ ደረጃ በማራኪና መረጃን መሰረት ባደረገ ዘገባው ያስተዋወቀ የአፍሪካ ልጅ ነው፡፡

ኩምላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ በናይጄሪያ ጆስ ዩኒቨርሲቲ ህክምና እንዲያጠና ተመድቦ የነበረ ቢሆንም ሳይገፋበት አቋርጦ በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ጋና በሶሾሎጂ የመጀመሪያውን ድግሪውን ተቀብሏል፡፡ በመቀጠልም በሕዝብ አስተዳደር የሙያ ዘርፍ ከሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የማስተርስ ድግሪ እንደተቀበለ ቢቢሲ በድህረ ገጹ አስነብቧል፡፡

በሥራውም እ.አ.አ ከ2000 እስከ 2006 በአክራ ጆይ ኤፍ ኤም እና ፎክስ ኦን አፍሪካን፣ ቢቢሲ ወርልድ ኒውስና ዘ-ወርልድ ቱደይ በተሰኙት ተወዳጅ ፕግራሞች ላይ ሰርቷል፡፡ በእ.አ.አ 2003 የጋና የጋዜጠኞች ማኅበር የሚያዘጋጀውን ዓመታዊ የምርጥ ጋዜጠኝነት ሽልማትን ወስዷል፡፡ በ2014 ኒው አፍሪካ የተሰኘው መጽሔት በዓመቱ ተጽዕኖ ፈጣሪ ካላቸው የ100 ሰዎች ስም ዝርዝር ውስጥ ስሙን አካትቶ አውጥቶታል፡፡ ሆኖም ቢቢሲ የኩምላ ዲሞሮን ለመተካት በአፍሪካ የሚገኙ ጠንካራ የጋዜጠኝነት ሙያን ከተለያዩ የግል ብቃቶች ጋር አጣምሮ የያዙና አፍሪካዊ ጉዳዮችን መስራት የሚችሉ አፍሪካውያንን ‹‹የወደፊት ኮከባችን ማድረግ እፈልጋለሁ›› ሲል አስታውቋል፡፡

አሸናፊውም ካለበት የአፍሪካ ክፍል ወደ ለንደን ተወስዶ በቢቢሲ አማካኝነት የአፍሪካንን ጉዳይ ለዓለም የማስተዋወቅ ዕድሉን እንዲያገኝ ይደረጋል ተብሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ በመላው ዓለም ካሉ የቢቢሲ ባልደረቦች ጋር ልምድ እንደሚለዋወጥና በቢቢሲ የማሰልጠኛ ተቋም ልዩ የሆነ ትምህርት እንደሚሰጠው ቢቢሲ አስታውቋል፡፡ ድረ-ገጹም አሸናፊው በቴሌቪዥን፣ በራዲዮና በኢንተርኔት በዓለም ላይ ለሚገኙ 265 ሚሊየን በላይ የቢቢሲ አድማጮችና ተመልካቾች ማስተላለፍ እንደሚችል ጠቅሷል፡፡

## ሰማያዊ ፓርቲ በስካይፒ የፓናል ውይይት አካሄደ



ሰማያዊ ፓርቲ ምርጫ 2007ትን አስመልክቶ ምርጫውን በተሳካ ሁኔታ ማካሄድ ስለሚቻልበት ሁኔታ ከትናንት በስትያ ጥር 11 ቀን 2007 ዓ.ም በሀገር ውስጥና በውጭ ያሉ ሰዎችን ያካተተ የፓናል ውይይት እና የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት አካሄደ፡፡

በሀገር ውስጥ የተካሄደው ዝግጅት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተጀምሮ አምስት ሰዓት ላይ የተጠናቀቀ ሲሆን ውጭ ያሉት አባላት ግን ሀገር ቤት ያለው ቢጠናቀቅም ከዛ በኋላም ሳያቋርጡ ቀጥለዋል፡፡ በስካይፒ ውይይቱ ላይ አቶ አባንግ ሜቶ፤ የዞን 9 ጦማሪ የሆነቸው ሶልያና ሽመልስ፤ እንዲሁም የ97 ምርጫ አጣሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የነበሩት ዳኛ ፍሬህይወት ሳሙኤል ከሀገር ውስጥ ደግሞ ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም፣ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ እንዲሁም የፓርቲው ፕሬዝዳንት የሆኑት ኢ/ር ይልቃል ጌትነት ተሳትፈውበታል፡፡ በሁለቱም ጉባኤ ላይ ከ170 ሰዎች በላይ ተሳትፈዋል፡፡

በውይይቱ ላይ የፓርቲው ፕሬዝዳንት የሆኑት ኢ/ር ይልቃል ጌትነት፡- ‹‹ለውጥ ይመጣል፤ የሚመጣው ለውጥ እንደ እስከዛሬው እንዳይከሽፍ ግን ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ቡድኖች በራሳችን ላይ አብዮት ማካሄድ አለብን፤ ከእስካሁኑ የተለየ ለውጥ አምጥተን የኢትዮጵያን ህዝብ የሥልጣን ባለቤት ማድረግ አለብን፡፡›› በማለት ተናግረዋል፡፡

በተያያዘም ፓርቲው በቀጣይ የካቲት 15 ቀን 2007ዓ.ም የተቃውሞ ሰልፍ ለማካሄድ እየሰራ መሆኑን የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አቶ ዮናታን ተስፋዬ ለሚሊዮኞች ድምፅ ጋዜጣ ገልጸዋል፡፡

# የጤናማ ኢኮኖሚ ዕድገት መለኪያው ምንድነው?



**አቶ ተመስገን ዘውዴ**

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ጥንካሬ የሚለካው ኢኮኖሚው አዳዲስ ስራዎችን መፍጠር በመቻሉ፤ ከዚያም በተፈጠሩት ስራዎች ምክንያት ህዝቡ ተመጣጣኝ ገቢ በማግኘት ረገድ ለዜጎች ትልቅ ፋይዳ ሲኖረው፤ መንግስት ከግብርና ከሌሎች ምንጮች በቂ ገቢ በማግኘት ሰፊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ስራዎችን መሥራት ሲችል ነው።

ኢኮኖሚው በትክክል የተቀረፀ የፖሊሲና የስትራቴጂ አቅጣጫ በመያዝ ውጤታማ መሆኑንና ያለመሆኑን በመመልከት አቅጣጫና ስልት ለመቀየስ እንዲረዱ የተወሰኑ የMacro economy ሂደቶች ጤናማ መሆናቸውን ማየት አስፈላጊ ተደርጎ ይወሰዳል። ከእነዚህ ማሳያዎች ውስጥ አንዱ ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት በመባል የሚታወቀው ሲሆን፤ ይህም ለብሔራዊ ምርት (GNP) በፍጥነት ማደግና መቀነስ አሉታዊና አዎንታዊ ተፅዕኖዎች ይኖሩታል። የመንግስት ኢኮኖሚ ፖሊሲ አስፈጻሚዎች ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ብሔራዊ ምርቱ በፍጥነት ማደጉን አዎንታዊ አድርገው የሚያቀርቡበት ሁኔታ ቢኖርም በተለያዩ ምክንያቶች የብሔራዊ ምርት ፈጣን ዕድገት ጤናማ ያልሆኑ ውጤቶች እንዳሉትና ወቅታዊ እርምቶች ካልተደረጉ በዜጎች ኑሮና ህይወት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ መረዳት ያስፈልጋል።

የብሔራዊ ምርት እድገት ስሌት መንግሥት ለጤና፤ ለትምህርት፤ ለመሰረተ ልማት፤ ለመከላከያ፤ ወዘተ.... ከጠቅላላው ብሔራዊ ምርቱ ምን ያህሉን) እንደመደበ ለማወቅ ይረዳል። ይሁን እንጂ የኢኮኖሚው በፍጥነት ማደግ ተፈላጊ መስሎ ቢታይም ፈጣን እድገት የራሱ የሆነ አደጋም አለው።ይሄ አደጋ እንዳይከሰት መንግስት ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ቢታወቅም፤ የኢኮኖሚ እድገቱን ተመጣጣኝና ጤናማ ማድረግ የሚያስከፍለው የፖለቲካ ዋጋ ይኖራል፡፤ በመሆኑም የአንዳንድ ሀገር መንግስታት የኢኮኖሚ እድገቱን እንዳለ ማስቀጠልን ይመርጣል። በዚህ መንገድ የዋጋ ግሽበት ችግሮችን (Inflation) የኢኮኖሚ ማሽቆልቆልን፤ (Recession) የሥራ አጥነትን (Unemployment) ጉዳይ አለባብሰው ለማለፍ በመሞከር ሀገራቸውን ለከፋ የኢኮኖሚ ቀውስ ሲያጋልጡ ይስተዋላል። ኢኮኖሚው በከፍተኛ መጠን ሲያድግ ጠቅላላ ፍላጎትና (Aggrgate demand) እና ጠቅላላ አቅርቦት (Aggrgate supply) ካልተጣጣሙ በምርቶች ላይ የዋጋ መዋዠቅም መታየቱ የማይቀር ነው።

እንግዲህ የጠቅላላ አቅርቦት፤ ፍላጎት፤ የመንግሥት የታክስ አሰባሰብና የገንዘብ ፍሰት ቁጥጥር እጦት የሚያመጡትን የኢኮኖሚ አለመረጋጋት ከመሰረቱ ለመቅጨት በመንግሥት በኩል የሚወሰዱ አንዳንድ የተለመዱ እርምጃዎች አሉ። ይሁን እንጂ በመንግሥታት በኩል እነዚህን መፍትሔዎች ሥራ ላይ ለማዋል ቁርጠኝነት አይታይም። በዚህም የተነሳ የብሔራዊ ምርት በፍጥነት ከማደግ ይልቅ የሚያሽቆለቁልበት፤ ሥራ አጥነት የሚስፋፋበት፤ የንግድና ኢንዱስትሪ ባለቤቶች በሙሉ አቅማቸው ለመንቀሳቀስ የማይችሉበትና ሸማቹ ህብረተሰብም መሠረታዊና እለታዊ ፍላጎቱን ጭምር ማርካት የማይችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በዚህም ምክንያት በጠቅላላ ኢኮኖሚው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ፈረንጆቹ (Reccssion) የሚሉት የኢኮኖሚ ወቅት (Cycle) ያጋጥማል። በነፃ የገበያ ኢኮኖሚ የዋጋ ንረትንም ሆነ መውደቅን የሚያስከትሉ ጉዳዮች በኢኮኖሚ ፖሊሲ አውጪው አካል ከፍተኛ ክትትል ካልተደረገባቸው በህዝብ ኑሮ ላይ የሚያደርሱት መመስቃቀል እጅግ ከፍተኛ ነው።

ሁለተኛው የኢኮኖሚ ጤንነት አመላካች ሥራ አጥነት (Unemployment) ሲሆን፤ የጤናማ ሲሆን፤ የጤናማ Macro economy ሁኔታን የሚገልፀው ኢኮኖሚው በሚፈጥራቸው አዳዲስ የሥራ መስኮችና በዚህም ምክንያት የዜጎች ሥራ መያዝና መንግሥት ከታክስና ከሌሎች ምንጮች የሚያገኘው ገቢ መጨመር ነው።

ሦስተኛው የጤናማ ኢኮኖሚ መለኪያ የጠቅላላ የዋጋ ግሽበት ደረጃ ሲሆን ለዚህም በተመረጡ ምርቶች ላይ የዋጋ ጥናት በማድረግ በየጊዜው በሚደረጉ የዋጋ ለውጦች መሰረት የኑሮ ውድነት ስሌት ወይም በእንግሊዘኛው Consumer price Index (CPJ) የሚባለው መለኪያ ነው። ይህ መለኪያ የዋጋ ንረቱ ከአንድ ከተመረጠ ዓመት ወይም (Base year) ጋር እየተነፃፀረ የምርት ዋጋ መናር ( Cycle in flationary) መሆንና ያለመሆንም የሚገለፀው በዚሁ (Consumre price) መጨመርና መቀነስ ነው።

መንግሥት የኢኮኖሚ እድገቱን ለማስቀጠል የዋጋ ንረቱን መቆጣጠር ይኖርበታል። ይሄ ደግሞ ለፖለቲካ ፍጆታ ሳይሆን ለሀገር ደህንነትም ሲባል የፖለቲካ ቁርጠኝነት ይጠይቃል። ቀደም ብለን ለመግለጽ እንደሞከርነው ብሔራዊ ምርት (GNP) እድገት ማሳየቱ ጥሩ ነገር ቢሆንም በፍጥነት ማደጉ ወይም ብሔራዊ ምርቱ በፍጥነት መቀነሱ ወይም (Recession) በዋጋ ንረትም (Inflation) ሆነ እና በስራ አጥነት (Unemployment) ወይም በጠቅላላው ኢኮኖሚው እንዳይረጋጋ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው።

የሀገር ሁኔታዎች ጥንካሬና ድክመት ከላይ በተገለፁ 1/ የብሔራዊ ምርት በፍጥነት እድገት መቀነስ፤ 2/ በሥራ አጥነት (Unemployment) 3/ በዋጋ ግሽበት (Inflation) የሚገለጹ ቢሆንም ለእነዚህም ችግሮች መከሰት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሌሎች ሁኔታዎች አሉ። ለማንኛውም የኢኮኖሚው በፍጥነት ማደግ ወይም በፍጥነት ማሽቆልቆል (GNP) ጉዳይ የሚያስከትለውን የኢኮኖሚ ቀውስ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሰለጠኑ ሀገሮች ምርታማነትን (Prodctivity) በማበረታታት ብሔራዊ ምርቱ ሳይጨምር ኢኮኖሚው በምርታማነት ከሚገኘው ውጤት ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋሉ። የመንግሥት የታክስና ግብር አሰባሰብን በማስፋፋትና ፍትሐዊ እንዲሆን በማድረግ ዜጎች ስለግብርና ታክስ ያላቸው አመለካከት የተስተካከለ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል። ግብር ከብሔራዊ የጋራ ጥቅም ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅ መሆኑን በማሳየት፤ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ብቻ ከዚህ ተጠቃሚ መሆናቸውን በማስቀረትና ለሙስና በር ከፋችነቱን በማጥበብ መንግስት ግብርን የኢኮኖሚ እድገትና መረጋጋት መሰረት ሊያደርገው ይችላል። የተረጋጋ ኢኮኖሚ ያላቸው ሀገሮች መንግስት አስተማማኝ የግብር ገቢ ፈሰስ የሚያገኙባቸውንና በእነዚህም ምክንያት መንግሥት ወጪና ገቢውን አጣጥሞ ኢኮኖሚውን የሚመራባቸው ዋነኛ የተረጋጋ ኢኮኖሚ መሳሪያ ናቸው።

የአንድን ሀገር ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ የEconomy cycel (Inlation Recession,deflation ) ወዘተ ማለፉ ስለማይቀር እነዚህን ሁኔታዎች ተቆጣጥሮ የኢኮኖሚ መረጋጋትን ለማረጋገጥ Fischal እና montery Policy tools ሥራ ላይ ማዋል ተገቢነት አለው።ከእነዚህ መፍትሔዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

1.የመንግሥት ወጪን እንደ ወቅቱ የኢኮኖሚ መጨመርና መቀነስ

2.ከግብር የሚሰበሰበው ገንዘብ መጠን እንዲጨምር ለማድረግ የግብር ከፋዩ ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ

3.በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው የገንዘብ ፍሰት እንደ ሁኔታው እንዲጨምር እና እንዲቀንስ ማድረግ

4.የባንኮች መጠባበቂያ Reserve Requirment እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ማድረግ

5.የባንኮች ብድር እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ለማድረግ ወለድን መቀነሰ ወይም መጨመር

6.የወለድ መጠን እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ማድረግ

7.የኢኮኖሚው ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግ

8.የባጀት Deficit እንዲቀንስ ማድረግ.... ወዘተ ናቸው።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ መፍትሔዎችን በመጠቀም ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት የሚቻል ቢሆንም ከዚሁ ጋር እያንዳንዱ መፍትሔ የሚያስከትለውን ጉዳትና ጥቅም ለይቶ ማስላት ካልተቻለ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፡፤ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዙሪያ ከምንሰማቸውና በጥቂቱም ቢሆን ከምናነባቸው ትንታኔዎች በመነሳት መንግስት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገትን ዋነኛ ስልቱ አድርጎ እንደተነሳና በዚህም ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ምክንያት የሚከሰቱ የኢኮኖሚ አለመረጋጋቶች ከቁምነገር ያልቆጠራቸው መሆኑን ለመገንዘብ ችለናል።

ባለፉት አምስት አመታት መንግስት ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ባንኮች የሚይዙትን የመጠባበቂያ ገንዘብ ከአምስት በመቶ ወደ አስራ አምስት በመቶ ሲያሳድግ የባንክ ወለድ መጠንንም ከሶስት በመቶ ወደ አራት በመቶ ማሳደጉን ገልፃሁ*ል። ሆኖም እነዚህ እርምጃዎች በቂ ያለመሆናቸውንና መንግስት በተጨማሪ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ወጪውን መቀነስና የባንክ ወለድ መጠንን ከፍ ማድረግ እንዳለበት የገበያ ሁኔታዎች ያመለከታሉ። አንዱና ዋነኛው የኢኮኖሚ እድገት የሚገኘው ዜጎች በባንክ ሂሳብ ቁጠባ ነው። ዜጎች በባንክ የሚቆጥቡትን ገንዘብ ባንኮች ለተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራ ስለሚያበድሩ የኢኮኖሚ እድገቱ ሀገር በቀል እንዲሆን ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

በሀገራችን ተመዝግቧል የተባለው የኢኮኖሚ እድገት ከዜጎች የቁጠባ ባህል መዳበር ጋር የተያያዘ ነው ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም ለቁጠባ የሚከፈለው ወለድ ዝቅተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ካለው የዋጋ ግሽበት አንጻር ዜጎች እንኳን በባንክ ሊቆጥቡ ይቅርና በሚያገኙት ገቢ ከወር እስከ ወር መድረስና መሰረታዊ ፍላጎታቸውንም ማሟላት አልቻሉም። ስለዚህ እድገቱ ከየት መጣ? እድገቱ በዋነኛነት የተገኘው የበጀት ጉድለት (Budjet Deficit) እንዲጨምር በማድረግ ያላመረትነውን እየበላን መጪው ትውልድ እዳውን እንዲከፍል በማድረግ ነው? ይሄ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል።

በመጨረሻም የሀገር ኢኮኖሚ ጤናማ እድገት የሁሉንም ዜጎች ተሳትፎ የሚጠይቅና ችግሩም በአንድ ገዥ ፓርቲ እይታ ብቻ የሚፈታ ጉዳይ እንዳልሆነ በፍጥነት መገንዘብ የመፍትሔው አካል መሆኑ ሊታሰብበት ይገባል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት አንዱን ወገን የሚያስደስት ሌላውን የሚያሳስብ ሳይሆን ጉዳዩ የሁላችንም በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያየ እይታ ያላቸው ወገኖች ለኢኮኖሚ እድገቱ መፍትሔ ይሆናሉ የሚሏቸውን ሃሳቦች ሁሉ እንዲያቀርቡ መንግስት መድረኩን የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።




“የሚሊዮኖች ድምጽ” ዝግጅት ክፍል በእስር ላይ ለምትገኘው ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ መልካም ልደት ይመኛል።

